# ኢትዮጵያ

## የመጨረሻ አተታ (ሪፖርት)

## የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
## እና የክልል ምክር ቤት ምርጫዎች
## ግንቦት 2002

## የአውሮፓ ኅብረት
## የምርጫ ታዛቢ ልዑክ

ይህ አተታ (ሪፖርት) በአውሮፓ ኅብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ በኢትዮጵያ 2002 የተጠናቀረ ሲሆን የልዑኩን የግንቦት 15/2002 ዓ.ም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የምክር ቤት ምርጫዎች ግኝቶች ያቀርባል። እነዚህ አቋሞች በአውሮፓ ኮሚሽን ተቀባይነት አግኝተው የጸደቁ ባለመሆናቸው እንደ አውሮፓ ኮሚሽን መግለጫ አድርጎ በመውሰድ ሊታመኑበት አይገባም። የአውሮፓ ኮሚሽን በዚህ አተታ ውስጥ የተካተቱትን ዘገባዎች ትክክለኛ ስለመሆናቸው ዋስትና አይሰጥም፣ እንዲሁም ደግሞ እዚህ ላይ ለዋለው ለየትኛውም ጥቅም ኃላፊነቱን አይቀበልም።

ይህ ሪፖርት (ሀተታ) በእንግሊዝኛና በአማርኛ ተዘጋጅቷል፤ ኦፊሽያል የሆነው የእንግሊዝኛው ቅጂ ብቻ ነው።

ማውጫ


I. የአፈጻጸም ማጠቃለያ ........ 1

II. መግቢያ ........ 4

III. ፖለቲካዊ ዳራ ........ 4

ሀ. ፖለቲካዊ አውድ ........ 4
ለ. አውራ ፖለቲካዊ ተዋናዮች ........ 5

IV. ህጋዊ እና የምርጫ አውታር ........ 6
ሀ. የህጋዊ አውታር ........ 6
ለ. አለማቀፍ እና ክልላዊ ግዴታዎች ........ 6
ሐ. የምርጫ ህግጋት ........ 7
መ. የምርጫው ሥርዓት ........ 7
ሠ. የምርጫ ክልሎች ወሰን ........ 8
ረ. “ልዩ” የአነስተኛ ቁጥር ያላቸው የምርጫ ክልሎች ........ 8

V. የምርጫ አስተዳደር ........ 8
ሀ. የምርጫ አስተዳደር መዋቅር እና ቅንጅት ........ 8
ለ. የምርጫዎች አስተዳደር ........ 9
ሐ. የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ........ 9
መ. የህዝብ ታዛቢዎች ........ 9
ሠ. የመራጮች ትምህርት ........ 10
VI. የመራጮች ምዝገባ ........ 10
ሀ. የመምረጥ መብት ........ 10
ለ. የመራጭ ምዝገባ ........ 11

VII. የእጩዎች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ ........ 12
ሀ. የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ ........ 12
ለ. የእጩዎች ምዝገባ ........ 12

VIII. የምርጫ ቅስቀሳ እና የቅድመ-ምርጫ ከባቢያዊ ሁኔታ ........ 13
ሀ. የምርጫ ቅስቀሳ ውዳራ ........ 13
ለ. የምርጫ ቅስቀሳ ውድባብ ........ 13
ሐ. የእጩስንብት ........ 14
መ. የመንግስት ጥሪት አጠቃቀሞች ........ 15
ሠ. ለቅስቀሳ የዋለ ገንዘብ ........ 15

IX. ብዙኃን መገናኛ እና ምርጫ ........ 16
ሀ. የብዙኃን መገናኛው ሁኔታ ........ 16
ለ. የመገናኛ ብዙሃንና የምርጫ ህግ ማዕቀፎች ........ 16
ሐ. የምርጫዎች የብዙኃን መገናኛ ሽፋን ቁጥጥር ........ 17

X. ሰበዓዊ መብቶች እና የሴቶች ተሳትፎ ........ 18
ሀ. የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታዎች ........ 18
ለ. የሴቶች ተሳትፎ ........ 19

XI. የሲቪል ማህበራት እና የሃገር ውስጥ ምርጫ ታዛቢዎች ተሳትፎ ........ 20

XII. አለማቀፍ የምርጫ ታዛቢ ........ 21

XIII. ቅሬታዎች እና አቤቱታዎች ........ 21
ሀ. ሕግ አውጪ የፍትህ አካላት ........ 21
ለ. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ (ኢብምቦ) እና ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ........ 22
ሐ. የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥምር ምክር ቤቶች ........ 24

መ. የምርጫ ጥፋቶች ........ 24

XIV. የምርጫ ቀን ........ 25
ሀ. አከፋፈት ........ 25
ለ. ድምጽ አሰጣጥ ........ 25
ሐ. አዘጋግ እና ቆጠራ ........ 25

XV. ውጤቶች እና የድህረ-ምርጫ ሁኔታ ........ 26
ሀ. የጊዜያዊ የምርጫ ውጤቶች ይፋ መሆን ........ 26
ለ. በምርጫ ክልል ቢሮዎች የነበረው የውጤት ተደምሮ መጠቃለል ........ 26
ሐ. በኢምቦ ዋና መስሪያ ቤት የነበረው የውጤት አሰራር ........ 27
መ. የድህረ-ምርጫ ሁኔታዎች ........ 27
ሠ. የምርጫ አቤቱታዎች ........ 28
ረ. የመጨረሻው ውጤት ህትመት ........ 29
ሰ. የምርጫ ውጤቶች ፖለቲካዊ ድባብ ........ 29

XVI. የማጠቃለያ አስተያየት ........ 30

# I. የአፈጻጸም ማጠቃለያ

ኢትዮጵያ አራተኛውን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ህተም) እና የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ ለአራተኛ ጊዜ ግንቦት 15/2002 ዓ.ም አካሄደች። የአውሮፓ ኅብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ (አኅ ምታል) ከኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከብሔራዊ የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ (ብኢምቦ) የደረሰውን ግብዣ ተከትሎ ከመጋቢት 5 እስከ ሰኔ 14 ቀናት 2002 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ ተገኝቶ ነበረ። አኅ ምታል የአውሮጳ ፓርላማ አባል በሆኑት በሚ/ር ቲጅስ በርማን የተመራ ነበረ። ልዑኩ ከ 25 የአውሮፓ ኅብረት መንግስታት እንዲሁም ከኖርዌይ፣ ስዊዘርላንድ እና ካናዳ የተውጣጡ 170 ታዛቢዎች የምርጫውን ሂደት ከአለማቀፍ እና ከክልላዊ የምርጫ ግዴታዎች እንዲሁም ከኢትዮጵያ ህግጋት አንጻር እንዲገመግሙ ወደ ሁሉም የሃገሪቱ ክልሎች አሰማርቷል። አኅ ምታል በደረሰባቸው ግኝቶች እና ድምዳሜዎች ገለልተኛ ሲሆን በጥቅምት ወር 1998 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት በተዘጋጀው *የዓለምአቀፍ የምርጫ ታዛቢ አዋጅ መርሆች* ተገዢ ነው፡ ፡ በምርጫው ቀን አኅ ምታል ታዛቢዎች የምርጫ እና ቆጠራውን ሁኔታ ለመታዘብ 815 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን እያንዳንዱን የኢትዮጵያ ክልሎች ጎብኝተዋል።

ግንቦት 15 ቀን 2002 ዓ.ም ምርጫው በአጠቃላይ ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ ሁሉም ተፎካካሪዎች በሙሉ ድምፅ እንደተስማሙበት ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ ተከናውኗል። በአንጻራዊነት ፀጥተኛ ይመስል የነበረው በተቃዋሚ ፓርቲዎች እና በገዢው የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) የተከናወነው የምርጫ ቅስቀሳ ወደ መጨረሻው ደረጃ ላይ በግለት አድጎ ነበር። ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ (ኢብምቦ) የምርጫውን ሂደት ቀልጣፋ እና ብቃት ባለው መንገድ በሰፊው የተቆጣጠረ ቢሆንም የምርጫ ድምሮችን ያጠቃለለበት መንገድ ግን አነስተኛ ምስጋና የሚያሰጠው ነው። የምርጫ ባለስልጣናት በገለልተኛነታቸው ላይ ያለውን የተቃዋሚ ፓርቲዎች እምነት ማጣት ሊያስወግድ አልቻለም። ከ 1997 ምርጫዎች ጀምሮ አያሌ አዎንታዊ መሻሻሎች የታዩ ቢሆንም ህጋዊ እና የምርጫ አውታሩን መተግበርን በተመለከተ ግን አሉታዊ የሆኑ አካሄዶች ነበሩ። በውጤቱም የምርጫው ሂደት ለምርጫ የተቀመጡትን አለማቀፋዊ ግዴታዎችን ያላሟላ ነበረ። አስፈላጊ በሆነው የሂደቱ ክፍል ውስጥ ግልጽነት እና ለሁሉም ተቃዋሚ ፓርቲዎች የተመቻቸ የመጫወቻ ሜዳ ማዘጋጀት ያለመቻል ጉድለት ነበረው። የበለጠ ተገቢ እና ወካይ የምርጫ ሂደትን ለማረጋገጥ የሚያስችል በቂ የሆነ ጥረት አልተካሄደም።

የኢትዮጵያ ህገ መንግስት እና የህግ አውታሩ ኢትዮጵያ ከፈረመቻቸው አለማቀፍ እና ክልላዊ ግዴታዎች አንጻር ሐቀኛ ለሆኑ ምርጫዎች በቂ የሆነ መሰረትን ያቀርባል። ህገ መንግስቱ፣ የምርጫው ህግ እና ሌሎች የምርጫ ነክ ደንቦች ፖለቲካዊ እና የሲቪል መብቶችን የሚያስጠብቁ ሲሆን ሐቀኛ የሆኑ ምርጫዎች እንዲካሄዱም ይፈቅዳሉ። እንዲሁም ደግሞ የማህበራት፣ የተሰብሳቢዎች፣ የእንቅስቃሴዎች እና የመግለጫዎችን ነጻነትንም ይፈቅዳል። ይሁን እንጂ ስለ ምርጫው የተቀመጡ የአንዳንድ ህግጋት እና ደንቦች ተግባራዊ አፈጻጸም ግን እነዚህን ግዴታዎች ከሚያጸኑ መርኾዎች በተቃራኒ በአንዳች አይነት መንገድ የተገላቢጦሽ ሆነው የተገኙ ናቸው። የምርጫ ሂደቱ ከዚህ የተነሳ አስገዳጅ፣ ልክ እንደተሟላ አይነት፣ አድልዎ ያልታየበት፣ የመሰረታዊ መብቶች ፍስሃ የነበረበት ነበረ።

በህጋዊ አውታሩ ያለው ለውጥ በተጨማሪም በ 1997 ከነበሩት ምርጫዎች በኋላ ያለው የዋና ተቃዋሚ ኃይላት መነጣጠል ብሎም ደግሞ የመሪ ተቃዋሚ ፓርቲ ሰዎች መታሰር እና የአንድ ተቃዋሚ ፓርቲ መሪ በስደት መሄድ የተጠረቃቀመ አጥባቢ የፖለቲካዊ ስፍራ በሃገሪቱ ውስጥ አስከትሏል። የገዢው ፓርቲ በሃገሪቱ ዙሪያ በተለይም የኢትዮጵያን ህዝብ ብዛት እስከ 80 በመቶ በሚይዘው በገጠራማዎቹ ቦታዎች ያለው ህልውና በተቃዋሚ ፓርቲዎች ለውድድር መቅረብ የማይችል ነበረ።

ኢብምቦ ከተሰጠው ውሱን ጥሪቶች አኳያ ወሳኝ የሆኑ ቴክኒካዊ ተግዳሮቶችን በመርታት ምርጫዎቹን ብቃት ባለው እና መያዊ በሆነ መልኩ አስተዳድሯል። ይሁን እንጂ በድምጽ መስጫ ጣቢያ ሰራተኛ ስልጠና ላይ እና በምርጫ ባለስልጣኑ ቴክኒካዊ መረጃዎች አቀባበል እና ጠቅላላ ድምር ላይ አንዳንድ ጉድለቶች ተስተውለዋል፤ ለምሳሌ የጠቅላላ ሂደቱን ግልጽነት ያበላሸ የተሟላ የድምጽ መስጫ ጣቢያ ዝርዝር አለመኖር። በኢብምቦ አድሏዊ አለመሆን እና ገለልተኝነት ውስጥ አጥጋቢ ያልሆኑ መለኪያዎች የአንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን እምነት ለማሳደግ ተብሎ ተወስደው ነበር።

ኢብምቦ እንደ ገዛ ራሱ እቅድ ከሆነ ከ 37 ሚሊዮን መምረጥ ይችላሉ ብሎ ከገመታቸው ዜጎች ውስጥ 31,926,520 መራጮችን ለ 2002 ዓ.ም ምርጫ ተመዝግበዋል። ይህ የሚያሳየው በአንጻራዊነት ከ 1997 ዓ.ም መራጮች በ 5 ሚሊዮን የሚበልጥ ቁጥር ያላቸውን መራጮች ያካተተ ምዝገባ መሆኑን ነው። የመራጭ ምዝገባ የተካሄደው በስድስት ሳምንታት ሲሆን ይህም በአንጻሩ አጭር ጊዜ ነበረ። የመራጭ ምዝገባ የተከናወነው ከአኅ ምታል መሰማራት በፊት ሲሆን በልዑኩ በቀጥታ ትዝብት ውስጥ አልገባም ነበረ። ማዕከሉን መሰረት ያደረገ እና በኮምፕዩተር የታገዘ ብሔራዊ የመራጭ ምዝገባ አለመኖር ለየትኛውም በርከት ላሉ ምዝገባዎች ማጣራት ወይም የትኛውንም ቁጥጥር ለማድረግ አላስቻለም።

የእጩዎች ምዝገባ በቂ በሆነ ሁኔታ ተከናውኗል። ለእጩዎች የቀረበው መስፈርት የዘር መድልዎ ያልነበረበት ነበረ። ኢብምቦ የፖለቲካ ፓርቲዎች ብሔራዊ ቅንጅት ምክር ቤት ያቀረበውን ጥያቄ ተከትሎ የእጩ ምዝገባ ቀነ ገደብን ለማራዘም በመስማማቱ የሚያስመሰግን ትብብር አሳይቷል። ከፋቱ ለሶማሌ ክልል ተመሳሳይ ነገር አለማድረጉ ነው። ለፖለቲካ ፓርቲ እጩዎች የነበረው የህዝባዊ ገንዘብ ድጋፍ ትውውቅ አዎንታዊ መለኪያ ነበረው፤ ይሁን እንጂ ገንዘቡ የተሳካ የምረጡኝ ቅስቀሳ ለማከናወን በአጠቃላይ የሚበቃ ተደርጎ አይወሰድም።

የምረጡኝ ቅስቀሳ ደንብ መተላለፎችን በተመለከተ ያለው ቅሬታዎች፣ ንዝነዛዎች እና ማስፈራሪያዎች ቁጥር - የደንብ መተላለፍ ጉዳዮችን ጨምሮ - በግንባር ቀደምትነት በተቃዋሚ ፓርቲዎች፣ በአነስተኛ መጠን ደግሞ በገዢው ፓርቲ መሰማቱ በቅስቀሳው የመጨረሻ ሳምንታት ላይ እየጨመረ ሄዶ ነበረ። በአጠቃላዩ የምርጫ ሂደት ግምገማ ውስጥ በገዢው ፓርቲ፣ በማዕከል አስተዳዳሪዎች እና በአንዳንድ ጉዳዮች ደግሞ በፖሊስ ላይ የነበረው የቅሬታዎች መጠን እና ዘለቄታ ከግምት ሊገባ ይገባል። ለሰላማዊ ምርጫዎች የተደጋገመ ጥሪ ከማድረግ ባሻገር ሊከሰቱ የሚችሉ ንዝነዛዎችን፣ እና ማስፈራሪያዎችን ለመገደብ በመንግስት እና በሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች እርምጃ ሊወሰድ ይችል ነበር።

በምርጫ ቅስቀሳው ጊዜ የመሰባሰብ፣ ሃሳብን የመግለጥ እና የእንቅስቃሴዎች ነጻነቶች በጥቅሉ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ሊጎዳ በሚችል መልኩ በመላው ሃገሪቱ በዘላቂነት የተከበረ ነገር አይደለም። ምንምእንኳን አንዳንድ የድጋፍ ስብሰባዎች በዋናነት የተያዙት በኢህአዴግ ቢሆንም ሁሉም ፓርቲዎች ከቤት ቤት እየሄዱ ያደረጉትን ድምጽ የማሰባሰብ ሂደት ወደውታል። የምረጡኝ ቅስቀሳ ተግባራት በጥቅሉ ያተኮሩት የቅስቀሳውን የመጨረሻ ሳምንት ላይ ሲሆን አብዛኞቹን ፓርቲዎች ለገንዘብ እጥረት ዳርጓቸዋል።

ብዙሃን መገኛኛው የዋናውን የቅስቀሳ ክስተቶች በአንፃራዊነት ገለልተኛ በሆነ ቃና ሽፋን ሰጥቶታል። ይሁን እንጂ በመንግስት ባለቤትነት ስር ያለ ብዙሃን መገናኛ ከአጠቃላይ የህትመት እና የስርጭት ብዙሃን መገናኛዎቹ 50 በመቶ የሚሆነውን ሽፋን ለገዢው ፓርቲ በመስጠት ሚዛናዊ ሽፋን ማደላደሉን ሊያረጋግጥ አልቻለም። በተናጥል ለፓርቲዎች እና እጩዎቻቸው የምርጫ ቅስቀሳ የተመደበው የአየር ሰዓት ለተለያዩ እጩዎች ተመጣጥኖ ተከፋፍሏል። ብዙሃን መገናኛው በአተታዎቻቸው ብዙውን ጊዜ ጥንቁቅ እንደነበሩ ተስተውሏል። በቅስቀሳው ጊዜ ውስጥ የአሜሪካ ድምጽ የአማርኛ አገልግሎት መዘጋት እንዲሁም ከምርጫው ቀን ጥቂት ቀናት በፊት የዶቼ ቬሌ መዘጋት መራጮች ሰፋ ካሉ የመረጃ ምንጮች መረጃን ሊቀበሉ የሚችሉበትን ሁኔታ ቀንሶታል። የህትመት እና የስርጭት ብዙሃን መገናኛዎች የነበራቸው የተገደበ ሽፋን ለመራጮች መረጃ ያገኙበትን ምርጫ ያደርጉ ዘንድ የሚረዳ መረጃ የማቅረብ ሚናቸውን በመቀነሳቸው በሌሎች ብዙሃን መገናኛዎች አልተካሰም ነበረ።

በአብዛኞቹ የሃገሪቱ ክፍሎች በማዕከላዊ ደረጃ በገዢው ፓርቲ እና በህዝብ አስተዳደር መካከል የነበረው ልዩነት ደብዛዛ ነበረ። አጎ ምታል በገዢው ፓርቲ የምርጫ ቅስቀሳ ተግባራት ላይ የመንግስትን ጥሪቶች ያለግባብ ጥቅም ላይ የዋሉበትን ጉዳዮች በቀጥታ ታዝቧል። የማዕከል ማህበረሰቦችን ልማት በጥሩ ለመጥቀም የሚውለው የቀበሌዎች (የገጠራማውን ማህበረሰብ ወይም የከተማውን ተጎራባቾች የሚይዝ የአስተዳደር ክፍል) ሚና በምርጫው ሂደት ወቅት እነዚህን ሁኔታዎች እንዳይከሰቱ ለመከላከል ቀስ በቀስ ሊቀነሱ ይገባል። ይህ እንዲሁም ደግሞ በሂደቱ ወቅት የተቃዋሚ ፓርቲዎችን የእምነት መጠን ለመጨመር ይረዳል። ሌላው ቢቀር በሥልጣን ላይ የመሆንን ተፈጥሯዊ ጥቅሞችን ከግምት በማስገባት ለ2002 የነበረው የምርጫዎቹ የመጫወቻ ሜዳ በበርካታ ስፍራዎች ለገዢው ፓርቲ ደግፎ በከፍተኛ ሁኔታ ያደላ በበቂ ሁኔታ ሚዛኑን ጠብቆ ያልተመጣጠነ እንደነበረ ልዑኩ ያስባል።

በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ትዕይንት ውስጥ እና በምርጫው አስተዳደር ስራ ውስጥ ሴቶች በአነስተኛ ሁኔታ ተወክለው ቀርበዋል። ከኢብምቦ በተገኘው መረጃ መሰረት ሴቶች ከተመዘገቡት መራጮች ውስጥ 47.8 በመቶ ያክሉን ይሆናሉ፤ እርሱም ከትክክለኛው የሃገሪቱ ቆጠራ ክብደት ያነሰ ነው። ለ2002 ዓ.ም ምርጫዎች እጩከነበሩት ውስጥ ሴቶች ከ12% እስከ 15% ድረስ ያለውን መጠን ለህተም እና ለክልል ምክር ቤቶች በየአንጻሩ የያዙ ሲሆን ይህም ከ1997 ዓ.ም ምርጫው ያነሰ ነበር። የኢህአዴግ 30% የሚሆነው መጠን ታላቅ የሴቶች መወከልን የሚያረጋግጥ አዎንታዊ እመርታ ነው። ለሴት እጩዎች የነበረው ታላቅ ህዝባዊ የገንዘብ ድጋፍ አቅራቦት የሴቶችን ወክልና የሚያበረታታ መነሳሳት ነበረ።

ኢብምቦ በመራጮች ትምህርት ዙሪያ የተሟላ ብቃት ለመያዝ ወስኖ ነበረ። አጎ ምታል በኢብምቦ ቀርቦ የነበረው የመራጮች መረጃ በአጠቃላይ በቂ ያልነበረ እና በጣም ተደጋግሞ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና አስተዳዳሪዎች በሃገሪቱ ገጠራማ ክልሎች የመራጮች ትምህርት ዋና ተንታኞች ነበሩ። ከአዲሱ እና ገዳቢው የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት እና ማህበራት ህግ ጋር ተያይዞ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች ከመራጮች ትምህርት መከልከል የማዕከል ድርጅቶችን ብቃት ያለው ሚና ከምርጫው ሂደት የገደበ ሆኗል።

ከመምረጥ፣ ቆጠራ እና ድምር ጋር ለተያያዙ ቅሬታዎች ያሉት ደንቦች ከባለፉት አምስት አመታት ይልቅ ፋይዳ ባለው መልኩ ተጠናክሯል። ይሁን እንጂ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የህግ አውጭው እና የፖሊስ ነጻነት እና ገለልተኝነት ላይ ካላቸው የልበ ሙሉነት እጦት አንጻር እነዚህ ደንቦች ከምርጫ ጋር ለተያያዙ ቅሬታዎች የተሳካ ህጋዊ መፍትሄ የሚያቀርቡበትን እድል ያረጋግጡ ዘንድ ተጨማሪ እርምጃዎች መወሰድ እንዳለባቸው አጎ ምታል ያስባል። በተጨማሪም ለቅሬታ ፍርድ አፈጻጸም ያሉት መንገዶች እርምጃ ያልተወሰደባቸውን እነዛን ጥፋቶች ለማስወገድ ሊጣሩ ይገባል።

የምርጫው ቀን ከከፍተኛ የመራጭ ተሰላፊ ጋር በአጠቃላይ ሰላማዊ እና ሥርዓት ባለው መልኩ ተከፍቷል። የምርጫው ሚስጢራዊነት ምንምእንኳን ጥቃቅን የተዛቡ ነገሮች መኖር በስተቀር ተከብሮ ነበረ። አጎ ምታል በተለይ በድምጽ መስጫ ጣቢያዎች መክፈቻ እና መዝጊያ ላይ የሚጸረር የሥርዓቶች አተገባበር ታዝቧል። የፓርቲ ተወካዮች በዋናነት ከኢህአዴግ እና የሃገር ውስጥ ታዛቢዎች በአብዛኞቹ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ ተገኝተው ነበረ። መዝጊያው እና ቆጠራው 66% በሚሆኑ ጉዳዮች በአዎንታዊነት የተገመገሙ ሲሆን የድምጽ አሰጣጥ ስርዓቶች በአጎ ምታል

ታዛቢዎች 87% በሚሆኑት በጎበኟቸው የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች በአዎንታዊነት ተገምግመዋል። ለትዝብት ከበቁት 25% በሚሆኑት ድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ የውጤት ቅጾች ቅጂዎች ለፓርቲ ተወካዮች ያልተሰጡ ሲሆን የቆጠራ ሂደቱን ግልጽነት እና ተዓማኒነት በሚያምታታ መልኩ ወደ አጋማሽ የሚጠጉ ውጤቶች ደግሞ ከድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውጪ አልተለጠፉም ነበር።

በብሔራዊ ደረጃ የድምጽ መስጫ ውጤቶችን ለማጠቃለል ለሚያስችለው ትይዩ የመግባቢያ ዘዴዎች ምስጋና ይግባና ኢብምቦ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ከተዘጉ በኋላ 48 ሰዓታት በሚያንስ ጊዜ ጊዜያዊ ውጤቶችን አስታውቋል። እንደ አጎ ምታል ታዛቢዎች ከሆነ በምርጫ ክልሎች ደረጃ ያለው የማጠቃለል ሂደት በእጅጉ አስቸጋሪ እንደነበረ ይገመታል። ለትዝብት ከበቁት 27% በሚሆኑት ውስጥ የድምጽ መስጫ ውጤቶች ቀደም ሲል በድምጽ መስጫዎች ውስጥ በታዛቢዎች ከታየው የተለዩ ነበሩ። በአያሌ ሁኔታዎች ውስጥ ያልተሟሉ ወይም ትክክለኛ ያልነበሩ ቅጾች ከድምጽ መስጫ ጣቢያዎች ውስጥ በምርጫ ክልሎች የምርጫ ሰራተኞች ሲስተካከሉ ወይም ሲሟሉ ነበር። የሂደቱ ግልጽነት 40% በሚሆኑት ለትዝብት ከበቁ ስፍራዎች ውስጥ አጥጋቢ እንዳልሆነ ይቆጠራል። እንዲህ አይነቶቹ ለትክክለኛ የውጤቶች መሰራጨት የሚሆኑ ወሳኝ ቅጾች ብዙ በሚባሉ የምርጫ ክልሎች ውስጥ አልተሞሉም ነበር።

ለኢህአዴግ ድል ክብረ-በዓልነት ያገለገለውን በምርጫው ላይ ጊዜያዊ የሆነውን መግለጫ ተከትሎ በእጅጉ ተቺ በነበረው የሰብዓዊ መብቶች ተመልካች አተታ ላይ የተወሰኑ ሰልፎች ተካሂደው ነበር። በእነዚህ ሰልፎች ላይ ልዑኩ በገዢው ፓርቲ ላይ “ፖለቲካዊ አጀንዳ” እንዳለው የሚጠቁሙ መፈክሮችን የያዙ ስሌዳዎች በአጎ ምታል ላይ ታይተው ነበር። ኦፊሲያላዊ የሆነ ውጤት ሰኔ 14 ቀን ተለቆ የነበረ ሲሆን በአብዛኞቹ ፓርቲዎች ተቀባይነት አግኝቶ ነበረ። መድረክ እና መኢአድ ውጤቶቹን ያልተቀበሉ ሲሆን ብሔራዊ ክልልን የሚሸፍን የዳግም ምርጫ ጥያቄ ለኢብምቦ ቢያቀርቡም ሊሳካላቸው አልቻለም። ሁለቱም ፓርቲዎች በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት (ፌከፍ) የኢብምቦን ውሳኔ ይግባኝ በማለት አቤቱታ አቅርበው ነበር። ፌከፍ የኢብምቦን ውሳኔ አጽንቶታል።

ገዢው ፓርቲ እና ሸሪክ የሆኑለት ፓርቲዎች ከ547 መቀመጫዎች 544 የሚሆኑትን ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሁም ከ1,904 መቀመጫዎች ደግሞ ከአራቱ በስተቀር ሁሉንም መቀመጫዎች ለክልል ምክር ቤቶች አሸንፏል። የተሳትፎ ተመኑ 93.4% ነው። አንድ የግል እጩ እና ከዋና ተቃዋሚ ቅንጅቶች አንዱ ከሆነው ከኢትዮጵያዊያን ፌደራላዊ አንድነት መድረክ (መድረክ) አንደኛው የሆነው እጩ ለህተም መቀመጫ አሸንፏል። በአንጻራዊነት አነስተኛው ከሚመስለው የአርጎባ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (አህዴድ) አንድ እጩ ሦስተኛውን መቀመጫ አሸንፏል። አህዴድ ሦስት የክልል ምክር ቤቶች መቀመጫዎችን አግኝቷል። የመላው ኢትዮጵያ ውያን አንድነት ፓርቲ (መኢአድ) አንድ የክልል ምክር ቤት መቀመጫ አሸንፏል። ኢህአዴግ በተግባር ፍጹም የሆነውን ቁጥጥር በአነስተኛው የህግ ምክር ቤት እና በክልል ምክር ቤቶች ላይ እንዳደረገ ውጤቶቹ የሚጠቁሙናቸው።

አጠቃላይ የጥቆማዎች እና አስተያየቶች ዝርዝር ተጨማሪ ማሻሻያዎችን በአንዳንድ የምርጫ ሂደት ቦታዎች ላይ ያደርጉ ዘንድ ለሚመለከታቸው ባለስልጣናት ግንዛቤ ሲባል በዚህ የመጨረሻ አተታ ማብቂያ ላይ ተካተዋል። ቁልፍ የሆኑት አስተያየቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡

- የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ተሳትፎ እና ብቃት ለማሳደግ እንዲሁም ደግሞ የፖለቲካዊ ስፍራውን በኢትዮጵያ ለማስፋት አንዳች አይነት እርምጃ መውሰድ አስፈላጊ ነው። የተሰደዱትን ተቃዋሚ መሪዎች መመለስ እንዲሁም የታሰሩትን ተቃዋሚ መሪዎች መፍታት በዲሞክራሲያዊ ሂደቱ ውስጥ ልበ ሙሉነትን የሚያድስ በመሆኑ በዚህ አቅጣጫ ጠቃሚ ደረጃዎች ይሆናሉ። የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የምርጫ ቅስቀሳዎች ለፖለቲካ ፓርቲዎች ከሚደረጉት የአቅም ግንባታ ፕሮግራሞች አፈጻጸም፣ ከአባላቶቻቸው እና ከእጩዎቻቸው ጋር አብሮ የሚታይ ሊሆን ይችላል።
- በገዢው ፓርቲ እና በመንግስት መካከል ግልጽ የሆነ መለያየት መኖሩን ለማረጋገጥ ከዚህም የተነሳ የመንግስትን ጥሪቶች በቅስቀሳዎች ወቅት ያላግባብ ስራ ላይ ማዋል እንዳይኖር ለማድረግ አንዳንድ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው። በምርጫ ተግባራት ውስጥ ላሉ የማዕከል አስተዳደራዊ መዋቅራት እንደ ብቸኛ አማራጭ የሚታዩበትን ሁኔታ በሂደት ለማስቀረት ኢብምቦ በቂ ጥሪቶች ሊዘጋጁለት ይገባል። ይህም ደግሞ ገለልተኛ እና ሊታመን የሚችል የምርጫ ሥራ አመራር አካልን ለመፍጠር ነው። ይህ የሥልጣንን አላግባብ መጠቀም እና የመንግስትን ጥሪቶች በማዕከል ደረጃ መጠቀምን ለማስቀረት የሚረዳ ነው። በተጨማሪም ይህ እርምጃ በምርጫ ሂደቶች ውስጥ የአያሌ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ልበ ሙሉነት ደረጃ ያሻሽለዋል።
- ትክክለኛነቱን እንዲሁም ደግሞ ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች የተመዘገበውን መራጭ ቅጂዎች በማዘጋጀት ታላቅ ግልጽነቱን እንዲረጋገጥ ወሳኝ የሆኑ የመከላከያዎችን ተግባራዊነት እውን ለማድረግ የመራጭ ምዝገባ ለወደፊት የምርጫ ሂደቶች በኮምፒዩተር የታገዘ ሊሆን ይገባዋል። ኢብምቦ ዘላቂ እና ብሔራዊ የሆነ የመራጭ ምዝገባን ስለመፍጠር ሊያስብበት ይችል ይኾናል።
- ኢብምቦ የምርጫ ሂደቶችን ግልጽነት ለማሳደግ እና አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አድሏዊ ባለመሆኑ ላይ ያላቸውን አተያይ ለማሻሻል እርምጃዎችን መውሰድ ይኖርበታል። እነዚህ እርምጃዎች ሁሉንም የምርጫ መረጃዎች ለተቃዋሚ ፓርቲዎች የማሳተምን እና የማስተላለፍን ኃላፊነት ሊያካትቱ ይገባል። ኢብምቦ አንዳንድ የምርጫ ቀን ሥርዓቶችን ሊከልስ ይገባል፣ በተለይ የቅጾችን ንድፍን፣ ለድምፅ መስጫ ጣቢያ ሰራተኛው የሚቀርበውን ሥልጠና ብሎም የምርጫ ክልል የምርጫ አስፈፃሚ መኮንኖች ጭምር ሲሆን እርሱም የማጠቃለል ሂደቱን ለማሻሻል ነው።

## II. መግቢያ

የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ (አኅ ምታል) ከኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከብሔራዊ የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ (ብኢምቦ) የደረሰውን ግብዣ ተከትሎ ከመጋቢት 5 እስከ ሰኔ 14 ቀናት 2002 ዓ.ም ድረስ በኢትዮጵያ ተገኝቶ ነበረ። አኅ ምታል የአውሮጳ ፓርላማ አባል በሆኑት በሚ/ር ቲጅስ በርማን የተመራ ነበረ። ልዑኩ ከ25 የአውሮፓ ኅብረት መንግስታት እንዲሁም ከኖርዌይ፣ ስዊዘርላንድ እና ካናዳ የተውጣጡ 170 ታዛቢዎች የምርጫውን ሂደት ከአለማቀፍ እና ከክልላዊ የምርጫ ግዴታዎች እንዲሁም ከኢትዮጵያ ህግጋት አንጻር እንዲገመግሙ ወደ ሁሉም የሃገሪቱ ክልሎች አሰማርቷል። አኅ ምታል በደረሰባቸው ግኝቶች እና ድምዳሜዎች ገለልተኛ ሲሆን በጥቅምት ወር 1998 ዓ.ም በተባበሩት መንግስታት በተዘጋጀው የዓለም አቀፍ የምርጫ ታዛቢ አዋጅ መርሆች ተገዢ ነው፡ ፡ በምርጫው ቀን አኅ ምታል ታዛቢዎች የምርጫ እና ቆጠራውን ሁኔታ ለመታዘብ 815 የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን እያንዳንዱን የኢትዮጵያ ክልሎች ጎብኝተዋል።

## III. ፖለቲካዊ ዳራ

ሀ. ፖለቲካዊ አውድ

የመድብለ ፓርቲ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት በኢትዮጵያ ፌደራል ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት መካተት የጀመረው በታህሳስ 1987 ዓ.ም. ጀምሮ ሲሆን ይህም የጸደቀው ከ1983 ዓ.ም የደርግ አገዛዝ ውድቀት በኋላ በተመረጡት የህገ መንግስት አርቃቂዎች ስብሰባ ነው። ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ተከታታይ ምርጫዎች በየአምስት አመቱ ይደረጋሉ። በግንቦት 15/2002 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ዜጎች የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትን (ህ.ተ.አ.) እንዲሁም የክልል አስተዳደር መማክርትን ባሉት የሃገሪቱ ክልሎች ሁሉ እንዲመርጡ ጥሪ ተደርጎላቸዋል። የክልል ምክር ቤት ምርጫዎች በድሬዳዋና በአዲስ አበባ መስተዳድሮች የተከናወነው በ2001/2002 ዓ.ም. ሲሆን ይህም የሆነው በ1997 ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያሸነፉትን መቀመጫ አንረከብም ካሉ በኋላ መሆኑ ይታወቃል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስከ 2002 ዓ.ም ድረስም መቀመጫዎቹ በተቃዋሚ ፓርቲ አልተያዙም።

የ 2002 ምርጫ ልዩ መታወቂያው በምርጫ 1997 ትዝታዎችና ክስተቶች የተከበበ የነበረ መሆኑ ነው። ግንቦት 1997 በአገሪቱ ታሪክ ውስጥ ልዩ እና ታላቅ የሆነ ፉክክር የነገሰበት ምርጫ በኢትዮጵያ ውስጥ ተደረገ። በምርጫው ቀን የተፈጠሩ መዛባቶች እንዲሁም በመጠናከር ሂደት ውስጥ የተፈጠረው ተቃውሞ ወደ አመጽ እና ነውጥ ተለውጦ ወደ 200 የሚደርሱ ሰዎች ለህልፈት ተዳርገዋል። ረዘም ያለ ጊዜ የወሰደውና አቤቱታ የበዛበት የምርጫ ማጣራት ሂደትም ተከናውኖ በሌላም በኩል በአንዳንድ ስፍራዎች ዳግም ምርጫ ተካሂዶ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ (ኢ.ብ.ም.ቦ) በመስከረም 1998 ዓ.ም. የመጨረሻውን የምርጫ ውጤት ይፋ አድርጓል። በዚህም መሰረት ተቃዋሚዎች ከ547 የተወካዮች ምክር ቤት መቀመጫዎች ውስጥ 170ውን ሲያሸንፉ በአዲስ አበባ ምክር ቤት ደግሞ ከ138 መቀመጫዎች 137ቱን አሸንፈዋል። በሌላም በኩል ዋንኛው የተቃዋሚ ፓርቲ ምርጫው ተጭበርብሯል በሚል ፓርላማ ባለመግባት እንዲሁም ለአንዳንድ የሲቪል ግዴታዎች ባለመገዛት የተቃውሞ ጥሪ አድርጓል። በህዳር 1998 ጥቂት የማይባሉ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች፣ የሰብአዊ መብት አቀንቃኞች፣ ጋዜጠኞች እና በሺህ የሚቆጠሩ ሲቭል ማህበረሰቦች ለእስር ተዳርገዋል። በታህሳስ 1998 137 ግለሰቦች በከፍተኛ ወንጀል ሲከሰሱ "ህገ መንግስቱን በሃይል ለመናድ" ተንቀሳቅሰዋል በሚል ነበር። አብዛኞዎቹ ከ18 ወራት በኋላ ይቅርታ ተደርጎላቸው ከእስር ተለቀዋል።

ከዚህ ምርጫ በኋላ የፈነዳው አመጽ በብዙ ኢትዮጵያውያን አዕምሮ ውስጥ ተቀርጾ ቀርቷል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በሁሉም ተፎካካሪ ፓርቲዎች እና በባለሃብቶች በ2010 አመጽ አልባ እና ሰላማዊ የምርጫ ሂደት ዋናና ተፈላጊ ነበር። ለብዙ ባለድርሻ አካላት የ 2002 ምርጫ ከ1997 ሲነጻጸር ሰላማዊነቱ ሂደቱን ይገመግሙ ዘንድ ወሳኝ ነበር።

የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ደንብ ስነ ምግባር (ፖ.ፓ.ም.ደ.ስ) ፊርማ መካሄዱ በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ አውድ ላይ እመርታን ያሳየበት ሁኔታ ነው። የፖለቲካ ምርጫ ደንብ ስነ ምግባር የተፈረመው ጥቅምት 20, 2002 ሲሆን ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ መሪዎች (ኢ.ዴ.ፓ.)፣ አንድነት ለዲሞክራሲ ፓርቲ (አ.ዲ.ፓ.)፣ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት እና ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (መ.ኢ.አ.ዴ.ፓ) የተሳተፉ ሲሆን አብዛኞዎቹ ሌሎች ፓርቲዎችም ኋላ ላይ ፈርመዋል። በጥር 2002 ዓ.ም. ደንቡ ህግ ሆኖ ተካተተ። ህግ ሆኖ አስገዳጅ ባህሪ መያዙ በተወሰነ መልኩ አስቀድሞ የነበረውን የጋራ ስምምነት መንፈሱን አዳከመው።

ለ. አውራ የፖለቲካ ተዋናዮች

በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከተመዘገቡት 79 የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ 63ቱ በ2002 ምርጫ በብሔራዊ ወይም በክልል ደረጃ ለመወዳደር ቢወስኑም አምስት ፓርቲዎች ብቻ ለአገር አቀፍ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልነት በቂ የሆኑ እጩዎች አቅርበዋል። የአብዛኞቹን የፖለቲካ ፓርቲዎች ፋይናንስ አቅማቸውንም በመመልከት የአኅ ምታል ታዛቢዎች ከኢ.ህ.ዴ.ግ በስተቀር አብዛኛዎቹ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች ያልተደራጁ፣ ልምድ አልባ፣ በቂ ፈንድ የሌላቸው በተለይም በአደረጃጀት ውስጣዊ ዲስፕሊን የሚጎላቸው ናቸው ብሏል። የአብዛኛዎቹ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ከመነሻው ጀምሮ ከፉኛ የተመናመኑ ሲሆን በተለይም ደግሞ ወደ 80 በመቶ የሚቆጠር መራጭ ህዝብ ባለበት የገጠሩ ክፍል ያይላል።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ አውድማ ከ 1983 ደርግ መንግስት ውድቀት በኋላ በህዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራቲክ ግንባር (ኢህአዴግ) ተጽእኖ ስር የወደቀ ሲሆን በነሐሴ 1981 የተመሰረተው ኢህአዴግ በስሩ አራት ድርጅቶችን[1] እንዲሁም በቀረው የአገሪቱ ክፍሎች ውስጥ በዛ ያሉ ተባባሪ እና አጋር ፓርቲዎችን ያቅፋል። ኢህአዴግ በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የሚመራ ሲሆን ሰብሳቢውም በአሁኑ ጊዜ ያሉት ጠቅላይ ሚንስትር መለስ ዜናዊ ናቸው። ኢህአዴግ በመጠን፣ በአደረጃጀት፣ በፓርቲ ዲስፕሊን መዋቅሩን በሁሉም የአገሪቱ ቀበሌዎች (ማህበረሰቡንና የከተማውን መንደሮች ሁሉ አስተዳዳሪ ክፍል ያለው) የዘረጋ ብቸኛ እና እውነተኛ ብሔራዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ነው። ኢህአዴግ እና አጋር ድርጅቶቹ በ 1987 ምርጫ ከ 547 መቀመጫዎች 492 መቀመጫ ያሸነፉ ሲሆን ከ 1992 ምርጫ በኋላ ወደ 482 ከዚያም ከ 1997 ጠንካራ ፉክክር በኋላ ወደ 377 መቀመጫ ወርዷል። ኢህአዴግ በሚያዚያ 2000 ዓ.ም በተካሄደው የአካባቢ ምርጫ በከፍተኛ ልዩነት ያሸነፈ ሲሆን በ 2002 ምርጫ ጊዜም ኢህአዴግ ለተወካዮች ምክር ቤት 501 እጩዎችን ለክልል ምክር ቤት ደግሞ 1,349 እጩዎችን አቅርቧል።

ከ 1997 ምርጫ በኋላ በዋንኛ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ የተከሰተው ከአባልነት መልቀቅ፣ መከፋፈልን ተከትሎ ከሉሎች ጋር መዋሃድ እንዲሁም የአዳዲስ ፓርቲዎች ብቅ ብቅ ማለት ሃይላቸውን አዳከመው። ተቃዋሚዎች በተጨማሪም የአንዱ መሪያቸው መሰደድ በተለይም ለውይይት የማኢፈቅደው ነውጠኛ አተያያቸው እንዲሁም የዋና ዋናዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች መሪዎች በእስር ቤት መወርወራቸው መዳከማቸውን አፋጥኖታል። ከ 1997 የቅንጅት ለአንድነት ፓርቲ ውህደት በኋላ የአንድነት ለዲሞክራሲ ፓርቲ እና የኢትዮጵያ ዲሞክራሲ ሃይሎች አዲስ ፓርቲ መስርተዋል። በሌላም በኩል ወጣ ብለው የሚታዩ ሌሎች ፓርቲዎች በ 2002 ምርጫ በግል ሲንቀሳቀሱ ነበር።

ለመንግስት ጠንካራ ተቃዋሚ ፓርቲ የነበረው የኢትዮጵያ ፌደራል ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፎረም (መድረክ) ሲሆን ይህ ፓርቲ የስምንት ፖለቲካዊ ፓርቲዎች ውህድ ነው። አብዛኞቹም ፓርቲዎችም ከቅንጅት ለአንድነት እና የህብረት ፓርቲዎች ጋር የተገኛኘ ነገር ያላቸው ሲሆኑ ሰብሳቢው የኢትዮጵያ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢህዴፓ)[2]፣ ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስን አድርገው ሾመዋቸዋል። መድረክ በንጽጽር ሲታይ በሰኔ 2000 ዓ.ም. የተመሰረተ በመስከረም 2002 ደግሞ በብሄራዊ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ቦርድ ኢትዮጵያ የተመዘገበ አዲስ ተቃዋሚ ሃይል ነው። መድረክ ብርቱ ህልውናውን በክልሎች ሁሉ ለመመስረት እንዲሁም ተቀናጅቶ ለመስራት ከባባድ ውጣ ውረዶችን አሳልፏል። ሆኖም በመስከረም 2002 በተዘጋጀው የምርጫ ደንብና ስነ ምግባር ውይይትና ስምምነት ላይ ስብሰባውን ረግጦ የወጣ ሲሆን ኢህአዴግ በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ለመነ ጋገር ፈቃደኛ እንዳልሆነ ያነሳል። መድረክ ምንምእንኳ የምርጫ ደንብና ስነ-ምግባር ለፖለቲካ ፓርቲዎች የተባለውን ሰነድ ባይፈርምም መስራች ፓርቲዎቹ ግን በደንብና ስነ ምግባሩ መሰረት እንደሚንቀሳቀሱ አመልክተዋል። መድረክ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 487 ለክልል ምክር ቤት ምርጫ ደግሞ 861 እጩዎችን አቅርቧል።

በሰኔ 2000 የቀድሞው የቅንጅት ለአንድነት ፓርቲ ምክትል ሰብሳቢ፣ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የአዲሱ አንድነት ለዲሞክራሲ እና ፍትህ ፓርቲ ዋና ሰብሳቢ ሆነው ተመረጡ። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ በ 1997 ዓ.ም. የተያዙ ሲሆን ህገ መንግስቱን በሃይል ለመናድ በሚል የእድሜልክ እስራት ተበይኖባቸዋል። በ 2000 ዓ.ም. በፈጸሙት ድርጊት በመጸጸት ዳግመኛ ወደዚያ አይነት ነውጠኛ ተግባር እንደማይሳተፉ ያስታወቁና የፈረሙቢሆንም በውጪ አገር የይቅርታውን ቅድመ ሁኔታ በመጣሳቸው ለእስር ሊዳረጉ ችለዋል። በርግጥ የይቅርታው ህጋዊነት አነጋጋሪ መሆኑ አልቀረም።[3] የተባበሩት መንግስታት የሰራተኞች ቡድን እስሩ ድንገተኛ እንደሆነ ይናገራሉ። ስለሆነም ኤንጂኒየር ግዛቸው ሽፈራው በቅርብ በተደረገው ምርጫ የአመራሩን ስፍራ ተረክበዋል። ቅንጅት ለአንድነት ፓርቲ ህጋዊ የበላይነቱን ካጣ በኋላ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ፓርቲ (መኢአፓ) በአቶ ሃይሉ ሻውል አማካኝነት ተመስርቷል። መኢአፓ ኋላ ላይ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ኢትዮጵያ ሰነድ ላይ መፈረሙ በተቃዋሚዎች አስተችቶታል። ቆየት ብሎም መኢአፓ የኢህአዴግ ሌሎች ፓርቲዎች ላይ የሚያደርገው የቁጥጥር መንገድ እንደሳዘነው አስታውቋል። መኢአፓ ለተወካዮች ምክር ቤት 319 ለክልል ምክር ቤቶች ምርጫ ደግሞ 619 እጩዎችን አቅርቧል። በ 2002 ከነበሩት ሌሎች ሁነኛ ተወዳዳሪ ፓርቲዎች መካከል በአቶ ልደቱ አያሌው የሚመራው የኢዴፓ ፓርቲ መንግስቱን በመተቸቱ ሂደት ውስጥ ተለሳልሶ ቀርቧል። ፓርቲው ለተወካዮች ምክር ቤት 230 እጩዎችን ለክልል ምክር ቤት ደግሞ 280 እጩዎችን አቅርቧል። ከቀድሞው ፓርቲ ጋር የፍርድ ቤት ትግል ከተደረገ በኋላ አቶ አየለ ጫሚሶ የቅንጅት ለአንድነት ፓርቲ ስም ወራሽነት ተስጥቶአቸዋል። እናም ይህ ፓርቲ 133 ለተወካዮች ምክር ቤት 137 ደግሞ ለክልል ምክር ቤት እጩዎችን አቅርቧል። በ 2002 ቀሪዎቹ ፓርቲዎች ያቀረቡት እጩዎች በንጽጽር እና በቁጥር ሲታይ አነስተኛ ሲሆኑ የህዝብንም

---

[1] የትግራይ ህዝቦች ነጻነት ግንባር (ትህነግ)፣ የአማራ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (አብዴን)፣ የኦሮሞ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) እና የደቡብ ኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ደኢዴን) ናቸው። ሸሪክ ፓሪቲዎቹ የሚያካትተው፡ የአፋር ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (አብዴፓ)፣ የሶማሌ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ሶህዴፓ)፣ የቤንሻንጉል-ጉመዝ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ቤጉህዴፓ)፣ የጋምቤላ ህዝቦች አንድነት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ጋህአዴን) እና የሐረር ብሔራዊ ሊግ (ሐብሊ) ናቸው።

[2] የውህደቱ ሌሎቹ ፓርቲዎች፡ አንድነት ለዴሞክራሲ እና ፍትህ (አዴፍ)፣ የኦሮማ ፌደራሊስት ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኦፌዴን)፣ የትግራዊያን አንድነት ለዴሞክራሲ እና ሉዓላዊነት (ትአዴሉ)፣ የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ አንድነት (ደኢህዴአ)፣ የኦሮሞ ህዝቦች ኮንግረስ (ኦህኮ)፣ የኢትዮጵያዊያን ዴሞክራሲያዊ አንድነት ንቅናቄ (ኢዴአን) እና የሶማሌ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ኃይላት (ሶዴአኃ) ናቸው።

[3] እንደ የቅጣት አዋጅ 395/1996 አንቀጽ 16 ከሆነ ይቅርታው በእነዚህ ሁለት ጉዳዮች ብቻ ሊሻር ይችላል 1) በቂ ምክኒያት ከይቅርታው በፊት የተገኘ እና በይቅርታ አድራጊው ተቀባይነት ሲኖረው ወይም 2) ይቅርታው በማጭበርበር ወይም በማታለል ምክንያቶች የተሰጠ ወይም ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ ነው። እንደ መንግስት ከሆነ ይቅርታው የተሰጠው በማጭበርበር እና በማታለል ምክኒያቶች አይደለም። የይቅርታው መሻር ይቅርታ መጠየቋን በመካዷ ብቻ ነው። ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ እና የህግ ጠበቃዎቿ ይቅርታውን መካድ ለይቅርታዋ መሻር ከህግ አንጻር አሳማኝ ምክኒያት እንዳልሆነ እና መከላከያዋንም ለማቅረብ እድል እንዳልተሰጣት ይናገራሉ። የይቅርታ አዋጁ ይቅርታን የሚያሽር ጉዳይ ሲኖር ሰጪው ቀደም ተብሎ የሚደርሰው የጽሁፍ ማሳሰቢያ ሊኖረው እና ምላሹንም በ 20 ማሳሰቢያውን በተቀበለበት ቀናት ምላሽ መስጠት ይኖርበታል በማለት በግልጽ ያስቀምጣል።

ድምጽ ለማግኘት ብዙ የታደሉ አልነበሩም። በአጠቃላይ ወደ 34 የሚያህሉ የግል እጩ ተወዳዳሪዎች ቀርበው ለፓርላማ ሲወዳደሩ 11 ደግሞ ለክልል ምክር ቤቶች ተወዳድረዋል።

## IV. ህጋዊነቱ እና የምርጫው አውታር

*ሀ. ህጋዊው አውታር*

በተወካዮች ምክር ቤት እና በክልል ምክር ቤት ምርጫዎች ገዢ የሆነው ህጋዊ ቅርጽ ለእውነተኛ እና ዴሞክራሲያዊ ምርጫዎች ገዢ የሆነው ህጋዊ ቅርጽ ለእውነተኛ እና ዴሞክራሲያዊ ምርጫዎች ከዓለም ዓቀፋዊ ሆነ ከክልሎች ጠንካራ ተሳትፎ ጋር ስምም የሆነ በቂ መሰረትን የሚሰጥ ነው። የኢትዮጵያ ህገ መንግስት እና ከምርጫ ነክ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ያለው ህግ የፖለቲካ መብት ዋስትናን ሲሰጥ እንዲሁም መሰረታዊ ነጻነቶችን ማለትም የመሰብሰብ፣ የመንቀሳቀስና የመደራጀት መብትን ያስጠብቃል። በሚደረጉት ወቅታዊ ምርጫዎች አጠቃላይ የመምረጥና የመመረጥ መብት እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለመምረጥ የሚስጥር ድምጽ አሰጣጥ በህገ መንግስቱ የተካተቱ ሲሆን ፍትሃዊ እና ህጋዊ ማስተካከያዎችን የማግኘት መብት ተገቢ የሆነ የፍርድ ሂደትንም ይጨምራል። ሆኖም ምርጫውን አስመልክቶ በህጎች ደንቦችና መመሪያዎች አፈጻጸም ላይ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ከተቀመጡት መርሆች ውጪ ነገሮች ሲያፈነግጡ ተስተውሏል። ይህ ደግሞ በምርጫው ሂደት እና በተቀመጡት መርሆች እና ስምምነቶች ላይ ጫናን የፈጠረ ሲሆን በተለይም በመሰረታዊ የሲቪል እና የፖለቲካዊ መብቶች ላይ ሊኖር የሚችለውን ደስታ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳርፎበታል።

የተወካዮች ምክር ቤትም ይሁን የክልል ምክር ቤት ምርጫዎች የሚመሩት በ 1987 በፌደራል ዴሞክራሲያዊ ኢትዮጵያ ህገ መንግስትና በሌሎች ልልዩ አዋጆች ማለትም በተሻሻለው የምርጫ ህግ (532/2007)፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ (573/2008) የምርጫ ደንብና ስነ ምግባር ለፖለቲካ ፓርቲዎች (662/2009)፣ ሰላማዊ ሰልፎችንና ህዝባዊ ስብሰባዎችን በተመለከተ ያለውን ቅደም ተከተል በሚያስቀምጠው አዋጅ (3/1991)፣ የበጎ አድራጎት ማህበራት አዋጅ(621/2009)፣ የጸረ ሽብርተኝነት ህግ (652/2009) የብዙሃን መገናኛ እና መረጃ የማግኘት አዋጅ (590/2008) እንዲሁም የ 1997 የወንጀለኛ መቅጫ ህግን መሰረት አድርጎ ነው። ሌሎች በዛ ያሉ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የወጡ መመሪያዎችና ደንቦች አሉ። እነርሱም የእጩዎች ምዝገባ መመሪያ (1/2009)፣ የመራጮች መመሪያ (2/2009)፣ የመምረጥና የመመረጥ፣ ድምጽን የመቁጠርና የምርጫን ውጤት የማሳወቅ መመሪያዎች (5/2010)፣ መንግስት ፖለቲካ ፓርቲዎችን በፋይናንስ ለመደጎም ያለው ድርሻና ቅደም ተከተል ደንብ (5/2009)፣ በቦርዱ በያንዳንዱ የምርጫ ደረጃ አጣሪ ኮሚቴ የማቋቋም ደንብና (1/2009) እና የመገናኛ ብዙሃን እንዲሁም የጋዜጠኞች ምርጫውን ሪፖርት ማድረጊያ አቀራረብ እና የስነ ምግባር ደንብ 6/2010 ናቸው።

*ለ. አለማቀፍ እና ክልላዊ ግዴታዎች*

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት ሁሉንም አብይ የሆኑትን የምርጫዎች አፈጻጸም አለማቀፋዊ እና ክልላዊ ግዴታዎችን ስምምነት ገብቷል። አብዛኛው በቀጥታ ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የ 1966 አለማቀፋዊ ቃልኪዳን በሲቪል እና ፖለቲካዊ መብቶች (አቃሲፓመ)፣ የ 1979 በሴቶች ላይ የሚደረጉ ሁሉንም አይነት መድሎዎች የማስወገድ ስምምነት (ሴሁመማስ)፣ የ 1966 ሁሉንም አይነት የዘር መድሎዎችን የማስወገድ አለማቀፍ ስምምነት (ሁአዘመማአስ)፣ የ 1952 የሴቶች ፖለቲካዊ መብት ስምምነት (ሴፖመስ)፣ የ 1981 የሰብዓዊያን እና የህዝቦች መብቶች የአፍሪካ ቻርተር (ሰህመቻ)፣ እና በሴቶች መብቶች ላይ የተፈራረመው ፕሮቶኮል ናቸው። በተጨማሪም ኢትዮጵያ ለ 2002ቱ በአፍሪካ ዴሞክራሲያዊ ምርጫዎችን በተመለከተ ገዢ የሆኑ መርኾዎች የአፍሪካ ህብረት አዋጅ ላይ ፖለቲካዊ ግዴታ አላት። እንዲሁም አሁን ድረስ በስራ ላይ ያልዋለውን በዴሞክራሲ፣ በምርጫዎች እና አገዛዝ ላይ የ 2007 የአፍሪካ ቻርተርን አጽድቃለች።

*ሐ. የምርጫ ህግጋት*

አብዛኞቹ የ 2002 ዓ.ም ምርጫን የገዙ ህግጋት እና ደንቦች ከ 1997 ዓ.ም የተወሰዱ ናቸው። ስለዚህ እነዚህ በዚህ አዲስ ማዕቀፍ ውስጥ የተያዙ የመጀመሪያ አጠቃላይ ምርጫዎች ናቸው። አዲሱ ደንብ እንዲህ አይነቶቹን አዎንታዊ ለውጦች አስተዋውቋል። ለምሳሌ በየድምጽ መስጫ ጣቢያው የሚገኙ የተመዘገቡ መራጮችን ወደ 1,000 መገደብ እና ለፓርቲ ወኪሎችኦፊሲያላዊ የውጤት መግለጫ ወረቀቶችን ቅጂ መላክ ናቸው። ከምርጫ ጋር ተዛማጅ የሆኑ አምባጓሮዎችን ለማርገብ የአዳዲስ አሰራሮች፣ አካላት እና ቀነ ገደቦች ፈጠራ መኖሩ ሌላኛው ወሳኝ ፈጠራ ነው። ሆኖም ግን በእኩል መብት ስለ መመረጥ እና በእኩልነት ስለ መምረጥ የተቀመጡት የደንቦች ተግባራዊ አፈጻጸሞች ከሌሎች መካከል በዚህ አተታ ውስጥ ቀለም ተቀብተዋል፤ ያለበቂነት ታይተዋል።

በባለፉት ጥቂት አመታት ውስጥ የተወሰዱ አንዳንድ ህጋዊ ሠነዶች በዋናነት የብዙሃን መገናኛ ህግ፣ የበጎ አድራጎት እና ማህበራት አዋጅ እና የጸረ-አሸባሪነት ህግጋት ሰላማዊ ምርጫዎችን ለማካሄድ የሚቻልበትን አቅም ለማሳደግ የታለሙ ህጎች መስለው ይታያሉ። ምንም እንኳን ለምሳሌ የጸረ-አሸባሪነት ህጉ በምርጫው ሂደት ወቅት ተግባራዊ ባይደረግም እነዚህ ህጋዊ ሠነዶች ውጤታማ የሆኑ መሰረታዊ ነፃነቶችን በመለማመድ ረገድ ካላቸው ተጽዕኖ አኳያ ኮስታራ የሆኑ ጉዳዮችን ያስነሳሉ። እነዚህ ህጎች የሚመለከታቸው ብሔራዊ ገለልተኛ ፓርቲዎች

በሂደቱ እንዳይሳተፉ አድርገው ቀንሰዋቸዋል። ይህ በዋናነት የምርጫውን ግልጽነት ሂደት የማረጋገጥ ሚና ሊጫወቱ የሚገባቸው የብዙሃን መገናኛ እና የመያዶች ጉዳይ ነበር።

የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር ህግ ትግበራ (ፖፓምሥህ) የፈረመበት ቢሆንም ባይሆንም የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥምር ጉባዔ (ፖፓጥጉ) አባልነትን ከማይጨምረው የሥነ-ምግባር ህጉን ፈራሚዎች ከሚገድበው ሁኔታ ጋር ሁሉንም የፖለቲካ ፓርቲዎች ያሰረ ሆኗል። በተጨማሪም በተባሉት ነገሮች ላይ እና ከምርጫ ጋር ተዛማጅ በሆኑ ጥፋቶች ላይ በሚበይነው በህግ ተርጓሚው፣ በኢብምቦ መዋቅራት እና በፖፓጥጉ የተከፋፈለው ሥልጣን ህጋዊ መፍትሄ ለማስገኘት ተገቢው መንገድ ነው በመባሉ ግራ መጋባትን ፈጥሯል።

*መ. የምርጫው ሥርዓት*

ሥልጣንን በማዕከላዊ መንግስት እና ክልላዊ መንግስታት መጋራት ባለበት ከሃገሪቱ የፌደራል ሥርዓት አኳያ የኢትዮጵያዊያን አጠቃላይ ምርጫዎች በተለመደ መልኩ የፓርላማ ታችኛው ምክር ቤት፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ህተም)፣ እና የዘጠኙን የክልል ምክር ቤቶች ብሎም የሁለቱን የከተማ አስተዳደሮች ያጣመረ ነው።[4] የሃገሪቱ የላይኛው ምክር ቤት፣ የፌደሬሽን ምክር ቤት በሚመለከታቸው የክልል ምክር ቤቶች ከህዝብ ብዛቱ አከፋፈል አንጻር የሚመረጡ በሃገሪቱ ህዝቦች ብሔሮች እና ብሔረሰቦች ተወካዮች የተወከሉ ጥምረቶች ናቸው።

እንደ ህገ መንግስቱ ከሆነ የህተም ምንም አንኳን በአተገባበር 547 ቁጥርን የያዘ ቢሆንም እስከ 550 መቀመጫዎች ሊኖሩት ይችላል። አብላጫ ድምጽ በማግኘት የሚደረግ ምርጫ ሥርዓት ጥቅም ላይ የሚውለው ከተናጥል አባል የምርጫ ክልሎች የሚገኝ ቀጥተኛ፣ ዝነኛ እና ሚስጢራዊ በሆነ የምርጫ መብት ሲሆን እርሱም የህተም አባላትን ለአምስት አመት ቆይታ ለመምረጥ ነው። ምንም እንኳን የምርጫ ህጉ ለክልላዊ መንግስት ምክር ቤቶች ምርጫዎች ግልጽ የሆነ ሥርዓት ባያስቀምጥም በተግባር ግን ቀላል የሆነ የአብላጫ ድምጽ ሥርዓት የሚከተሉ ነገር ግን ከብዙሃ-አባላት የምርጫ ክልሎች ጋር ያሉ ናቸው። መራጮች ተመሳሳይ ቁጥር ያለው ምርጫዎችን በምርጫ ክልላቸው ባለው መቀመጫ ልክ የሚከቱ ሲሆን በምርጫ ክልላቸው ከትልቁ የመራጭ መጠን ጋር ያሉ እጩዎች ደግሞ ለክልል ምክር ቤቶች መቀመጫዎችን ያገኛሉ። የኢብምቦ በእያንዳንዱ የምርጫ ክልል ያለውን የመቀመጫ ብዛት ክልላዊ ህግጋቶችን መሰረት አድርጎ ይወስናል። በሃገሪቱ ዙሪያ ያሉ የክልል ምክር ቤቶችን መዋቅር በግልጽ የሚያሰባስቡ ህዝባዊ ሠነዶች ቢኖሩ ኖሮ የሂደቱ ግልጽነት ይሻሻል ነበር። በእጅጉ ግልጽ በሚሆኑ የአብላጫ ድምጽ ሥርዓቶች ውስጥ እንዳለው ሁሉ የምርጫ ቱሩፋቶች በሃገሪቱ የሚገኙ የፖለቲካዊ አማራጮችን ስብጥር የሚወክሉ አይደለም።

*ሠ. የምርጫ ክልሎች ወሰን*

የሃገሪቱ ወቅታዊ 547 የምርጫ ክልሎች ወሰን በ1988/9 መጀመሪያ ላይ ከተመሰረተ በኋላ ተከልሶ አያውቅም። የህገ መንግስቱ አንቀጽ 103 የኢብምቦ በየአስር አመቱ በብሔራዊ የቆጠራ ኮሚሽን የሚደረገውን ቆጠራ መሰረት አድርጎ ፕሮፖዛል ለህተም እንዲያቀርብ ይጠይቃል። ምንም እንኳን አንዳንድ ቀበሌዎች በማዕከል ድምጽ አሰጣጥ በአስተዳደራዊነታቸው ለተለያዩ አውራጃዎች የተጣመሩ ለመሆን የመረጡ ቢሆኑም ቁጥራቸው ግን በአንጻራዊነት ያን ያክል ወሳኝ አይደለም። በባለፉት 15 ዓመታት ከነበሩት የውልደት እና ሞት ቁጥር ለውጦች አንጻር በምርጫ ክልሉ ያሉ መራጮች ቁጥር በአሁኑ ሰዓት በወሳኝነት ይለያል። በውጤቱም በየምርጫ ክልሉ ያሉ ብሔራዊ የመራጮች አማካኝ ቁጥር ወደ 53,500 የሚጠጋ ሲሆን በየምርጫ ክልሉ ያሉ አማካኝ ግምታዊ የመራጮች ቁጥር ከ40,000 ጀምሮ በቤንሻንጉል ጉመዝ እስከ 130,000 በአፋር ክልል ይለያያል። ይህ የምርጫ አውታር ባህሪ ከዚህ የተነሳ ሁሉም መራጮች እኩል ሊሆኑ የሚገባበትን "እያንዳንዱ መራጭ እኩል ክብደት ሊኖረው ይገባል" በማለት ከሚገልጸው የምርጫ ህጉ አንቀጽ 26.3 እና ከአለማቀፋዊው የሲቪል እና የፖለቲካዊ መብቶች ቃልኪዳን (አሲፓመቃ) ድንጋጌ አንጻር መስፈርቱን ለማሟላት የሚጎድለው ይሆናል።[5]

*ረ. "ልዩ" የአነስተኛ ቁጥር ያላቸው የምርጫ ክልሎች*

በህገ መንግስቱ እና በምርጫ ህጉ በተደነገጉት መርኾዎች አንጻር 22 መቀመጫዎች በህተም በነገድ አነስተኛ ለሆኑ ህዝቦች የተጠበቀ ነው። ከዚህ የተነሳ 22 "ልዩ" የአነስተኛ ቁጥር ያላቸው ምርጫ ክልሎች አሉ። በአንዳንድ ክልሎች ለአነስተኛ ቁጥር ላላቸው የነገድ ቡድኖች የተደረገው ማስተካከያ የተለያዩ መጠን ያላቸው መቀመጫዎች ለአነስተኞቹ በሚጠበቅላቸው በምክር ቤቶች ምርጫዎች ላይም ተግባራዊ ይሆናል። የምርጫ ህጉ "የ [ልዩ አነስተኞቹ] ዝርዝር የምርጫ ክልሎቹ የሚወሰኑት እና ለህዝብ ይፋ የሚደረጉት [ብሔራዊ አስመራጩ] ቦርድ አጥንቶ ለፌደሬሽን ምክር ቤት ገቢ በሚያደርግ ጊዜ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው።" የእነዚህ የምርጫ ክልሎች ዝርዝር መረጃ በህግ የሚወሰን እንደሚሆን ህገ መንግስቱ ይደነግጋል። የልዩ ምርጫ ክልሎች ድልድል የምርጫ ክልሎች በ1988 በተወሰኑ

---

[4] የሃገሪቱ ዘጠኙ ክልሎች፡ አፋር፣ አማራ፣ ቤንሻንጉል-ጉመዝ፣ ጋምቤላ፣ ሃረሪ፣ አሮሚያ፣ ሶማሌ፣ የደቡብ ሕዝቦች ብሔሮችና ብሔረሰቦች ህዝቦች ክልል (ደህብብህክ) እና ትግራይ ናቸው። ሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች ድሬዳዋ እና አዲስ አበባ ናቸው።

[5] የአሲፓመቃ አንቀጽ 25፤ የተባበሩት መንግስታት ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን፣ አጠቃላይ መግለጫው ቁጥር 25፤ አንቀጽ 21፤ "በእያንዳንዱ ክልል የምርጫ ሥርዓት አውታር ውስጥ የአንድ መራጭ ድምጽ ከሌላው እኩል ነው። የምርጫ ወሰኖች አሰማመር እና መራጮችን የመመደብ ስልቱ የመራጮችን ስርጭት ሊያዛባ ወይም በየትኛውም ቡድን ላይ መድልዎ ሊያደርግ አይገባም" የሚለውን መርኽ ያስምርበታል።

በዛው አይነት ተመሳሳይ ጊዜ ላይ ተከናውኗል። የኢብምቦ ጥናት ከአኅ ምታል ጋር የጋራ ነበረ፤ ነገር ግን ልዑኩ ምንም አይነት በፌደሬሽን ምክር ቤት ተከትሎ የመጣውን ውሳኔ ሊያገኝ አልቻለም። ግልጽ የሆነ ፣ የተሰባሰበ ህጋዊ ወይም ሥርዓታዊ ማመሳከሪያ አለመኖሩ አተገባበሩ ሊገመገም የሚችልበትን መጠን ገድቦታል ደግሞም የምርጫውን ሂደት ግልጽነት አበላሽቶታል።

በተመሳሳይ መልኩ የልዩ ምርጫ ክልል ምርጫዎች አተገባበር ይልቁንም ውስብስብ ነበረ። ለምሳሌ በሃረሪ ልዩ የምርጫ ክልል ድምጽ መስጠት ሲከናወን የነበረው በሃረሪ እና በ 12 አዲስ አበባ ውስጥ ባሉ የድምጽ መስጫጣቢያዎች እና በሃገሪቱ ባሉ ሌሎች ከተሞችም ጭምር ነበረ። ከእነዚህ የድምጽ መስጫጣቢያዎች የተገኙት ድምጾች በኢብምቦ ዋናው መስሪያ ቤት የልዩ ምርጫ ክልሎች ላይ ይጨምሩ ነበረ። የድምጾችን ታላቅ እኩልነት ለማረጋገጥ አስፈላጊ የሆነው የምርጫ ክልሎች ወሰን ክለሳ የልዩ ምርጫ ክልሎችን ወሰንንም፣ እንዲሁም አስፈላጊነታቸውን እና አግባብነታቸውንም ሊከልስ ይገባል። ወደ 80 የጎሳ ቡድኖች በሚገኙበት ሃገር የልዩ ምርጫ ክልል ሥርዓቱ ከትክክለኛው የውልደት፣ ጋብቻ እና ሞት ቆጠራ መሰረት አንጻር የታረቀ ሊሆን ይገባዋል።

## V. የምርጫ አስተዳደር

### *ሀ. የምርጫ አስተዳደር መዋቅር እና ቅንጅት*

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ (ኢብምቦ) የተመሰረተው በ 1986/7 በአዋጅ ቁጥር 641/1986 የነበረ ሲሆን እርሱም ሁሉንም በሃገሪቱ ያሉትን ምርጫዎች እና የመገንጠል ምርጫዎች ለማስተዳደር ኃላፊነት እንዳለው ገለልተኛ እና ራሱን ችሎ በነጻነት የሚተዳደር አካል ሆኖ ነው። ተልዕኮው በህገ መንግስቱ አንቀጽ 103 እና በምርጫ ህጉ ላይ የተቀመጠ ሲሆን ለሁሉም አይነት የምርጫ ሂደቶች ሥነ -ምግባር የህግ፣ የሥርዓተ ደንብ እና የአፈጻጸም አውታር መመስረትን ያካትታል። ኢብምቦ የምርጫ ውጤቶችን ሊያቃውስ ወይም በምርጫው ሂደት ውስጥ በጥቅሉ መዛባትን ሊፈጥር የሚችል ነገር ካገኘ የምርጫ ውጤቶችን ሊሽር እና ዳግም ምርጫዎችን ሊያዝ ይችላል።

አብዛኞቹ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የኢብምቦን ገለልተኛነት በተደጋጋሚ ጠይቀዋል። በማዕከል ደረጃ በአንዳንድ ጉዳዮች ውስጥ በምርጫ መኮንኖች፣ በመንግስት እና በገዢው ፓርቲ ታዋቂ ሰዎች ተግባራት እና አመለካከት ላይ አስቸጋሪ የሚሆን መደራረብ ነበረ። በጥቅሉ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ኢብምቦ ላይ ታዩ የሚሏቸው አድልዎ ነገሮች ሊገመገሙ የሚገባቸው በአጠቃላይ የህዝባዊ አካላትን ካለማመን እንደሆነ ተደርገው ነው። ሆኖም ግን ኢብምቦ ግልጽነትን እና እንዲያሳይ እና ተቃዋሚ ፓርቲዎች በስራው ላይ ያላቸውን እይታ እንዲያሻሽል ለህዝብ እና ለፖለቲካ ፓርቲዎች የተሻለ መያዊ መረጃ ማቅረብ መቻሉን ሊያረጋግጥ ይገባል። እንዲህ አይነቱ መረጃ የተሟላ እና ወጥነት ያለው የምርጫ ክልሎች፣ የድምጽ መስጫዎች እና የተመዘገቡ መራጮችን ዝርዝር ሊያካትት ይገባል።

ኢብምቦ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰጠውን አስተያየት ተከትሎ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ህተም) በተሾሙ ዘጠኝ አባላት ባሉት ቦርድ ይመራል። አዲስ ቦርድ በ 2000/1 የተሾመ ሲሆን ግዙፍ ቁጥር ያለውን የሰራተኞቹን መተካትን ያካተተ የመልሶ ማዋቀር ፕሮግራም አስጀምሯል። በአሁኑ ሰዓት የቦርዱ አንደኛው አባል በተመሳሳይ ሁኔታ በኢብምቦ ውሳኔዎች ላይ ለሚቀርቡት አቤቱታዎች ፍጹሙ ወሳኝ አካል በሆነው በፌደራል ዋና ፍርድ ቤት ውስጥ ፕሬዘደንት መሆኑ የሚያስቆጭ ነው። ኢብምቦ ቦርዱን እና በዋና መስሪያ ቤት ያለውን ጽህፈት ቤት ጨምሮ፣ 11 ቋሚ የክልል ቢሮዎች፣ ወደ 43 የሚሆኑ የዞን ቅርንጫፎች፣ 547 ጊዜያዊ የምርጫ ክልል የምርጫ ቢሮዎች እና ወደ 43,5000 የሚሆኑ ድምጽ መስጫጣቢያዎች ያሉት ባለ አምስት ተዋረድ መዋቅር ያለው ነው።

በብሔራዊ ደረጃ ያለው ኢብምቦ ለአኅ ምታል በእጅጉ ተባባሪ የነበረ ሲሆን ከፍተኛ ደረጃ ያለው መያተኝነትን አሳይቷል። በአብዛኞቹ ሁኔታዎች ይህ ትብብር በሃገሪቱ ዙሪያ ባሉ በክልላዊ እና በምርጫ ክልሎች የምርጫ ቢሮዎችም ጭምር ቀጥሎ ነበረ።

### *ለ. የምርጫዎች አስተዳደር*

ኢብምቦ የምርጫ ዝግጅቶች ወሳኝ የሆኑ ቴክኒካዊ ተግዳሮቶችን በጥሩ ጊዜ ላይ በመጀመር እና ከተሰጠው ጥሪቶች አኳያ የሚያስደምም ድርጅታዊ ብቃቶችን በማሳየት በእጅጉ ተቆጣጥሮታል። ስኬታማ የነበረው እና ወቅቱን የጠበቀው የድምጽ መስጫ ቁሳቁሶች በመላው ሃገሪቱ መሰራጨት አንደኛው እንዲህ አይነቱ ስኬት ነው። ሆኖም ግን በቂ የሆኑ የደንነት መቀናጀቶች ብዙ ጊዜ ይጎድሉ የነበረ ሲሆን እንዳለመታደል ሆኖ ቁሳቁሶችን ለማስቀመጥ የነበረው ብቸኛው የተገኘው ስፍራ ብዙ ጊዜ በገዢው ፓርቲ ቁጥጥር ስር እንዳሉ የሚታሰቡት እና በእርግጥም የነበሩት የማዕከል የአስተዳደር ቢሮዎች ነበሩ።

የምርጫ ክልሎች የምርጫ ቢሮዎች በጥቅሉ ብቃት ያላቸው ነበሩ። ሆኖም ግን አብዛኞቹ የምርጫ መኮንኖች በመንግስት ቅጥረኞች የተሞሉ መሆኑ ገለልተኛ ላለመሆን በነበራቸው ፈቃደኝነት እና ችሎታ የአንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን እምነት የማጣት ደረጃ ሊያሻሽለው አልቻለም። በተጨማሪም በእጅጉ ወጥ እና ስኬታማ ግንኙነት በምርጫ ክልል ቢሮዎች እና በኢብምቦ ዋና መስሪያ ቤት መካከል የነበረ ይመስል የነበረ ሲሆን እርሱም አሁን ላሉት ክልላዊ ቢሮዎች እጅግ ተስማሚ አጠቃቀም ፈጥሮ እንደሆነ ጥያቄን የሚያስነሳ ነው።

ባለ አምስት አባላት የድምጽ መስጫጣቢያ ኮሚቴዎች ሥራቸውን በይፋ የጀመሩት ታህሳስ 30 ቀን 2002 ዓ.ም የመራጮች ምዝገባ ማካሄድ ሲጀምሩ ነው። የድምጽ መስጫጣቢያ ሰራተኞች በአብዛኛው የሚመረጡት በየምርጫክልላቸው ቢሮዎች ነበር። ቀድሞም ያለው የምርጫ መስፈርት ቢኖርም በአመራረጥ ሂደቱ ላይ የግልጽነት ጉድለት ነበረ። እርሱም የተቃዋሚ ፓርቲዎች በድምጽ መስጫጣቢያ ሰራተኞች ገለልተኝነት ላይ ያላቸውን እምነት ማጣት ያሳደገ ነበረ። ይሁን እንጂ አኅ ምታል አያሌዎቹ የድምጽ መስጫጣቢያ ሰራተኞች ለትዝብት በበቁት የድምጽ መስጫጣቢያዎች ውስጥ በምርጫው ቀን እድሎ የሌለባቸው ነበሩ።

ሁሉም የምርጫ መኮንኖች በሁለት ዙር የ "የአነስተኛ ፏፏቴ" ዘዴን ተከትሎ የሰለጡኑ ነበሩ። የመጀመሪያው ያተኮረው በመራጭ ምዝገባ እና ሁለተኛው ደግሞ በትክክለኛው የምርጫ ቀን ሥርዓቶች ላይ ነበረ። በኢብምቦ ዋና መስሪያ ቤት የነበረው ሥልጠና ከፍተኛ ጥራት የነበረው ሲሆን በአኅ ምታል ለትዝብት የበቃው ለድምጽ መስጫጣቢያ ሰራተኞች የተሰጠው የሥልጠና ደረጃ ከቆይታ እና ከአሰጣጥ ዘዴው አንጻር ተፃራሪ እና በአመዛኙም በቂ ያልነበረ ነበር።

*ሐ. የደምጽ መስጫጣቢያዎች*

ቁጥራቸው ከጨመሩት ተመዝጋ መራጮች እና ከአዲሱ በእያንዳንዱ የድምጽ መስጫጣቢያ የ 1,000 መራጮች ገደብ አኳያ የድምጽ መስጫጣቢያዎች አጠቃላይ ቁጥር በ 1997 ዓ.ም ከ 33,000 በ 2002 በነበረው ምርጫ ወደ 43,500 በታላቅነት አድጓል። ተቃዋሚ ፓርቲዎች ለሁሉም የሃገሪቱ ክልሎች የድምጽ መስጫጣቢያዎች ግልጽ በሆነ እና ሊጨበጥ በሚችል የሠነድ ዝርዝር ላልቀረበው ለዚህ ቁጥር መጨመር እምነት ማጣት እንዳላቸው ገልጸዋል። ምንም እንኳን ኢብምቦ ለአኅ ምታል በሃገሪቱ ያሉትን የተመዘገበውን የድምጽ መስጫጣቢያዎች ዝርዝር ቢያቀርብም እነዚህ በተደጋጋሚ ያልተሟሉ ወይም በምርጫክልል የምርጫቢሮዎቹ ዘንድ ወጥነት ያልነበራቸው ነበሩ። ምንም አይነት ትክክለኛ እና የተሟላ የድምጽ መስጫጣቢያ ዝርዝር ወይም ስሌት ለምርጫ ሂደቱ ከሚጠየቀው ግልጽነት በተቃራኒ ለታዛቢዎችም ሆነ ለፖለቲካ ፓርቲዎች አልቀረበም ነበር። አያሌ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ግዙፍ ቁጥር ባላቸው የምርጫጣቢያዎች በቂ የሆኑ የፓርቲ ተወካዮችን መመልመል እንደማይችሉ ቅሬታ አቅርበዋል። ከዚህ አኳያ የኢብምቦ የፓርቲ ተወካዮች ምዝገባ ቀነ ገደብን ለማራዘም የነበረው ፈቃደኝነት ተቀባይነት የነበረው ውሳኔ ነበር።

*መ. የህዝብ ታዛቢዎች*

የ "ህዝብ ተወካዮች" ሚና ከአካሄድ ችግሮች ጋር ብቻ የነበረ ሲሆን ከአያሌ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አለመታመንን የሚጠብቅ ነበረ። የህዝብ ታዛቢዎች በቂ ባልነበረ ሁኔታ ውጤታማ እና አድልዎ ለሌለበት የተግባራቸው አፈጻጸም ታጥቀው እንደነበረ እና በሂደቱ ውስጥ ለግልጽነቱ ወይም ለልበ ሙሉነቱ አስተዋፅዖ እንዳላደረጉ የአኅ ምታል ይገምታል።

የህዝብ ታዛቢዎች ለመታዘብ እና አስፈላጊም ከሆነ የመራጭ እና የእጩ ምዝገባ፣ የቁሳቁስ ስርጭት፣ የድምጽ አሰጣጥ፣ ቆጠራ እና ማጠቃለልን ጨምሮ በተወሰኑ የምርጫው ሂደቶች ላይ አስተያየት መስጠት ወይም ጣልቃ እንዲገቡ አደራ የተጣለባቸው የማህበረሰቡ አባላት ናቸው። ለእያንዳንዱ ድምጽ መስጫጣቢያ አምስት ህዝባዊ ታዛቢዎች እንዲሁም ለእያንዳንዱ የምርጫ ክልል ቢሮዎች ደግሞ ሦስት ታዛቢዎች አሉ። ሁለት የሚሆኑ የህዝብ ታዛቢዎች በድምጽ መስጫጣቢያዎች፣ በክልል እና በክልል የምርጫቢሮዎች የቅሬታ ሰሚ ለመሆን አንደኛው ክፍል በመሆን ኮሚቴ መስርተዋል።

ህዝባዊ ታዛቢዎችን[6] ለመምረጥ የተኬደው አካሄዶች እንዴት እንደሆነ ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ሊገለጽላቸው የሚገባ መሆኑን ይጠይቃል። ነገር ግን ይህ እንዳልሆነ በስፋት የሚነገሩ አተታዎች ነበሩ። ይህ ደግሞ በበቂ ሁኔታ ያልተወገደውን ስለ ህዝብ ታዛቢዎች ገለልተኛነት ያለውን ጥርጣሬ የሚያቀጣጥል ነበረ። ምንም እንኳን የህዝብ ታዛቢዎች ሥልጠና ወስደው የነበረ ቢሆንም፣ በርከት ያለው ጣልቃ የመግባት ሥልጣናቸው ለተሰጣቸው ሥልጠና እና የብቃት ደረጃቸው ልክ በተሰጠበየትኛውም ግልጽ ሊባል በሚችል ትኩረት የተደገፈ አልነበረም።

*ሠ. የመራጭ ትምህርት*

የኢብምቦ የተሰጠው ኃላፊነት የመራጮችን ትምህርት በቀጥታም ሆነ በሌሎች ድርጅቶች በኩል መስጠትን ያካትታል። ለ 2002ቱ ምርጫ ቦርዱ በዚህ አቅጣጫ የተሟላ ብቃት ከመያዝ ታቅቧል። ቦርዱ ቁሳቁሶችን አዘጋጅቶ ወደ ክልላዊ እና የቀጠና ቢሮዎች፣ እንዲሁም በብዙሃን መገናኛ፣ ድራማ እና ተለጣፊ ማስታወቂያዎች በኩል አሰራጭቷል። ይሁን እንጂ ቀበሌ አስተዳደሮች ለህዝቡ ግንባር ቀደም የመረጃ ምንጭ ሆነው ተገኝተዋል። ይህም ደግሞ ስለ ገለልተኛነታቸው ይህ ነው ሊባል የሚችል ጥርጣሬን የሚያመጣ አስቸጋሪ ነገር ነው። ከምርጫው ቀን ቀደም ብሎ ባለው የሣምንቱ ማብቂያ ላይ በደካማ ሁኔታ የተላለፈ ብሔራዊ ስፋት ያለው የመራጭ ትምህርት ተካሂዶ ነበረ። ይህ ደግሞ

---

[6] አንቀጽ 9 እና 11፣ የህዝብ ታዛቢዎችን፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮችን እና እጩዎችን ተግባራትን በተመለከተ የተቀመጡ መምሪያዎች ናቸው፤ መምሪያ 3/2009። በድምጽ መስጫጣቢያው ዋና የምርጫ መኮንን በተጠራው ስብሰባ ላይ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎችን ማስታወቅ ከተካሄደ በኋላ አግባብ በሚሆነው የድምጽ መስጫጣቢያ ሊመዘገቡ በሚገባቸው ዜጎች እጅ ማውጣት (በግልጽ ያልተለየ) የ 10 እጩዎች መታጩት ተካሂዷል። አምስቱ ብዙ ደጋፊ የነበራቸው ተመልማዮች ተመርጠዋል። የቀሩት አምስቱ ደግሞ እንደ ተጠባባቂ እንዲቀመጡ ተደርገዋል። በክልል የምርጫጣቢያ ደረጃ ያሉ የህዝብ ታዛቢዎች በክልል የምርጫጣቢያው ተመረጠው በነበሩት በእነዛ ሰዎች ሁሉ አማካኝነት ተመርጠዋል።

ከምርጫው ቀደም ብሎ ባለው በመጨረሻው የሣምንቱ ማብቂያ ላይ ሁሉም ፖለቲካዊ ቅስቀሳዎች በእነዛ ቀናት የተከለከሉ በመሆናቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ሊኖራቸው የሚችለውን ቅስቀሳ በተሳካ ሁኔታ ገድቦታል። ምንም እንኳን በምርጫው ቀን አያሌ መራጭ በረድፍ ቢገኝም ለ 2002 የነበረው የመራጮች ትምህርት ስኬታማነት የሚታወስ ነው፤ ሂደቱን በተመለከተ ያለው የዜጎች መረዳትም ጎዶሎ ሆኖ ተገኝቷል። ከፍተኛ ያልተማረ ቁጥር እና አነስተኛ የትምህርት ደረጃዎች በሚገኙበት ሃገር ነፃ እና መረጃ የተገኘበትን ምርጫ የማግኘቱ የመራጮች እድል ሚዛናዊ መረጃ ሊያገኙ በሚችሉበት እድል ልክ የተገደበ ነበረ።

## VI. የመራጭ ምዝገባ

### *ሀ. የመምረጥ መብት*

የመምረጥ መብት በህገ-መንግስቱ እና በምርጫ ህጉ ላይ የጸና ነው። የብቃት መስፈርቶች ከዓለማቀፍ የምርጫ መብት መርኆዎች ጋር አብሮ የሚሄድ ሲሆን የመድልዎ ገደቦችን ከአለማቀፍ እና ክልላዊ ግዴታዎች አንጻር አያካትትም። ከ 18 ዓመት በላይ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች ላለፉት ስድስት ወራት በኖሩበት ለምርጫው የመመዝገብ መብት አላቸው። የእስር ፍርድ የተጣለባቸው ዜጎች አይመዘገቡም። መመዝገብ በሚሹበት የድምጽ መስጫ ጣቢያ ዜጎች አንዳች አይነት ማንነታቸውን የሚገልጽ ነገር ሊኖራቸው ይገባል አሊያም ማንነታቸው በምርጫ መኮንኖች፣ የህዝብ ታዛቢዎች ወይም ጥንታዊ በሆነ መንገድ ሊረጋገጥ ይገባል። የተመዘገቡ ዜጎች የግል ምንነታቸውን ዝርዝር ያካተተ የመራጭ ካርድ ይሰጣቸዋል፤ ነገር ግን ፎቶግራፎቻቸውን አያካትትም።

በኢትዮጵያዊያን የህግ እና የምርጫ አካሄድ ማዕቀፍ ውስጥ በውጭ ሃገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን የመምረጥ መብት እንዲኖር የሚያመቻች አቅራቦት የለም። ለእነዚህ ኢትዮጵያዊያን ግልጽ የሆነ መራጭነትን የሚፈጥር ነገር ከሃገር ውጪ ከሚገኝ ምዝገባ በኢምባሲዎች እና ቆንፅላዎች ለወደፊት ምርጫዎች ሊታሰቡ ይችላሉ። ህገ መንግስቱ 550 መቀመጫዎችን በህተም ወስኖ እያለ በአሁኑ ሰዓት ግን ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት 547 የምርጫ ክልሎች ናቸው። የቀሩት ሦስቱ መቀመጫዎች በውጪ ሃገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንን ለመወከል ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።

### *ለ. የመራጭ ምዝገባ[7]*

የመራጭ ምዝገባ አካሄዶች ምንም አንኳን የመራጭ ምዝገባን ትክክለኛነት እና ተዓማኒነት ላረጋገጥ ያልበቁ ቢሆኑም በአንጻራዊነት ግን እንደ አስፈላጊነቱ ሊለዋወጡ የሚችሉ እና አጠቃላይ ነበሩ። አዲስ የመራጭ ምዝገባ ልምምድ ለእያንዳንዱ የምርጫ ዑደት ተካሂዷል። ለ 2002ቱ ምርጫ የመራጭ ምዝገባ ብዙም ሳይቆይ ቢጀመርም ከሶማሌ በስተቀር በሃገር አቀፍ ደረጃ ከጥር 1 ቀን እስከ የካቲት 10 2002 ድረስ ተካሂዷል። እንደ ኢብምቦ ከሆነ 31,926,520 መራጮች በ 2002 ሲመዘገቡ ከእነዚህም ውስጥ 15,252,240ዎቹ ሴቶች ነበሩ። በ 1997 ለነበረው ምርጫ ከተመዘገቡት 25,600,000 ገደማ ከሚሆኑት መራጮች ጋር ሲተያይ ከ 5 ሚሊዮን በላይ ብልጫ ነበረው። በኢትዮጵያ ውስጥ ካለው የ 80 ሚሊዮን ገደማ ህዝብ ብዛት መካከል የኢብምቦ እቅድ 37 ሚሊዮን ሰዎች ለመምረጥ ይመዘገቡ ዘንድ ብቃት እንዳላቸው ነበረ።

እንደዚህ አይነት ግዙፍ እና የተበታተነ ህዝብ ብዛት ላላት ሃገር የመራጭ ምዝገባ ጊዜ በአንጻራዊነት አጭር ነበረ። ምንም እንኳን ቅሬታዎች ወይም ማስተካከያዎች እንዲኖሩ ለማስቻል የመራጭ ምዝገባዎችን በማዕከል አካባቢ የማሳየት ሁኔታ ቢኖርም ይህም ደግሞ እንዲሁ አጭር ነበረ (አምስት ቀናት) ብሎም ደግሞ የምዝገባ ማገባደጃን የቀደመ ነበረ። ይህም ማለት ጊዜያዊ እትሙ ብቻ ነበር የታየው ማለት ነበረ። ረዘም ያለ የምዝገባ ጊዜ እና ቋሚ የሆነ ብሔራዊ የምርጫ ምዝገባ ለወደፊት ምርጫዎች ሊታሰቡ ይገባል።

ምንም አይነት ብሔራዊ የመራጭ ዝርዝር ተሰባስቦ አያውቅም። በእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር በምርጫ ክልል ቢሮዎች ደረጃ ተጠቃሏል። ከዚያም በኋላ ቁጥሩ ብሔራዊ ማጠቃለያ ወደሚያገኝበት ይደመሩ ዘንድ ወደ ኢብምቦ ዋና መስሪያ ቤት ተልከው ነበረ። ብሔራዊ ድምሩ በእያንዳንዱ የምርጫ ክልል የተመዘገቡትን አጠቃላይ የወንዶች እና ሴቶች ብዛት ያስቀምጣል። ነገር ግን ምንም አይነት የማመሳከሪያ ማጣራቶችንም ወይም የመከላከያ ተግባራትን የሚፈቅድ አይደለም። ለምሳሌ አያሌ ምዝገባዎችን ማጣራት የማይቻል ነበረ። ለሁሉም ክልሎች ወጥነት የሌላቸው ድምሮች ተፈጥረው ነበረ። በተለይም ከመራጮች ምዝገባ መዝጊያ በኋላ ድምሩ ሊረጋገጥ በሚገባው ጊዜ። ግልጽ፣ ወጥ እና የተብራራ ድምር በእያንዳንዱ የምርጫ ክልል ያልተሰባሰበበት እና ያልተሰራጨበት ስኬት አልባነት የሂደቱን ግልጽነት እና ተዓማኒነት አበላሽቶታል።

ተደጋግሞ የሚደረግ ምዝገባዎች እና ቀደም ሲል ከሚገኙ የመራጭ ስርዓቶች አኳያ የዓላማ መከላከያ አለመኖሩ ሊከሰት የሚችሉ የማጭበርበር መከራዎችን ለማስቀረት በቂ አይሆንም። ምንም እንኳን በድምጽ መስጫ ጣቢያው ከሚገኘው የመራጮች ዝርዝር ውስጥ ተመዝግበው ሳይገኙ ለምርጫ መቅረብ ክልክል ቢሆንም ማንነት በግል እስከተረጋገጠ ድረስ (በድምጽ መስጫ ጣቢያው ኮሚቴ አባል፣ በህዝብ ታዛቢ ወይም በሌላ የተወከለ ሰው) ያለ መራጭ ካርድ መምረጥ ይቻላል። ይህም ደግሞ የሚጠየቀው ብቸኛው የማንነት መለያ ማረጋገጫ ነው። ከዚህ አኳያ ሊከሰት ከሚችለው ተደጋጋሚ መራጭነት ብቸኛው መከላከያ በመራጮች ጣት ላይ የማይለቅ ቀለም መቀባት እና በማዕከሉ

[7] የመራጭ ምዝገባ የተካሄደው አጎ ምታል በሃገሪቱ ውስጥ ከመሰማራቱ ቀደም ብሎ ሲሆን ከዚህም የተነሳ በልዑኩ በቀጥታ ለትዝብት ሊበቃ አልቻለም።

መኮንኖች አድልዎ የሌለበት የአፈጻጸሞች አተገባበር ላይ ያላቸው መተማመን ነበር።

የምርጫ ህጉ ለከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና ለአንዳንድ ወታደራዊ ሰራተኞች መመዝገብን እና በሚኖሩበት እና በሚሰሩበት አካባቢ እንደየ መገኛቸው የምርጫ ክልል መራጭነታቸው የሚወከላቸውን መምረጣቸውን የሚፈቅድ ነው። እንደ ኢብምቦ ከሆነ የመራጭነት ምዝገባ በ111 ኮሌጆች እና ወታደራዊ ካምፖች ውስጥ በሃገሪቱ ዙሪያ ሁሉ ሲካሄድ ይህም ከሃገሪቱ መራጮች 231,269 ያክሉን ይዟል። ኢብምቦ በእያንዳንዱ ተቋም ውስጥ ባሉት የምርጫ ክልሎች በመቶዎች የሚቆጠሩ አያሌ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች እደላ እና መልሶ ማግኘት ውስጥ ያለውን የአሰራር ይህ ነው ተብሎ ሊገለጽ የሚችለውን ተግዳሮት ተወጥቶታል። በተጨማሪም ይህ አሰራር የተማሪዎች እና ወታደራዊ ሰራተኞች ድምጽ በኢብምቦ ዋና መስሪያ ቤት ውስጥ ለሚመለከታቸው የምርጫ ክልሎች ብቻ የሚደመሩ በመሆኑ የሂደቱን አጠቃላይ ውጤቶች ግልጽነት ቀንሶታል። ከዚህም ሌላ እነዚህ ድምጾች ለተናጥል የምርጫ ክልሎች በአጠቃላይ ውጤቱ ላይ ለውጥ የሚያመጡ ከሆነ ብቻ ይፋ ሆነው ለህትመት የሚበቁ ነበሩ። በተጨማሪም ለብሔራዊ ደህንነት በሚል ምክኒያት ኢብምቦ በወታደራዊ ሰፈሮች ውስጥ ያሉትን የድምጽ መስጫጣቢያዎች ውጤቶች ይፋ ሊያደርገው አልቻለም። በነጻነት ሊጎበኝ እና ለትዝብት ሊበቃ በማይችል ስፍራ ውስጥ ድምጽ መስጠት ሊካሄድ ይችላል ወይስ አይችልም ከሚለው ጥያቄ አንጻር ዝርዝር ውጤት ሊወጣ አልቻለም።

## VII. የእጩዎች እና ፖለቲካ ፓርቲዎች ምርጫ

### *ሀ. የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ*

ለፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ ኃላፊነት ያለበት ኢብምቦ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ የተቀመጡት ህጋዊ ደንቦች ከአለማቀፍ እና ክልላዊ የማህበራት ነጻነት[8] ግዴታዎች አንጻር ተቀባይነት ሊኖረው የሚችል ምክኒያታዊ የሆኑ ናቸው። አኅ ምታል የትኛውም አይነት ይህ ነው ተብሎ የሚገለጽ የሚያሳስቡ ጉዳዮች ስለ ፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ መረጃ አልደረሰውም። የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ የፓርቲ ምዝገባን ይወስናል፣ ደግሞም ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን በሙሉ ፖለቲካ ፓርቲ እንዲመሰርቱ እና አባል እንዲሆኑ ይደነግጋል። ጥላቻ እና ጠላትነትን በህዝቦች መካከል የሚሰብኩ፣ መንግስትን በኃይል ለመገልበጥ የሚሞክሩ፣ ወይም በአመጽ የፖለቲካ ለውጥ የሚሹ ድርጅቶች እንደ ፖለቲካ ፓርቲ ለመመዝገብ ይታገዳሉ። ምዝገባ ላይ ያለው ውሳኔ በፌደራል ዋና ፍርድ ቤት ሊጠየቅ ይችላል።

### *ለ. የእጩዎች ምዝገባ*

ለህተምም ሆነ ለክልል ምክር ቤቶች ምርጫዎች እጩሆኖ ለመመዝገብ አብይ የሆኑ መድልዎ ያለባቸው አሊያም በበቂ ምክኒያት ያልተደገፉ መስፈርቶች የሉም። ለሁለቱም አካላት እጩ የሚሆኑት በምዝገባ ወቅት ቢያንስ 21 ዓመት የሞላቸው፣ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች የሆኑ እና እጩ በሚሆኑበት ክልላዊ መንግስት ያለውን የሥራ ቋንቋ የሚያውቁ መሆን አለባቸው። እጩዎች ለምርጫ ክልሉ ቢያንስ ለሁለት አመታት ነዋሪ የሆኑ ወይም እዚያ የተወለዱ መሆናቸው በተጨማሪነትም የሚጠየቅ ነገር ነው። ፖለቲካዊ መብታቸው የተከለከለባቸው ግለሰቦች፣ የእስር ቤት ፍርድ የተጣለባቸው ወይም የአእምሮ ህመም አሊያም እብደት እንዳለባቸው የተመሰከረባቸው እንደ እጩ ሆነው ለመመዝገብ አይበቁም። ገለልተኛ እጩዎችም ቢሆኑ በተጨማሪነት ቢያንስ 1,000 የድጋፍ ፊርማ ማሰባሰብ አለባቸው። የመንግስት ሰራተኞች እጩዎች እንዲሆኑ ይፈቅዳል ህጉ ይፈቅዳል። በአንጻሩ ደግሞ ዳኞች፣ ወታደሮች እና የፖሊስ መኮንኖች ከተመደቡበት ሥራ እንዲለቁ ይጠይቃል።[9]

ሆኖም ግን የምርጫ ህጉ በእያንዳንዱ የምርጫ ክልል ሊኖሩ የሚችሉትን የእጩዎች የመጨረሻ ቁጥር ወደ 12 ገድቦታል።[10] ከ12 በላይ ቢኖሩ ቅድሚያ የሚሰጠው በፖለቲካ ፓርቲዎች ታቅፈው ለሚቀርቡት ነው። ገለልተኛ እጩዎች ከዚህ የተነሳ ተጎጂዎች ናቸው። በተጨማሪም የፖለቲካ ቅስቀሳ ለማድረግ ከህዝብ ሊገኝ የሚችለው የገንዘብ ድጋፍ ገለልተኛ እጩዎችን አያካትትም። ዜጎች በፖለቲካ ፓርቲ መድረክ ስር ወይም እንደ ገለልተኛ እጩዎች ሆነው

---

[8] ከአይሲሲፒአር፣ ዩናይትድ ኔሽንስ ሂዩማን ራይትስ ኮሚሽን፣ አንቀጾች 22 እና 25 አጠቃላይ አስተያየት ቁጥር 25 አንቀጽ 26 አኳያ፡ “የመደራጀት እና ድርጅቶችን የማጣመር መብትን እና ፖለቲካዊ እና ህዝባዊ ጉዳዮች የሚመለከታቸው ማህበራትን ጨምሮ የማህበራት ነጻነት መብት በአንቀጽ 25 ላይ በተጠበቀው መብቶች ላይ በመሰረታዊነት የተካተተ ነው።” እንዲሁም ደግሞ የኤሲኤችፒአር አንቀጽ 10ን እና የአፍሪካ ህብረት በአፍሪካ ዲሞክራሲያዊ ምርጫን የሚያስተዳድሩ መርኆዎች IV. ላይ ያወጣውን አዋጅ ይመልከቱ:: ምርጫዎች፡ መብቶች እና ግዴታዎች፣ አንቀጽ 5፡ “እያንዳንዱ ዜጋ ከህግ አንጻር የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ድርጅት የመመስረት እና አባል የመሆን ነጻነት ሊኖረው ይገባል።”

[9] ከአይሲሲሰፒአር አንቀጽ 2 እና 3 አኳያ፣ ከአይሲኢአርዲ አንቀጽ 5 አኳያ እና ከሲኢዲኤደብልዩ አንቀጽ 4 እና 7 አኳያ። የአይሲሲፒአር፣ ከተባበሩት መንግስታት ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን፣ አንቀጽ 15 ላይ ከሚገኘው አጠቃላይ አስተያየት ቁጥር 25 አንጻር “የትኛውም ለመመረጥ በመነሳት መብት ላይ ያሉ እንደ አነስተኛ እድሜ ያሉ ገደቦች ከአላማ እና አሳማኝ መስፈርት አንጻር ተገቢ ሊሆኑ ይገባል። አለበለዚያ ደግሞ ለምርጫ ለመነሳት ብቁ የሚሆኑ ሰዎች ምክኒያታዊ ባልሆነ ወይም መድልዎ ባለበት እንደ ትምህርት፣ ነዋሪነት ወይም ዘር አሊያም በፖለቲካዊ ዝምድና አይነት ባሉ መስፈርቶች ምክኒያት ሊነፈጉ አይገባም።” እና በአንቀጽ 16 መሰረት ደግሞ “ከምልመላ ቀናት፣ ክፍያ ወይም ተቀማጭ ክፍያዎች አኳያ ያሉት ሁኔታዎች አሳማኝ እና መድልዎ የሌለባቸው ሊሆኑ ይገባል።” በተጨማሪም የአፍሪካ ህብረት በአፍሪካ ዲሞክራሲያዊ ምርጫን የሚያስተዳድሩ መርኆዎች 2002 ያወጣውን አዋጅ ይመልከቱ።

[10] የተሻሻለው የምርጫ ህግ አንቀጽ 49፣ አዋጽ 532/2007

ቢንቀሳቀሱም ለሁሉም ዜጎች የመመረጥ እኩል መብት እንዲከበር እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው።

እጩዎች በምርጫው ሂደት ወቅት ለኮስታራ ጥፋቶች በፍላግራንት ደሊክቶ ጉዳዮች ካልሆነ በቀር በቁጥጥር ሥር ከመዋል ነጻ መውጣታቸው አስደስቷቸዋል። በሁሉም በሌሎች ሁኔታዎች እጩዎች ከውጤቶች ይፋ መሆን በኋላ ብቻ ተከሰው ህግ ፊት ይቀርቡ ይሆናል። የተመረጡ እጩዎች የከእስር ነጻ የመሆናቸው ጊዜ ከተነሳ በኋላ በምርጫው ወቅት ፈጸሙት ለሚባለው ለየትኛውም ወንጀል ተጠያቂ ሆነው ውይያዛሉ። ከፋቱ ይህ የህግ ድንጋጌ በ 2002 ዓ.ም የምርጫ ሂደቱ ወቅት ሁልጊዜም አልተከበረም ነበረ።[11]

የእጩዎች ምዝገባ በምርጫ ክልል የምርጫ ቢሮዎች ደረጃ የተከፈተው ታህሳስ 16/2002 ዓ.ም ነው። በብሔራዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ጉባዔ ላይ በአያሌ የፖለቲካ ፓርቲዎች እጩዎቻቸው አቋርጠው እንዲወጡ እየተገደዱባቸው እንደሆነ ከቀረበው ተከታታይ ቅሬታዎች በኋላ ኢብምቦ የእጩዎች ምዝገባ ቀኑን ወደ የካቲት 15 ቀን 2002 ዓ.ም አራዝሞታል። ደግሞም ተጨማሪ የአምስት ቀን "የመቻቻል" ጊዜ እንዲኖር ፈቅዷል። በኢብምቦ የታየው እንደ ሁኔታው የመለዋወጡ ሁኔታ ከዚህ አኳያ በምርጫው ሂደት ወቅት ግዙፍ ብዙሃነትን ለማምጣት ረድቶ ነበረ። እንደ ኢብምቦ ከሆነ 2,188 እጩዎች ለህተም እና 4,746 ለተለያዩ የክልል ምክር ቤት ምርጫዎች ተመዝግበው ነበር። ይህ ደግሞ ከ 1997 ዓ.ም ምርጫ ጋር ሲተያይ ለእያንዳንዳቸው ወሳኝ የሆነ የ 18% እና የ 26% ገደማ እድገት ነው።

ስለ እጩዎች ምዝገባ በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው (ቅሰኮ) የቀረቡት ቅሬታዎች አስራ አንድ ብቻ ናቸው። እርሱም በዋናነት የቋንቋ መስፈርቱን ባለሟሟላት ወይም የሚጠየቁትን ሠነዶች በተባለው ጊዜ ማቅረብ ባለመቻላቸው የሆነ ነው። ስለ እጩምዝገባ የተነሱት ሁሉም ቅሬታዎች እና አቤቱታዎች በበቂ ሁኔታ መፍትሄ አግኝተዋል። የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት (ፌከፍ) እጩምዝገባን እና የእጩነት ምልክትን በተመለከተ ሦስት አቤቱታዎችን በኢብምቦ ወይም ቅሰኮ ላይ የተቀበለ ሲሆን እርሱም ቀደም ሲል የተወሰዱ ውሳኔዎችን ያስጠበቀ ነው።

በሶማሌ ክልል የእጩምዝገባ የተካሄደው ከመራጭ ምዝገባ ጋር በአንድ ላይ በ 21 ቀናት ጊዜ ከ መጋቢት 10 ጀምሮ ነበረ። ምንም እንኳን በኋላ ላይ ሂደቱን[12] ከመካፈል ከተቆጠቡት ከአንዳንድ የክልል ፓርቲዎች ጥያቄው ቢመጣም በሌሎች የሃገሪቱ ክልሎች ተደርጎ እንደነበረው ሁሉ የእጩምዝገባ ጊዜው አልተራዘመም። ከአንዳንድ መነሻ ግራ መጋባቶች በኋላ እና ቀደም ሲል ከተከናወኑ ምርጫዎች በተቃራኒ በሶማሌ ክልል ያለው የህተም ምርጫዎች በሌሎች የሃገሪቱ ክልሎች እንደሚደረገው ሁሉ በተመሳሳይ ቀን እንዲከናወን ተደርጓል። የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ ከሰባት ቀናት በኋላ ግንቦት 22 ቀን እንዲካሄድ ተደርጓል። ሆኖም ግን የእጩዎች ምዝገባ ከአፊሲያላዊው የምርጫ ቅስቀሳ ጅማሬ በኋላ የተከናወነ የመሆኑ እውነታ ከሌሎች የሃገሪቱ ክልሎች ጋር ሲነጻጸር በሶማሌ ክልል ያለውን የቅስቀሳ ጊዜ እንዲያጥር አድርጎታል። ምንም እንኳን ይህ የድምጽ መስጫ ቀናት ተስማምቶ መካሄድ አዎንታዊ ቢሆንም የአጎ ምታል ግን የእኩልነት መርኾዎች በእጩምዝገባ ሂደቱ እና በሶማሌ ክልል ባለው የቅስቀሳው ጊዜ ላይ በበቂ ሁኔታ እንዳልተከበረ ያስባል።

## VIII. የምርጫ ቅስቀሳ እና የቅድመ-ምርጫ ሁኔታዎች

*ሀ. የምርጫ ቅስቀሳው ዳራ*

ኦፊሲያላዊው የምርጫ ቅስቀሳ ጊዜ ከምርጫው ቀን ወደ ሦስት ወራት አካባቢ ቀደም ብሎ የካቲት 2 ቀን የተጀመረ ሲሆን ያበቃው ደግሞ ከ 48 ሰዓታት የቅስቀሳ ጸጥታ ጊዜ በኋላ ነበር። ህጉ ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅስቀሳዎቻቸውን በተመቻቸ የመጫወቻ ሜዳ ውላይ በነጻነት እንዲያከናውኑ መብት ይሰጣቸዋል። የቅስቀሳ ግዴታዎች መሰረታዊ የሆኑ ሰልፍ ለማካሄድ ህዝባዊ ቦታዎችን በእኩልነት እንደመያዝ እና የቅስቀሳ ቁሳቁሶችን እንደመለጠፍ እንዲሁም ለብዙሃን መገናኛው እኩል የሆነ እድል እንደማግኘት ያሉ መርኾዎችን ያስቀምጣል። የሚያስቆጣ፣ ስም አጥፊ፣ ወይም አንቋሻሽ ቋንቋ ያለበት ወይም ለህዝብ መቃወስ፣ አመጽ ወይም ማስፈራራትን የሚያነሳሱ ነገሮችን መጠቀምን ከልክለዋል። ከቅስቀሳ ሰልፎች አኳያ ከአውራጃው ኮሚሽነሮች ምንም አይነት የቅድሚያ ፈቃድ አያስፈልገውም፤ ፖሊስ እንዲያውቀው ለማንኛውም በሚል እንዲህ አይነቶቹን ክስተቶች ለህዝባዊ ስርዓቶች ሲባል ብቻ መረጃ ደርሶት እንዲያውቀው ይደረጋል። በህዝባዊ ቢሮው ከሚፈለገው ውጪ ላሉ ዓላማዎች የመንግስትን ጥሪቶች መጠቀምን የሚከለክሉ ህጋዊ ደንቦችም አሉ።

*ለ. የምርጫ ቅስቀሳው ድባብ*

የምርጫ ቅስቀሳው ድንጉጥ፣ ዝግተኛ እና የተረጋጋ ሳይሆን ጸጥ ያለ ሁኔታ ባለው መልኩ ተካሂዷል። ይሁን እንጂ ቅስቀሳው ምንም እንኳን እውነተኛ የሆነ የጋለ ስሜትን በአመዛኙ ህዝብ ላይ መፍጠር ቢሳነውም በመጨረሻው ሳምንት አካባቢ ላይ እያየለ የሄደበት ከፍታ ግን ነበረው። ሁሉም ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሰላማዊ ምርጫ ለማካሄድ ያላቸውን የተሟላ መሻት ደጋግመው አሳይተዋል። ሆኖም ግን የተለያዩ ተካፋዮች በዛ ያሉ ግፊት ተደረገብን የሚሉ እና በገዢው ፓርቲ፣ በማዕከል አስተዳዳሪዎች እና በፖሊስ ብሎም በአነስተኛ ደረጃ በቅስቀሳው ወቅት በተቃዋሚ ፓርቲዎች

---

[11] ለተጨማሪ ዝርዝር ክፍል X ሰብዓዊ መብቶች እና የሴቶች ተሳትፎ የሚለውን ያመሳክሩ
[12] ለተጨማሪ መረጃ እባክዎን የምርጫ ቅስቀሳ እና የቅድመ-ምርጫ ሁኔታ፣ ሲ. የእጩአቋርጦ መውጣት ክፍል VIII. የሚለውን ይመልከቱ

ማስፈራራት ተደረገብን የሚሉ ክሶችን ሪፖርት አድርገዋል። በአንዳንድ ክልሎች ፖለቲካዊ መነሳሳት ያላቸው ሊሆኑ የሚችሉ ጥቂት የአመጽ ጉዳዮች ተከስተዋል፤ በተለይም በኦሮሚያ እና ትግራይ። በዚህ ጽሁፍ ዝግጅት ጊዜ ትክክለኛ ዝርዝር እና የአያሌዎቹ የእነዚህ ተግባራት ሁኔታዎች ግልጽ አልነበሩምነበረ።

የተወሰኑ የፖለቲካዊ አመጾች የተባሉት ንዝነዛዎች እና ማስፈራራቶች ኮስተር ያሉ አነጋጋሪ ጉዳዮች ነበሩ። እነዚህ የተባሉት ነገሮች በዋናነት ነገር ግን ሙሉ በሙሉ ሳይኾን በገዢው ፓርቲ፣ በማዕከሉ አስተዳደሮች እና በፖሊስ ላይ በተቃዋሚ ፓርቲዎች የተደረጉ ነገሮች ናቸው። አብዛኞቹ የበለጡ መራራ የነበሩ የቅስቀሳ ንግግሮች እርስ በእርስ በተለያዩ የቅስቀሳ ጥፋቶች[13] ላይ በተካሰሱት በኢህአዴግ እና መድረክ መካከል የተካሄዱት ነበሩ። ተቃዋሚ እጩዎች የፖለቲካ ተግባራቶቻቸውን በማከናወናቸው ሊመጡ የሚችሉትን ውጤቶች ፈርተው ለአኅ ምታል ታዛቢዎች በተከታታይ ፍርሃታቸውን ሪፖርት አድርገዋል። ምንም እንኳን አብዛኞቹ የተባሉት ነገሮችን የሚያረጋግጡ የተጨበጠ መረጃ ባይኖርም በተቃዋሚ እና በገዢው ፓርቲ ሃይላት መካከል በተወሰኑ የሃገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሰቀለ ደረጃ ያለው ውጥረት እንደነበረ አመላካች ነው። ተከታታይ የተቃዋሚ ፓርቲዎችን ሰልፍ ከመንግስት መገናኛ እና ኮሚዩኒኬሽን ቢሮ በፊልም መቅረጫ መቀረጹ ሊያስፈራራቸው የሚችል እንደሆነ የአኅ ምታል ታዛቢዎች ገምቷል። በጥቅሉ ልዑኩ ሰላማዊ ምርጫዎችን ለማካሄድ ተደጋግመው ከተደረጉት ጥሪዎች ባሻገር በሃገሪቱ ሁሉ ከዛቻ እና ማስፈራሪያ ውጪ የሆነ ቅስቀሳ ለማካሄድ ያለውን መብት ለመጠበቅ በቂ ያልሆኑ እርምጃዎች ተወስደዋል።

የተለያዩ ተሳታፊዎች የፖለቲካ ቅስቀሳዎችን የተሸነፈ ድባብ ተያያዥ ከሆኑ እውነታዎች የተነሳ ነው ይላሉ። የ 1997 ዘላቂ የሆኑት ትውስታዎች በህዝቡ መካከል ለፖለቲካዊ መመሪያዎች ሃያል ባህሪ በመሆን በእርግጥም አገልግሏል። ለአብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች የገንዘብ ድጋፍ እጥረት መኖሩም በተጨማሪ ለተቀዛቀዘው ቅስቀሳ በድጋሚ የሚገለጽ ግልጽ ምክኒያት ተደርጎ ይወሰዳል። እርሱም ዘግየት ብለው ለሚሆኑት ቅስቀሳዎች ገንዘብ ለማቆየት የተወሰደ ብልሃታዊ ውሳኔ ነው። በተጨማሪም የኢሲሲፒፒ ስምምነትን በጣሱት ላይ ከምርጫው ሂደት በኋላ ህጋዊ እርምጃ እንደሚወሰድ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የተደረገው የህዝባዊ አዋጅ ማስጠንቀቂያ ለአንዳንድ የተቃዋሚ መሪዎች ያሳሰባቸው ነገር ነበረ። ይህም በኢትዮጵያ ህገ መንግስት አንቀጽ 38 መሰረት የእጩዎችን ንግግር የማድረግ ነጻነት፣ ቅስቀሳ የማድረግ ነጻነት እና የመመረጥ መብታቸውን የገደበ ተደርጎ ሊታይ ይችላል፡፡

የተወደደው የምርጫ ቅስቀሳ ዘዴ ቤት ለቤት እየሄዱ የሚደረግ አሰሳ ነው። አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች ይህንን ዘዴ ለገንዘብ ድጋፍ እጥረታቸው ገንዘብ ቆጣቢ ስልት አድርገው ወስደውታል። በሃገሪቱ ዙሪያ ያለው የተገደበ የብዙሃን መገናኛው ተፅዕኖ በቅስቀሳው ላይ ሊኖረው የሚችለውን ግብዓት ቀንሶታል። አያሌ የተቃዋሚ ፓርቲዎች የኢህአዴግን የቤት ለቤት ቅስቀሳ ስልት እንደ ገደቢስ አድርገው ቆጥረውት ነበረ። ምንም እንኳን አተታ የተካሄደበት የመራጮች ዝርዝር፣ በፖለቲካዊ ታማኝነት ላይ ያለው ጥያቄ እና ሰንሰለትን መሰረት ያደረገ የተባለው ምልመላዎች ሙሉ ለሙሉ በህጋዊ ገደቦች ስር ቢሆኑም አንዳንድ ፓርቲዎች ከፉኛ የቀኑ የፖለቲካ ካድሬዎች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ኃይል ተጠቅመዋል ብለዋል። ጥቂት የተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዲህ አይነቶቹ ግፊቶች ልክ እንደ ማስፈራሪያዎች እንደነበሩ ጠቁመዋል።

ኢህአዴግ ከግዙፍ ህዝባዊ ቁጥር ድጋፍ ጋር በሰልፎቹ እና በመላው ሃገሪቱ እጅግ ብዙ በሆኑ ተለጣፊ ማስታወቂያዎች አማካኝነት በጣም የተሳካ እና የሚታይ ፖለቲካዊ ቅስቀሳ አካሂዷል። እንደ ቀድሞው ሁሉ ኢህአዴግ ቅስቀሳውን ያተኮረው 19 ዓመታት በስልጣን ላይ በመቆየቱ የተገኙትን ስኬቶች ከሃገሪቱ የኢኮኖሚ እድገት እና በመሰረተ ልማት ከታዩት ወሳኝ እድገቶች አንጻር በማሞገስ እየተናገረ ነበር። የተቃዋሚ ፓርቲዎች ቅስቀሳዎች ከዛ ይልቅ በጣም አነስተኛ ነበሩ። ተቃዋሚ ፓርቲዎች አሳማኝ የሆኑ አማራጭ የመንግስት ፕሮግራሞችን ማቅረብ አልቻሉም። በተወሰነ ሁኔታም አብዛኞቹ ቅስቀሳዎቻቸው በመንግስት እና በኢህአዴግ ላይ ትችቶችን መሰረት ያደረጉ ነበሩ።

*ሐ. ከእጩነት ስለ መሰናበት*

እንደ ኢብምቦ ከሆነ 72 እጩዎች በቅስቀሳው ጊዜ ላይ አቋርጠው ወተዋል። ብዙውን ጊዜ ማስፈራራት እና ንዝነዛ እንዲሁም የገንዘብ አቅም ማጣት እና በኢብምቦ ማዕከላዊ መዋቅሮች ላይ የታዩ አድልዎች ስላሉ እንደሆነ ተናግረዋል። በአንጻሩ አነስተኛ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሙሉ ለሙሉ አቋርጠዋል።[14] አራት ክልላዊ ፓርቲዎች በሶማሌ ክልል ምርጫውን ሙሉ ለሙሉ ከመሳተግ ተቆጥበዋል።[15] በማዕከላዊ ትግራይ የመላው ኢትዮጵያዊያን አንድነት ፓርቲ ከዋናው መስሪያ ቤት የገንዘብ ድጋፍ እጥረት እንደገጠመው በመግለጽ እጩዎቹን አሰናብቷል። በውጤቱም ገዢው ፓርቲ በ 36 የምርጫ ክልሎች ውስጥ ብቻውን ለመመረጥ ሊቆም ችሏል። ከእነዚህም ውስጥ 16 በሶማሌ ክልል፣ ሦስት በአማራ ክልለ፣ አምስት በደቡብ ህዝቦች ብሔር ብሔረሰቦች ክልላዊ መንግስት እና አንድ በትግራይ እንዲሁም 11 በኦሮሚያ ናቸው። በተመራጮች እና በተወካይነት ባህሪ ባለው ሂደቱ ምርጫየ ማድረጉ ሁኔታ በእነዚህ የምርጫ ክልሎች ውስጥ ጠባብ ነው።

---

[13] ኢህአዴግ መድረክን "ችግር ፈጣሪዎች" ሲል የከሰሰ ሲሆን ሰላማዊ ምርጫን ለማስኬድ የተደረገውን የኢሲሲፒፒ ስምምነትን ላለመፈረም ተቃዋሚዎች ሆናችኋል በሚል ነበር። እነርሱ እንዲሁም በተከለከሉ የቅስቀሳ ቦታዎች (እንደ ገበያዎች ባሉ) ላይ ቅስቀሳ በማድረግ ተደጋግሞ ተከሰው የነበረ ሲሆን የቅስቀሳ ቁሳቁሶችን በመደምሰስ እና "የጥላቻ ፖለቲካ" በማራመድ የሚከሰሱም ነበሩ።

[14] የአፋር ነጻነት ግንባር (አነግ)፣ የአፋር አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ህብረት ግንባር (አአዲህግ)፣ የአፋር ብሔራዊ አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (አብአዴግ)።

[15] የሶማሌ ዴሞክራሲያዊ ህብረት ኃይሎች (ሶዴህኃ)፣ የዴል ዋቢ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ፣ የዱቤ እና ዳኙ ብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ እና የምዕራብ ሶማሌ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ።

*መ. የመንግስትን ጥሪት አጠቃቀም*

የህዝብ ጥሪቶች አጠቃቀም (የፌደራል፣ የክልላዊ፣ የማዘጋጃ ቤት ወይም ሌሎች) ለተናጥል ፓርቲ ቅስቀሳ መዋላቸው በኢሲሲፒፒ ስምምነት አንቀጽ 14 ላይ "ሥልጣንን ያላግባብ መጠቀም" በሚል የተከለከለ ነገር ነው። ይሁን እንጂ አኅ ምታል ታዛቢዎች የእንዲህ አይነቶቹን ጥሪቶችን በገዢው ፓርቲ ቅስቀሳ ወቅት በሃገሪቱ ዙሪያ በዋናነትም በኦሮሚያ፣ ሶማሌ ክልል እና በትግራይ ጥቅም ላይ ሲውል እንዳስተዋሉ መስክረዋል። በተመሳሳይም ልዑኩ በዜጎች እንደ አንድነት ጠላ ማንነት በሚታዩት እና በሚመሳከሩት በገዢው ፓርቲ እና በማዕከላዊ አስተዳደር መካከል ደበዛዛ ልዩነት እንዳለ ታዝቧል። በህዝባዊ አስተዳደር ባሉ ህንጻዎች ላይ ያሉ የገዢው ፓርቲ ፕሮፐጋንዳ መካሄዱ፣ የመንግስት ሰራተኞች በስራ ላይ እያሉ የገዢውን ፓርቲ ፕሮፓጋንዳ መልበሳቸው፣ የኢህአዴግ የቅስቀሳ ተለጣፊ ማስታወቂያዎችን በማዕከል የአስተዳደር መኪናዎች ላይ መለጠፍ፣ የማዕከል አስዳደር ስራ ቢሮዎችን የቅስቀሳ ተግባራትን ለማከናወኛነት መጠቀማቸው፣ የገዢው ፓርቲ ቢሮዎች በማዕከል አስተዳደር ግቢዎች (ብዙዉን ጊዜ የኢብምቦን ቢሮዎች ያስተናገዱ) ውስጥ ማስተናገዳቸው እና የኢህአዴግ ተለጣፊ ማስታወቂያዎችን በማዕከል አስተዳደራዊ መቆያዎች ማከማቸትን የመሳሰሉት ነገሮች በሙሉ በአኅ ምታል በቀጥታ ለትዝብት የበቁ ነገሮች ናቸው። እነዚህ ተግባራት በቅስቀሳ ወቅት ሥልጣን ይዞ ላለው አግባብ ያልሆነ ጥቅም ያስገኙ ሲሆኑ እንዲሁም ደግሞ ቀደም ብሎም ደብዘዝ ብሎ ባለው በመንግስት እና በገዢው ፓርቲ ላይ ያለውን ልዩነት ያደበዘዙ ናቸው።

የተለያዩ ተካፋዮች የህዝባዊ ባለስልጣናት ለፖለቲካዊ ታማኝነት ብለው የ"ሴፍቲ ኔት" ፕሮግራምን በዋናነት በመጠቀም የምግብ እርዳታን መለወጣቸውን ጨምሮ ሥልጣን አላግባብ ማዋል እንዳካሄዱ እየተናገሩ ድምጻቸውን ያሰማሉ፣ በተለይ በትግራይ ክልል። አኅ ምታል እነዚህን የተባሉትን ነገሮች ሊያረጋግጥ አልቻለም። ተቃዋሚ እጩዎች መጓጓዣውን፣ የቢሮ ኪራዩን እና መስተንግዶውን በያዙት የማዕከል ባለሥልጣናት የሚመጣውን መሰናከል በሌሎች መሰረታዊ ነጻነቶች ላይ እና ለመመረጥ ባላቸው መብት ላይ እያመቻቹ በመሆኑ ቅር ተሰኝተውብ ታል። ምንም እንኳን ተቃዋሚ ፓርቲዎች በገዢው ፓርቲ ብሔራዊ ስፋት ያለው ስልት እንደሚቀናጅላቸው የሚጠቀስ ቢሆንም እነዚህ አመለካከቶች ከፉኛ በቀኑ የማዕከል ፖለቲከኞች እና አስተዳዳሪዎች ግለሰባዊ ተነሳሽነት የተቀነባበሩ ተግባራት ሊሆኑ እንደሚችሉ ይገመታሉ። ከዚህ አኳያ አኅ ምታል በድርጅት እና የምርጫ ሂደት አተገባበር ላይ ያሉ የማዕከል አስተዳደራዊ ባለስልጣናት ሚና በሂደት ሊገደቡ እንደሚገባ ያምናሉ። ይህ በምርጫው ሂደት ውስጥ ላለው ግልጽነት እና ገለልተኝነት የሁሉንም ፓርቲዎች የመታመን ደረጃ ለማሳደግ ይረዳል።

*ሠ. የቅስቀሳ ገንዘብ ድጋፍ*

ለፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ቅስቀሳ የተደረገው ህዝባዊ የገንዘብ ድጋፍ በኢትዮጵያ ፌደራል ምርጫዎች አዲስ ነገር እንደ ፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ እና እንደ ኢብምቦ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚደረግ የመንግስት የገንዘብ ድጋፍ ማከፋፈል አወሳሰን ስርዓት ደንብ መሰረት የተካሄደ ነው። የገንዘብ ድጋፎች በፌደራል መቀመጫዎች ውስጥ ባሉት የተመረጡ ተወካዮች ቁጥር መሰረት እና በተሞሉት እጩዎች ቁጥር ብሎም በሴት እጩዎች ልክ ነው። ይህ ቀመር ቀደም ብሎም በህተም ውስጥ ተወክለው ላሉት ፓርቲዎች ያደላ ሲሆን ገለልተኛ እጩዎችን ደግሞ ችላ ያለ ነው። እንደ ኢብምቦ ምንጮች ከሆነ ወደ 13 ሚሊዮን ብር ተመድቦ ነበር።[16] አበዛኞቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የተቀበሉት መጠን ውጤታማ ቅስቀሳ ለማድረግ የማይበቃ እንደነበረ ገምተዋል። አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች በእነዚህ የገንዘብ ድጋፎች ስርጭት መዘግየቶች ላይ በተደጋጋሚ ቅሬታ ሲያሰሙ ነበረ።

የፖለቲካ ፓርቲዎች በተለመዱት የገቢ ምንጮቻቸው የቅስቀሳ ጥረቶቻቸውን በገንዘብ ይደግፋሉ። በፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ እንደጸደቀላቸው እነዚህ ድጋፎች የአባልነት ምዝገባ እና ከኢትዮጵያዊያን ዜጎች እና ድርጅቶች የሚገኙትን ድጋፎችን የሚያካትቱ ናቸው። ከውጪ ሃገር ዜጎች፣ ድርጅቶች፣ መንግስታት ወይም የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚገኝ እርዳታ እና ልገሳ የተከለከለ ሲሆን ከሃይማኖት ድርጅቶች፣ አሸባሪ ድርጅቶች ወይም ከተለያዩ ምንጮች ጭምርም እንዲሁ። ከኢትዮጵያዊያን የውጭ ሃገር ነዋሪዎች የሚላከው የገንዘብ መዋጮ ከ 1997 ዓ.ም ምርጫዎች አንጻር ሲተያይ አነስተኛ ጠቀሜታ እንደነበረው ሪፖርት ተደርጓል። ይህም ሊሆን የቻለው ከፖለቲካ ፓርቲዎች የምዝገባ አዋጅ ገዳቢ ሁኔታዎች አንጻር ሊሆን ይችላል። ኢህአዴግ ከትልቅ የገንዘብ ምንጮች፣ ከትልቅ የአባላቶቹ የገንዘብ መዋጮ እንዲሁም ከበርካታ የግል ዘርፍ የተገኙ የገንዘብ ድጋፎች ተጠቅሟል።

## IX. ብዙሃን መገናኛ እና ምርጫዎች

*ሀ. የብዙሃን መገናኛው ሁኔታ*

[16] ወደ 720,000 ዩሮዎች ገደማ

የወሳኝ ሆኖም በከፍተኛ ሁኔታ የተወጠረ የብዙሃን መገናኛ ሁኔታ የ 1983ን የብዙሃን መገናኛ ዘርፍ ነጻ መውጣት ተከትሎ ተገኝቷል። ሆኖም ግን በመንግስት እና በግል ህትመቶች መካከል ያለው ግንኙነት በጋራ አለመተማመን ያለው ነው። የ 1984 የህትመት ህግ ባለስልጣናቱ ጋዜጠኞችን ያለ ክስ ያቆዩዋቸው ዘንድ ፈቀደ። ተግባራዊ የተደረገውን ህግ ተከትሎ አያሌ ጋዜጠኞች በእርቅ ቆዩ። በኢትዮጵያ ያለው የብዙሃን መገናኛ ሁኔታ ወደ 1997ቱ ለሚደረገው የምርጫ ጥድፊያ በጣም ንቁ የሆነውን እመርታ ተለማመደ፤ በተለይ ደግሞ በጽሁፍ ህትመቶች። የተስፋፉ ሽፋን ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ተሰጠ ምንም እንኳን በጣም ግልጽ የሆነ አድልዎ ቢኖርም።[17] እነ ዚህን የ 1997 ምርጫዎች ተከትሎ አያሌ ጋዜጠኞች እንዲቆዩ እና ከተለቀቁም በኋላ ሃገሪቱን ትተው እንዲወጡ ተደርጓል። አያሌ ጋዜጦችም በዚህ ጊዜ እንዲዘጉ ተደርጓል። አሁን ያለው የብዙሃን መገናኛ ሁኔታ ያን ያክል ንቁ አይደለም እንዲሁም ደግሞ በአንድ አቅጣጫ የተወጠረም አይደለም።

ምንም እንኳን ጋዜጦች እና ቴሌቭዥን ጣቢያዎች በአያሌ የከተማ ክልሎች የሚገኙ ሲሆኑ ራዲዮ ጣቢያዎች የተገደቡ ቢሆኑም ከወሳኝነት ጋር በሃገሪቱ ዙሪያ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ናቸው። የግል ዘርፉ እያደገ ቢሆንም የኢትዮጵያ የብዙሃን መገናኛ ሁኔታ አሁንም ቢሆን በመንግስት ባለቤትነት በተያዙ የመገናኛ ብዙሃን የተዋጡ ናቸው። መንግስት ብቸኛ የሆነውን ብሔራዊ ስፋት ያለውን የቴሌቭዥን መረብ በባለቤትነት ይዟል።

አንድና ብቸኛ የሆነው የሀገር ውስጥ ቴሌቪዥን ስርጭት፡ ከበርካታ ክልላዊ ቅርንጫፎቹ ጋር፣ አገር አቀፍ ሬድዮ ጣቢያዎች፣ አካባቢያዊ ሬድዮ ጣቢያዎችና በርካታ የህትመት ማሰራጫዎች በመንግስት ቁጥጥር ስር ናቸው። በግለሰቦች የሚካሄዱ መገናኛ ብዙሃን ቁጥራቸው አነስተኛ ሲሆን፡ እነዚህም በአዲስ አበባና አካባቢው የተወሰኑ ናቸው። ከዚህ ለየት ያለ ነገር ቢኖር በአገር አቀፍ ደረጃ የሚያሰራጨው ሬዲዮ ፋና ነው። በርካታ ቁጥር ያላቸው ራሳቸውን የቻሉ ነፃ ጋዜጦች በትልልቅ ከተሞችና በአካባቢያቸው ይሰራጫሉ። በመንግስት ቁጥጥር ስር የሚገኘው የቴሌኮሚኒኬሽን አገልግሎት ሞኖፖሊ ሲሆን፡ የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን አንድና ብቸኛ የሆነውን የኢንተርኔት አገልግሎት ይቆጣጠረዋል። አንዳንድ የኢንተርኔት ሳይቶች፡ በተለይም ውጭ አገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የሚካሄዱት፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ይታገዱ/ይታፈኑ ነበር።

የውጭ አገር ሬዲዮ ጣቢያዎች፡ በቮይስ ኦፍ አሜሪካ (voa) እና በዶች ቬለ (Deutsche Welle) የሚካሄዱ ሬድዮ ጣቢያዎች በሀገሪቱ ውስጥ ይሰራጫሉ። ነገር ግን ከውጭ አገር በሚሰራጩት የማይጥሙ ሪፖርቶች ሲከሰቱ በኢትዮጵያ ባለስልጣኖች ብዙ ቅብልነት የላቸውም። መንግስት ሀገሪቱን ያዋከባል የሚለውን የ ቪኦኤን ኤዲቶሪያል መስመር ለመቃወም የሚያስችል አለም-አቀፋዊ የህግ መድረክ የለም በሚል ምክንያት የሀገሪቱ የመገናኛ ብዙሀን ተቆጣጣሪ አካል -የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን -ከውጭ ጣልቃ ገብነትን ለማገድ፡ መረጋጋቷንና እድገቷን የሚያደናቅፍ ነው በማለት እፈናውን ሊያፀድቀው ችሏል።

ዶች ቬለ ምርጫው ከመካሄዱ ሁለት ቀን በፊት ስርጭቱ ታፍኖ እንደነበር፡ ምርጫው ከተጠናቀቀ በኋላ ግን እንደበፊቱ ያለ ችግር ቀጥሏል። ዶች ቬለ በመጀመርያ የ <<ቴክኒካል ብልሽት>> ብሎ ገልፆት እንደነበር፡ በኋላ ግን በመንግስት የመታፈኑን ነገር አለም-አቀፋዊ የኢንፎርሜሽንን ነፃነትን የሚጥስ ህገ-ወጥ ድርጊት ብሎ ኮንኖታል። በተመሳሳይ ሁኔታ በግንቦት 7 ስርጭት ይጀመረውን ውጭ አገር በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የተመሰረተውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ከግንቦት 16 ጀምሮ በተደጋጋሚ መቋረጥና መታፈን እንደደረሰበት ታይቷል።

*ለ. የመገናኛ ብዙሃንና የምርጫ ህግ ማዕቀፎች*

ህገ-መንግስቱ በራስ መግለጽ ነፃነት (freedom of expression) ዋስትና ይሰጣል፡ ከዚህ በተጨማሪም የአፈና ድርጊትን (censorship) ያግዳል። የመገናኛ ብዙሃንና የኢንፎርሜሽን ቀረቤታ ነፃነት ለሚድያ ፕሮፌሽናሎች አዎንታዊ የሆነ ለውጥ፡ በተለይም ጋዜጠኞች ከመፈረዳቸው በፊት የመታሰር ሁኔታዎችን ማሻሻል አምጥቷል። በአንፃሩ ግን ይህን ህግ ተመርኩዞ መንግስት ስም ማጥፋት እያለ ክስ ማቅረብ፣ የገንዘብ ቅጣት እርምጃ መውሰድ፡ በተጨማሪም የብሮድካስት ፍቃድ መከልከልንና መንጠቅን ሊጠቀምበት ችሏል። ይህ ህግ ምንም እንኳን በቅርብ በተካሄደው የምረጡኝ ዘመቻ ላይ ባይጐበኝም፡ ሽብርተኝነትን በሚመለከት የወጣው ህግ ትንታኔ ውልቅ በመሆኑ ባለስልጣኖች እንደመሰላቸው ተጠቅመው ሽብርተኛነትን ያሰራጫል የሚል ክስ ማቅረብ ያስችላቸዋል። ይሄም ስለ ታጠቁ ተቃማዊ ቡድኖች የሚተነትኑ ሀተታዎችን ወይም በባለስልጣኖቹ አመለካከት ፀረ-ሰላም ወይም ፀረ-ህዝብ ተብለው የተገኙ የሚድያ ሪፖርቶችን ሊያጠቃልል ይችላል።

በሚድያ ሀተታ የመስጠት ነፃነት በጥቅሉ በምርጫው ተከብሮ እንደነበር፡ ጋዜጠኞችም የተለያዩ ፓርቲዎችንና የእጩዎችን የምረጡኝ ዘመቻ ሂደት በነጻነት ሊሸፍኑ ችለዋል። አንዳንድ ግላዊ ጋዜጠኞች ከመንግስት ባለስልጣኖች የኢንፎርሜሽን ቀረቤታን ለማግኘት ጠብነት እንደተሰማቸው ገልጸዋል። ነገር ግን በግል በሚካሄዱ ሚድያዎች ፀረ-መንግስት የሆኑ ብሮድካስቶች ከመጠን በላይ በጥንቃቄና ጥቂቶች እንደነበሩ፡ ይህ እንደ ራስን

[17] ለተጨማሪ ዝርዝር "የአጎ ምታል የህግ አውጪ ምርጫዎች በኢትዮጵያ 1997 የመጨረሻ አተታ" የሚለውን እባክዎ ያመሳክሩ http://ec.europa.eu/external_relations/human_rights/election_observation/ethiopia/final_report_en.pdf.

ማገድ (self-censorship) የታየውን ሁኔታ ለልዑክ ቡድኑ ዘገባ ቀርቦለታል። ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ፕሮፌሽናል እውነተኛነትና ብቃት ጐዶሎነው የሚለውን የመንግስት ነቀፌታ በከፊል ቢረጋገጥም ይሄ ነገር በግል በሚካሄዱ ጋዜጣዎች ብቻ የተወሰነ አልነበረም። እነኚህ ክስቶች የግል ጋዜጠኞች በህግ ተርጓሚው ባለስልጣን ከመንግስት ገለልተኝነት (independence) ያላቸውን የአመኔታ ጉድለት፡ ግላዊ ሚድያዎች ፀረ-መንግስት የሆኑ ነቀፌታዎችን በጭብጥ የማጣራት ወይም ጥናታዊ ጋዜጠኝነት የማካሄድ ችሎታቸውን ወስኖታል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የሚድያ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችንና የምርጫ አስተዳዳሪ አካልን መብትና ሀላፊነትን የሚወቅር የምርጫ ስነምግባርና ደንብ ምርጫውን ለሚያሰራጩ መገናኛ ብዙሃንና ጋዜጠኞች ሰጥቷል። ይህ የምርጫ ስነምግባርና ደንብ በአለም-አቀፋዊ የምርጫ ስርጭት ወግና ደንብ ተከትሎ የወጣ ቢሆንም፡ ከምርጫው ቀን ጥቂት ሳምንታት በሚያዝያ 7 የወጣ በመሆኑ የሚያሳዝን ነገር ነው።
የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማህበር በዚህ ደንብ ረቂቅ ዝግጅት ውስጥ እንዲሳተፉ መደረጉ አዎንታዊና አሳታፊ የሆነ እርምጃ ነው። የግል ጋዜጠኞች ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ከነኚህ ውይይቶች ስላገለላቸው ተችተውታል።
በምርጫ ህጉ መሰረት የመንግስት ሚዲያ ለሁሉም ተፎካካሪ ተዋናዮች እኩል ተደራሽ የመሆንና እንዲሁም ነፃ የአየር ጊዜ የመስጠት ግዴታ አለባቸው። በህጉ ባይጠቀስም እንኳ የግል የብሮድካስት ሚዲያም በብሮድካስት አገልግሎት ህግ መሰረት እንዲሁ የማቅረብ ግዴታም አለባቸው። ባጠቃላይ የኢትዮጵያ ሚዲያ በምርጫ ሂደቱ ጉልህ የሆነ ሚና ለመጫወት ያላቸውን ፍላጎት አሳይተዋል፣ ብዙዎቹም ግዴታቸውን ለመወጣት ከማስታወቂያ የሚገኙ ገቢዎች ወደመጠቀም ገብተዋል።

በምርጫው ለሚወዳደሩ 63 የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ በዛ ያለ ነፃ የአየር ጊዜና ቦታ በብሔራዊ ምርጫ ቦርድና በኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ተሰጥቷቸዋል። የአየር ጊዜና ቦታው ከሌሎች አገሮች ልምዶች በተሰሩ ቀመር መሰረት ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ተከፋፍለዋል፣ ይህም በብሔራዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ስምምነት የተደረሰበትና በምርጫ ቦርድ ደንብ የወጣ ነው።[18] በተጨማሪም በጋራ ምክር ቤት ስምምነት በተደረሰባቸው ዘጠኝ የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሊቪዥን ድርጅት (ኢሬቴድ) ክርክር አዘጋጅቶ ነበር። በተሳታፊ ፓርቲዎች ከፍተኛ ብዛት የተነሳ አምስት ፓርቲዎች (ኢህአዴግ፣ መኢአድ፣ ኢዴፓ፣ ቅንጅትና መድረክ) ብቻ ናቸው ክርክሮቱን በመደበኝነት የተከታተሉት። ክርክሮቹ በተሳታፊዎቹ ጥያቄ መሰረት የተቀረፁና አርትኦት የተሰራላቸው ናቸው። በመንግስት ሚዲያ ውስጥ ያለ የክርክሮቹ የዘፈቀደ አርትኦት በተመለከተ ኢዴፓ ለጋራ የፓርቲዎች ምክር ቤት አቤቱታ አቅርቦ ነበር። ነፃ የአየር ጊዜ በተመለከተ የኢዴፓ ሁለተኛ አቤቱታ እና የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲና የመላ ኢትዮጵያ ብሔራዊ ንቅናቄ ተመሳሳይ አቤቱታ ለጋራው ምክር ቤት ቀርበው ከኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ጋር በመተባበር እነኚህን ቅሬታዎች የሚያጣራ አጣሪ ኮሚቴ እንዲፈጠር ተወስኗል። እንደ ኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ከሆነ ሁሉም አቤቱታዎች በፓርቲዎቹ ስምምነት ተፈትተዋል። በቅስቀሳው ወቅት የብሮድካስት ባለስልጣኑ የሚዲያ አሰራር ከተቀመጡት ደንቦች ጋር መጣጣሙን ተከታትሏል። የብሮድካስትና የፅሁፍ ሚዲያ የሚከታተል በአለምአቀፍ አሰልጣኞች የቀረበ ስልት የሚጠቀም አካል ተቋቁሞ ነበር። የብሮድካስት ባለስልጣኑ የነፃ አየር ጊዜ ድልድሉ የተከታተለና በተፎካካሪ ፓርቲዎቹ የቀረቡ አቤቱታዎች የቀረበ ነበር። እንደብሮድካስት ባለስልጣኑ ከሆነ ተፎካካሪ ፓርቲዎቹ ነፃ የአየር ጊዜያቸውን በከፊል ብቻ ነው የተጠቀሙት፤ በሬዲዮ ከተሰጣቸውን የአየር ጊዜ 53 በመቶ፣ የቴሌቪዥን 65 በመቶና ከጋዜጣ አምዶች 42 በመቶ ብቻ ነው የተጠቀሙት።

*ሐ. የሚዲያው የምርጫ ሽፋን መከታተል*

የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ በ*ኦሳሪዮ ዲ ፓቪያ* እና በአውሮፓ የሚዲያ ተቋም የተቀየሱ በአለምአቀፍ የአሰራር ደረጃ የብዛትና የጥራት ትንታኔ በመጠቀም ከሚያዝያ 13 እስከ ሰኔ 4 አንድ ናሙና የኢትዮጵያ ሚዲያ ተከታትለዋል። ናሙናው የመንግስት ብሮድካስት ሚዲያ ያካትታል፦ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን (ኢቴቪ 1)፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሬዲዮና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሬዲዮ ኤፍ.ኤም. አዲስ 97.1 እና ኤፍ.ኤም. 96.3፤ እንዲሁም የግል ብሮድካስት ሚዲያ፦ *ሬዲዮ ሸገር* እና አገር አቀፉ *ሬዲዮ ፋና*። ልዑኩ አስር ጋዜጦችም ተከታትለዋል፣ ሶስት የመንግስት (አዲስ ዘመንና የእንግሊዘኛው *ኢትዮጵያን ሔራልድ*፣ እንዲሁም በሳምንት ሁለት ጊዜ የሚታተመው አዲስ ልሳን)፣ እና ሰባት የግል ጋዜጦች (*ዘ ዴይሊ ምኒተር፣ ዘ ሪፖርተር፣* አውራ አምባ ታይምስ፣ አዲስ አድማስ፣ ኢትዮ-ቻናል፣ ሳምታዊ የንግድ ጋዜጦቹ *ፎርቹን* እና *ካፒታል*)።

ብዙ ክስተት ያልታየበት ምርጫ ቢሆንም እንኳ የኢትዮጵያ ሚዲያ በአጠቃላይ ምርጫ ነክ የሆኑ ፕሮግራሞችና ይዘት በማቅረብ ዋናዎቹ የፖለቲካ ቅስቀሳ ክስተቶች በመላ አገሪቱ ሽፋን ማግኘታቸውን አረጋግጠዋል። የግልም የመንግስት ሚዲያም ለየምርጫ ቦርዱ የመራጭ ስልጠና መልዕክቶች ያላቸውን ቁርጠኝነት አሳይተዋል። ይሁንና የህትመትና የብሮድካስት በአገሩ ያላቸው ውሱን ስርጭት መራጮች በምርጫ ቀን አገናዝበው ውሳኔ ለማድረግ የሚያስችላቸውን በቂ መረጃ ለሁሉም መራጮች የማቅረብ ብቃታቸውን ቀንሶታል። ክትትል በተደረገበት ጊዜ ሁሉ ሚዲያው፣ በተለይ የመንግስት ሚዲያው፣ እንደ የህዝብ ስራዎች መመረቅ ያሉ የመንግስት አባላት የሚሰሯቸው ዕለታዊ ስራዎች በመደበኝነት ሲዘግብ ነበር፣ ይህም ለገዢው የሚያደላ ሚዛኑን ያልጠበቀ ሽፋን አስከትሏል።
ባጠቃላይ፣ የመንግስት ሚዲያ ሚዛናዊ የሆነ ሽፋን በፕሮግራሙ ኣላቀረበም፣ በዋናነት በዜናዎቹ ላይ። በሚዛናዊ ሽፋኑ ላይ ጉልህ የሆነ መሻሻል በቅስቀሳው መጨረሻኛው ሳምንት ላይ ታይቷል። በኢቴቪ 1 ኢህአዴግ ከምርጫ ነክ ዜናዎች ውስጥ 58 በመቶ ሽፋን ያገኘ ሲሆን መድረክ 13 በመቶ አግኝቷል። በተመሳሳይ መልኩ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሬዲዮ ለገዢው ፓርቲ 60 በመቶ የአየር ጊዜ ሰጥቷል። ኢህአዴግ በኤፍ.ኤም. አዲስ 97.1 የነበረው ሽፋን ከአጠቃላዩ 68 በመቶ ሲሆን በኤፍ.ኤም. 96.3 72 በመቶ ነበር።

ይህ የሚዛን መጓደል በመንግስት የህትመት ሚዲያ ይበልጥ ተንፀባርቋል፣ ኢህአዴግ ከጠቅላላ ሽፋኖቻቸው የአዲስ ዘመን 70 በመቶ፣ *የኢትዮጵያን ሔራልድ* 77 በመቶና በአዲስ ልሳን 72 በመቶ አግኝቷል። የግል ጋዜጦች ትንሽ ሰፋ ያለ የፖለቲካ መድረክ የሸፈኑ ሲሆን ባጠቃላይ ለተለያዩ ፓርቲዎች የበለጠ ሚዛናዊ የሆነ ሽፋን አቅርበዋል። ይሁንና በሁሉም የግል ጋዜጦች የነበረው ትኩረት በገዢው ፓርቲና በአንዳንድ ዋና የተቃዋሚ ፓርቲዎችና ጥምረቶች ላይ የነበረ ነው፦ መድረክ፣ መኢአድና ኢዴፓ። ለአናሳ ፓርቲዎች የተሰጠው ሽፋን ችላ የሚባል ነው።
ምንም እንኳ የመንግስት ሚዲያዎች ለኢህአዴግና መንግስት ነክ ስራዎች ሰፊ ሽፋን የሰጡ ቢሆኑም፣ በምርጫ ነክ ዘገባዎቻቸው ገለልተኛ የሆነ ድምጽ ነው የነበራቸው። በተመሳሳይም ምርጫውን የሚዘግቡ የግል ሚዲያዎች አዘጋገብም ገለልተኛ ነበር።

---

[18] የአየር ጊዜው በሁለት ዙር ነው የተከፋፈለው። የአጠቃላይ አየር ጊዜ 25 በመቶ በሁሉም ተፎካካሪ ፓርቲዎች በእኩልነት የተከፋፈለ ነው፣ 55 በመቶ በህዝብ ተወካዮችና በክልል ምክር ቤቶች ባላቸው መቀመጫ ብዛት የተከፋፈለና ቀሪው 20 በመቶ እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ባስመዘገበው የአጩዎች ብዛት ነው።

ከቅስቀሳ ነፃ በሆነው የ48 ሰዐቱ ጊዜ ውስጥ አነስ ያለ ብዛት ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ሰላማዊ ምርጫ የማካሄድ መልዕክቶቻቸው በኢቴቪ 1 እና በኢትዮጵያ ሬዲዮ አማካኝነት ለማስተላለፍ ችለዋል። በተጨማሪም የቅስቀሳ ሪፖርቶች የተላለፉና ጥቂት የፓርቲ ተወካዮችም በሚዲያ ቀርበዋል። በዚህ ከቅስቀሳ ነፃ በሆነ ጊዜ የሚዲያ ድርሻ የሚመለከት ግልፅ የሆኑ ደንቦች የሉም። ይሁንና ውሱን ተፎካካሪ ፓርቲዎች ለሽፋን መምረጥ በኢትዮጵያ የሚዲያ ህጎች ደንቦች ከሚፈለገው የሚዛናዊ ሽፋን መርህ ጋር የሚጋጭ ነው። በተጨማሪም መራጮች ወደ ድምፅ መስጫዎች ከመሄዳቸው በፊት ባደረጓቸው ውሳኔዎቻቸው ላይ እንዲያስቡበት ከምርጫ ቀን በፊት የሚዲያ ዝምታ መኖር በአለምአቀፍ ደረጃ እንደአዎንታዊ እርምጃ ተደርጎ የሚወሰድ ነው።

የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ የመጀመሪያ መግለጫ በመንግስት ሚዲያ የተሰጠው ሽፋን ሚዛናዊ አልነበረም፣ አዎንታዊ ገፅታዎቹ ብቻ እያሳዩ በምርጫ ሂደቱ ላይ የነበረ ማንኛውም ትችት ችላ የተባለበት ነበር። ሚዲያው በምርጫ ሂደቱ ሚዛናዊ ዘገባ እንዲኖር ከሚያዘው የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሀን ስነምግባር ደንብ በሚፃረር መልኩ የመንግስት ሚዲያ የኢትዮጵያ ህዝብ በምርጫው ሂደት ሙሉና ሚዛናዊ መረጃ የማግኘት መብቱን ነፍጎታል። የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ ዋና ታዛቢ በመጀመሪያ መግለጫው ላይ እጅግ አዳላይ በሆነው ዘገባ የተቃወመበት ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት አዘጋጅ ደብዳቤ ፅፎ ምላሽ ተሰጥቶበትም አያውቅም፣ በመንግስት ሚዲያም አልተለቀቀም። አንዳንድ የግል ሚዲያዎች ብቻ ናቸው ደብዳቤውን ይዘው የወጡት።

## X. ሰብዓዊ መብቶችና የሴቶች ተሳትፎ

### *ሀ. የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ*

የፖለቲካዊ መብቶች መጠበቅና የመሰረታዊ ነፃነቶች መከበር የመምረጥና የመመረጥ መብቶች በሚገባ ለመጠቀም የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች ናቸው።[19] የኢትዮጵያ ህገ መንግስት በኢትዮጵያ የፀደቁ በአለምአቀፍ ደረጃ አስገዳጅነት ያላቸው የሰብዓዊ መብት ግዴታዎች ውስጥ ለተጠቀሱት መሰረታዊ የሲቪልና ፖለቲካዊ መብቶች እንዲከበሩ ያዛል።[20] ከዚህ በተጨማሪ የተወሰኑ የቅርብ ጊዜ ህጎች፡- የፀረ ሽብር ህግ፣ የመገናኛ ብዙሀን ነፃነትና የመረጃ ተደራሽነት ህግ፣ እንዲሁም የበጎ አድራጎትና የማህበራት ህግ ጨምሮ በተለምዶ ከሚቀመጡት እንደብሔራዊ ደህንነት፣ የድንበር መከበር፣ የህዝብ ደህንነት፣ ጤናና ስነ ምግባር ካሉ የፖለቲካ ነፃነቶች ላይ ከሚቀመጡት ገደቦች ባሻገር ላሉት መሰረታዊ ነፃነቶች በሚገባ መጠቀም መቻሉ ላይ ስጋቶች ያስነሳል።
የኢትዮጵያ መንግስት ባለፉት ጥቂት አመታት ከልማት፣ በተለይ የ"አብዮታዊ ልማታዊ ዲሞክራሲ" ስትራቴጂውን በጠበቀ መልኩ የመሰረተ ልማት ስራዎች አንጻር የህዝቡ መሰረታዊ መብቶች በማሳደግ ረገድ ጉልህ የሆኑ ውጤቶች አስመዝግቧል። ይሄ ስትራቴጂ የኢትዮጵያ ልማት ወደ መካከለኛ ገቢ አገር እንዲያድግ ለማረጋገጥ ገዢው ከ20 እስከ 30 አመት በስልጣን ላይ እንዲቆይ ያዛል።[21] መንግስት የላቀ ትኩረት የሰጠው እንደ ዋነኛው መሰረታዊ ሰብዓዊ መብት ለጋራ ልማት ነው፤ ይሄ የግለሰብ ሲቪልና ፖለቲካዊ መብቶች እንዲንሰራሩ ከመፈቀዱ በፊት መረጋገጥ ያለበት ነው።

የመዘዋወር፣ የመሰብሰብና ሐሳብ የመግለጽ መብቶች በቅርቡ የምርጫ ሂደት ሁልጊዜ አልተከበሩም። አዲሱ የፀረ ሽብር ህግ፣ በዚህ ጊዜ ባይተገበርም እንኳ፣ ለአካባቢያዊ አስተዳደሮችና ለፀጥታ ሀይሎች ሰፊ ስልጣን ይሰጣል። ይሄ ከሌሎች እንደ በፖሊስና ፍትህ አካላት ገለልተኝነት ላይ እምነት አለመኖር ካሉ ሁኔታዎች ጋር ተደምሮ በብዙ የተቃዋሚ እጩዎች ደጋፊዎች የተነገረውን በአገር ውስጥ፣ በተለይ በገጠራማ አካባቢዎች፣ ለነበረውን የፍርሀትና የጥርጣሬ ድባብ የራሱ አስተዋፅኦ አበርክቷል። ለነገሩ ከተደረገው ተደጋጋሚ የሰላማዊ ምርጫ ጥሪዎች ባሻገር ባለስልጣኖቹ እንደ በቅስቀሳ ጊዜ የእጩዎች ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ ነፃነትና ለሁሉም እጩዎች በእኩል ሁኔታዎች ቅስቀሳ የማካሄድ መብት ማረጋገጥ ያሉ ስጋቶች ለመቅረፍ አዎንታዊ እርምጃዎች መውሰድ አልቻሉም።

ምንም እንኳ የምርጫ ህጉ ሰልፎች ቀድሞ ማሳወቅ እንጂ ከአካባቢው ባለስልጣናት ፍቃድ እንደማያስፈልጋቸው በግልፅ ቢያስቀምጥም በተግባር የታየው እጩዎች ባብዛኛው ከአካባቢ ባለስልጣናት ፍቃድ ማግኘት ይፈለግባቸው ነበር፣ ይህንን ካላደረጉ እስራት ይጠብቃቸው ነበር። የአውሮፓ ህብረት ምርጫ ታዛቢ ልዑክ 27 የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ያለፍቃድ ቅስቀሳ አካሂደው ስለታሰሩበት መረጃ ደርሶታል።[22] በተጨማሪም የእጩ ተወዳዳሪዎች አለመደፈር መብት ተጥሶ ስድስት የተቃዋሚ እጩዎች የታሰሩበት ሪፖርቶች ለአውሮፓ ህብረት ምርጫ ታዛቢ ልዑክ ደርሶታል። በተመሳሳይ መልኩ በብዙ የአገሪቱ ክፍሎች የተቃዋሚ እጩዎች ተወዳዳሪዎች፣ የደጋፊዎች ወይም የተወካዮች መታሰር ለልዑኩ መረጃ ደርሶታል።

ቀበሌዎቹ እንደ ምግብ እርዳታ ማከፋፈል ያሉ የስር መሰረታዊ አገልግሎቶች የማቅረብ ኃላፊነት አለባቸው። ይህና በአገሪቱ ያለውን ሰፊ የሎጂስቲክስ ችግር በሩቁ የአገሪቱ ክፍሎች የመንግስት ብቸኛ ተወካይ ያደርጋቸዋል። ገዢው ፓርቲ እስከ እያንዳንዱ ቤተሰብ ድረስ የሚዘልቀው የቀበሌ ስርዐት ላይ ያለው ቁጥጥር የመንግስትን ልማታዊ ስትራቴጂ ለመተግበር ተሰርቶበታል። ይህ እንዳለ ሆኖ የአውሮፓ ህብረት ምርጫ ታዛቢ ልዑክ በሂደቱ ገለልተኝነት ላይ ያለው እምነት ለማሳደግና ለሁሉም ፖለቲካ ፓርቲዎች የበለጠ እኩል የሆነ የመጫወቻ ሜዳ እንዲኖር ሲባል በምርጫዎች አደረጃጀትና አፈፃፀም ያላቸውን ሚና ቀስ እያለ እንዲቀነስ ይመክራል።

### *ለ. የሴቶች ተሳትፎ*

---

[19] ICCPR፣ የተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን፣ አጠቃላይ አስተያየት ቁጥር 25፣ አንቀፅ 12፣ "ሐሳብ የመግለፅ፣ የመሰብሰብና የመደራጀት ነፃነት የመምረጥ መብት በሚገባ ለመጠቀም የሚያስፈልጉ መሰረታዊ ሁኔታዎችና በሙሉ መጠበቅ ያለባቸው ናቸው።"

[20] የኢትዮጵያ ህገ መንግስት አንቀጽ 13 የአለምአቀፍ ሰብዓዊ መብቶች ህግጋት (1941) እና ሌሎች የሰብዓዊ መብቶች ሰነዶች በህገ መንግስቱ ለተጠቀሱት መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ለመተርጎም እንደመሰረት ሆነው እንደሚያገለግሉ በግልፅ ይጠቅሳል። አንዳንድ ዋና ሰነዶቹ *ክፍል 4. ህጋዊና የምርጫ መዋቅር፣ ቢ. ሁለንተናዊና ክልላዊ ግዴታዎች* ተጠቅሰዋል። ኢትዮጵያ የ1968ቱ የአለምአቀፍ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ስምምነት፣ እና ሌሎች ክልላዊና አለምአቀፋዊ የሰብዓዊ መብቶች ሰነዶችም ፈርማለች።

[21] "ልማታዊ አገር" የሚለው መፈክር መጀመሪያ ጥቅም ላይ የዋለው በ2000 ኢ.ም. "ብሔራዊ ተግዳሮቶች፣ ቀጣይ ተግዳሮቶችና የአብዮታዊ ዲሞክራዊያዊ መፍትሔዎች" በሚል ያልታወቀ ህትመት ነው። ከተከታታይ ህትመቶች ሶስተኛው ነበር፣ ቀዳሚዎቹ "ልማት፣ ዲሞክራሲና አብዮት" (ጥቅምት 2000 ኢ.ም.) እና "የአብዮታዊ ዲሞክራሲ ዲሞክራሲያዊ ስርዐት የመገንባት ትግል" (መጋቢት 1999 ኢ.ም.) ናቸው።

[22] ቢያንስ በአንድ ጉዳይ ላይ በቶንጎ (ቤኒንሻንጉል-ጉሙዝ) ይሄ በሚፃፍበት ወቅት የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ስነ ስርዐት በአንቀጽ 63-75 ላይ የሰፈሩት መርሆች በሚፃረር መልኩ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ያለዋስ እንደታሰሩ ነበሩ።

የኢትዮጵያ ህገ መንግስት የፆታ እኩልነት የሚያረጋግጥና በፆታ ላይ የተመሰረት አድሎ የሚከለክል ነው። የምርጫ ህግና ሌሎች ከምርጫ ጋር የተገናኙ ደንቦች በፖለቲካው መስክ ያለውን የሴቶች ተሳትፎ ለማሳደግ ያለሙ ናቸው። ይሁንና ሴቶች በኢትዮጵያ የፖለቲካና የህዝባዊ መስክ ላይ ያላቸውን ተሳትፎ አሁንም አነስተኛ ነው፣ ባለፉት አሰርት አመታት የተወሰነ መሻሻሎች ቢታዩም እንኳ። እንደ ምርጫ ቦርድ ተመን ከሆነ ከተመዘገቡት ተመዝጋቢዎች የሴቶች ብዛት ከስነ ህዝባዊ ብዛታቸው ትንሽ አነስ ብሎ 47.8 በመቶ ናቸው። ይሁንና የምርጫ ቦርድ በ2002 አ.ም. ከነበሩት 2,188 የህዝብ ተወካዮች እጩ ተወዳዳሪዎች 12.4 በመቶ፣ ከተለያዩ የክልል ምክር ቤት 4,746 እጩዎች ደግሞ 15.3 በመቶ ብቻ ሴቶች እንደነበሩ አመልክቷል። በምርጫ አስተዳደር የነበረው የሴቶች ተሳትፎ በዚሁ ልክ የተገደበ ነበር፣ ምንም እንኳ በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ የነበሩት የሰው ሀይል ውስጥ በጣም ቢበልጡም። በምርጫ ቀን ሴቶች ከምርጫ ጣቢያ ኮሚቴዎች ውስጥ 28 በመቶ ሴቶች ነበሩ፣ ምንም እንኳ የአውሮፓ ህብረት ምርጫ ታዛቢ ልዑክ ከታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ በሴቶች የተመሩ ኮሚቴዎች 11 በመቶ ብቻ ቢሆኑም። ከተመዘገቡት 15,252,240 ሴት መራጮች ውስጥ 93.2 በመቶ ድማፃቸውን በምርጫ ቀን ሰጥተዋል፣ ይህም 93.7 በመቶ ከነበረው የወንዶች ተሳትፎ ጋር በጣም የተቀራረበ ነው።

በሁለቱም በፖለቲካ ፓርቲዎችም፣ በተለይ 30 በመቶ የሴት እጩዎች ኮታ በመደበው ኢህአዴግ፣ እና ግን በምርጫ ቦርድም ሴቶች በፖለቲካው መስክ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ እርምጃዎች ተወስደዋል። ለፖለቲካ ቅስቀሳው ከሚሰጠው ድጎማ ውስጥ ለሴቶች የበለጠ ድርሻ እንዲሰጥ መደረጉ አዎንታዊ እርምጃ ነው፣ ምንም እንኳ የበለጠ የሴት እጩ ተወዳዳሪዎች ባያመጣም። እንዲያውም፣ ከ1997ቱ ምርጫ ከነበሩት የህዝብ ተወካዮች 15 በመቶና የክልል ምክር ቤት 23 በመቶ እጩ ሴት ተወዳዳሪዎች አንፃር ሲታይ ቁጥራቸው ቀንሰዋል። የጎሉ ክልላዊ ልዩነቶችም መቀረፍ አለባቸው። በ2002 ምርጫ በቤኒንሻንጉል የነበረው የሴት እጩ ተወዳዳሪዎች 8 በመቶ ብቻ ሲሆን በአዲስ አበባ ወደ 20 በመቶ አድጎ ነበር።

## XI. የሲቪል ማህበራትና የአገር ውስጥ ምርጫ ታዛቢዎች ተሳትፎ

የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት በምርጫው ሂደት ላይ የነበራቸው ተሳትፎ በወጣው የኢትዮጵያ በጎ አድራጎትና ሲቪል ማህበራት አዋጅ ምክንያት እጅግ በጣም ተገድቧል። በዚህ ህግ መሰረት ማንኛውም የድጎማውን 10 በመቶ በላይ ከውጭ ምንጮች የሚቀበል ድርጅት የአገር ውስጥ ድርጅት ተብሎ ሊቆጠር አይችልም። በተጨማሪም የአገር ውስጥ ድርጅቶች ብቻ ናቸው በሰብዓዊ መብቶችና በዲሞክራሲ ዙሪያ መስራት የሚችሉት። የዚህ አዋጅ መውጣትና የሁሉም አገር ውስጥ ድርጅቶች በድጋሚ መመዝገብ ማስፈለጉ ብዙ የአገር ውስጥ ድርጅቶች ትኩረት ከሰብዓዊ መብቶችና ዲሞክራሲ ቀይረው ወደ የልማት ፕሮጀክቶች እንዲያዞሩ አድርጓቸዋል። አዋጁ የኢትዮጵያ መንግስት ለውጭ ጣልቃ ገብነት ቦታ ከሌለበት ሰብዓዊ መብቶች የአገር ጉዳዮች ናቸው ብሎ በተደጋጋሚ ከተናገረው ጋር አብሮ የሚጓዝ ነው። የአውሮፓ ህብረት ምርጫ ታዛቢ ልዑክ ህጉ የሚያስቀምጠው ሁኔታዎች ከመሰብሰብ ነጻነት ጋር የሚፃረሩና በሰብዓዊ መብትና ዲሞክራዊ ዙሪያ ለሚሰሩ የአገር ውስጥ የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች የሚጎዳ ነው ብሎ ያምናል።

ከላይ እንደተጠቀሰው የምርጫ ቦርድ ሁሉም የመራጮች ስልጠና በራሱ ለማካሄድ በመወሰኑ የሲቪል ማህበራቱ በመራጭ ስልጠና ላይ ምንም ሚና አልተጫወቱም። የሲቪል ማህበራት ድርጅቶች በረጅም ጊዜ ውስጥ ሊኖራቸው ከሚችለው አዎንታዊ ተፅዕኖ አንፃር ይህ ያልተፈለገ አጋጣሚ ነው። በተመሳሳይ መልኩ በአዲሱ ህግ መሰረት የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ቡድን መሆን ለመቻል እንደሲቪል ማህበር ድርጅት ሆኖ መመዝገብ ላይ ይወሰናል። በዚህም ምክንያት በአገር ውስጥ በምርጫ መታዘብ ስራዎች ላይ ሊሳተፉ ይችሉ የነበሩ የድርጅቶች ቁጥር ብዛት ቀንሶታል። ምንም እንኳ ህጉ የምርጫ ቦርድ ውሳኔዎችን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማለት ቢያስችላቸውም፣ የምርጫ ታዛቢነት ፍቃድ፣ የሲቪክና የመራጭ ስልጠና ወይም የምርጫ ሂደቱን የሚሸፍኑ ጋዜጠኞች በተመለከተ የተሰጡ የምርጫ ቦርድ ውሳኔዎች ይግባኝ የማይባሉ ናቸው።[23]

ትልቁ የአገር ውስጥ ምርጫ ታዛቢ ቡድን የነበረው በዛ ካሉ የተለያዩ ድርጅቶች የተዋቀረው የኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ጥምረት የምርጫ ታዛቢ ሲሆን ከነኚህ ውስጥም ዋነኛው አባል የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ነበር።[24] ጥምረቱ በመላው የአገሪቱ ክልሎች 40,000 ታዛቢዎች ለመላክ ያለመ ሲሆን፣ ምንም እንኳ ይሄ ቁጥር ማሳካቱ አጣራጣሪ ቢሆንም የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ ከታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ በዛ ባሉት ውስጥ የጥምረቱ ታዛቢዎች ታይተዋል። ጥምረቱ በግንቦት 16 የምርጫው ሂደት ግምገማው ያቀረበ ሲሆን ስለየትኛውም የሂደቱ ክፍሎች ትንሽ ዝርዝር ነው የሰጠው። ስለጥምረቱ ቴክኒካዊ ብቃትና ወሳኝ ግምገማዎች ስለማካሄድ ነፃነቱ ትንሽ ማስረጃ ነው የነበረው።

ሌሎች እውቅና የተሰጣቸው የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ቡድኖች የእስልምና ጠቅላይ ምክር ቤት፣ የደርግ ተጠቂ ቤተሰቦች ማህበርና የእግር ኳስ ዳኞች ማህበር ያካትታሉ፣ ነገር ግን እነኚህ ለምርጫው ሂደት የሚጨበጥ አስተዋፅኦ አላበረከቱም።

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽንም (ኢሰመኮ) ምርጫውን ታዝቦታል፣ የቅድመ ምርጫው ድባብ የገመገመና በምርጫ ቀን ወደ 100 ታዛቢዎች መላኩ ተብሏሌ። ኢሰመኮ የምርጫ ሂደቱን መታዘብ ህገ መንግስታዊ መብቴ ነው በማለት ከምርጫ ቦርድ እውቅና አልጠየቀም። ኢሰመኮ የምርጫ ትዝብት ውጤታቸው በተመለከተ መግለጫ አውጥተዋል።

## XII. የአለምአቀፍ ምርጫ መታዘብ

የኢትዮጵያ መንግስት የ2002 ምርጫ እንዲታዘቡ ለአውሮፓ ህብረት፣ ለአፍሪካ ህብረትና ለካርተር ማዕከል ጥሪ ልኮላቸዋል። የካርተር ማዕከል ጥሪውን አልተቀበለም። የአፍሪካ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ ምርጫውን ለመታዘብ ከግንቦት 8 እስከ 20 እስኪመጣ ድረስ የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ ብቸኛው አለምአቀፍ የምርጫ ታዛቢ ልዑክ ነበር። የአፍሪካ ህብረት በእያንዳንዱ የአገሪቱ ክልል 59 ታዛቢዎች የላከና በግንቦት 18 መግለጫ የሰጠ ነው።

---

[23] የ1997 ምርጫ ላይ የምርጫ ቦርድ የተወሰኑ የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ቡድኖች ምርጫውን እንታይታዘቡ ብሎ ያገደበትን ውሳኔ ፍርድ ቤቶቹ ቀልብሰውታል።

[24] የጥምረቱ አባላት የኢትዮጵያ አሰሪዎች ማህበር፣ የኢትዮጵያ ሰራተኞች ማህበራት ኮንፌዴሬሽን፣ የኢትዮጵያ ሴት ነጋዴዎች ማህበር፣ የጥንታዊት ኢትዮጵያ አርበኞች ማህበር፣ የኢትዮጵያ ህዳሴ ማህበር፣ የኢትዮጵያ ወጣቶች ፌዴሬሽን፣ የኢትዮጵያ ሴቶች ፌዴሬሽን፣ የኢትዮጵያ አስጎብኚዎች ማህበር፣ የኢትዮጵያ ጠበቆች ማህበር፣ የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች ማህበርና የኢትዮጵያ ጠበቆች ማህበራት ህብረት ያካትታል።

የኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ከዲፕሎማሲያዊ ልዑኮች የሚመጡ የታዛቢ ቡድኖች ምርጫ የመታዘብ ስራዎች ለማከናወን የሚያስፈልገው ስልጠና ስለሌላቸው እና እንዲህ ያሉ ተግባራት ዲፕሎማ እንደመሆናቸው ከሚኖራቸው ስልጣን ውጭ ነው በማለት የአሜሪካ ኤምባሲ በምርጫ ቀን ታዛቢዎች ለማሰማራት ያቀረበውን ጥያቄ አልተቀበለውም። ዲፕሎማቶች በ2002 ምርጫ እንዳይታዘቡ ከተጣለው እገዳ በተያያዘ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሪ በአዲስ አበባ ያለው የአለምአቀፍ ማህበረሰብ ከአዲስ አበባ ውጭ ስለሚኖራቸው ማንኛውም የጉዞ እቅድ አስቀድሞ እንዲያሳውቁት ጠይቋቸዋል። ይህ እርምጃ መጀመሪያ ከግንቦት 2 እስከ ሰኔ 3 ተፈፃሚ እንዲሆን ነበር የታሰበው፣ ግን ከምርጫው ቀን አንድ ቀን በኋላ በግንቦት 16 ተነስቷል።

## XIII. ቅሬታዎች እና አቤቱታዎች

ምርጫ ነክ አቤቱታዎች የሚቀርብባቸው መንገዶች ቅር ለተሰኙ ወገኖች ጊዜውን የጠበቀ መፍትሔ እንዲገኝ ያስቻሉና የ1997 ምርጫ ካስተዳደረው መዋቅር አንፃር ከተደረጉ ጉልህ መሻሻሎች አንዱ ነበሩ። ይሁንና በተግባር ሲታይ አቤቱታ በሚቀርቡባቸው 3ቱም መንገዶች ገለልተኝነት ላይ እምነት አለመኖርና የተጋራው ጉዳይ የማየት ስልጣን፣ በተለይ በምርጫ ወንጀሎች ጉዳይ፣ አጥፊዎች ባብዛኛው ለጥፋታቸው የማይጠየቁበት ሁኔታ ነው የፈጠረው። ልዑኩ የአካባቢ ምርጫ ባለስልጣናትና ፖሊስ አቤቱታዎች ለታዛቢዎቹ ለመስጠት ፍቃደኛ አለመሆን ታዝቧል። በአንዳንድ አካባቢዎች ልዑኩ መቀበላቸውንና በኦፊሴላዊ መልኩ በፋይል ውስጥ ማስቀመጣቸውን የሚያውቅ አቤቱታዎችን አልተቀበልንም በማለት ክደዋል። በተጨማሪም የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ ታዛቢዎች የአካባቢ ፖሊሶች ከገዢው ፓርቲ ጋር እንደወገኑ ሆነው አይተዋቸዋል። ስለዚህ በብዙ አጋጣሚዎች ውጤታማ መፍትሔ የማግኘት መብት፣ የሂደቱ ግልፅነትና እውነተኛ ተፈጥሮው ለአደጋ የመጋለጥ እድል አጋጥሟቸዋል።

ከምርጫ ጋር ለተያያዙ አቤቱታዎች ሶስት አካላት ናቸው ኃላፊነት የነበራቸው፦ የፍትህ አካላት፤ የምርጫ ቦርድ በብሔራዊ ደረጃና እንዲሁም በምርጫ ጣቢያ፣ በክልልና በምርጫ ክልል ደረጃ ያሉ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች፤ እና የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት።

### *ሀ. የፍትህ አካላት*

የኢትዮጵያ ፍትህ አካል በህገ መንግስቱ መሰረት ከሌሎቹ የመንግስት አካል ነፃ የሆነና የምርጫ ወንጀሎች የሚመለከቱ አቤቱታዎች ወይም በምርጫ ባለስልጣናት የተሰጡ የውሳኔዎች ይግባኝ ወይም በነሱ የተመሩ ውሳኔዎች የመስማት ብቃት ያለው ነው። በክልል ደረጃ ያሉ የፍትህ አካላትና አቃቤ ህጎች የምርጫ ወንጀሎች የሚሸፍኑ የምርጫ ፍርድ ሂደቶች፣ የተዛመዱ ስርዐቶችና የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ስነ ምግባር ደንብ ላይ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል። ለምርጫ ነክ ጉዳዮች ቅድሚያ የተሰጣቸውና በእያንዳንዱ ፍርድ ቤት ለዚህ አንድ ዳኛ የተመደበ ነበር።[25]

ይሁንና በኢትዮጵያ ውስጥ በፍትህ አካላት ገለልተኝነት ላይ ትንሽ እምነት ነው የነበረው፣ በተለይ የፍትህ አካላቱ በገዢው ፓርቲ የሚመሩ መሆናቸውን የማያምኑና በዚህም ወደ ፍርድ ቤትም ለመሄድ ፍላጎት ባልነበራቸው በተቃዋሚ ፓርቲዎች ዘንድ። ለአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ እንዲያውቅ እንደተደረገው እንዲያውም ስር የሰደደ ወደ ፍርድ ያለመሄድ አዝማሚያ ነው ያለው። አጅግ በአብዛኛው ጉዳዮች ውስጥ የተከተሉት ምርመራዎች ክሶቹን ለማጠናከር በቂ ማስረጃ አላቀረቡም።
ፖሊስና የአካባቢ ታጣቂዎች የጥሰቶች ፈፃሚዎች መባላቸው የምርመራቸው ተአማኒነት ገድቦታል። በተመሳሳይ መልኩ ምስክሮች አቤቱታ ካቀረቡ ፓርቲዎች መቅረብ እንደአለመቻላቸውና የአካባቢ ህዝቦች በማንኛውም የፖለቲካ ጉዳይ ላይ መሳተፍ ላይ ያላቸው አጠቃላይ የፍርሀት ስሜት ማስረጃ የማግኘቱ እድል ቀንሰውታል። በብዙ ክልሎች የተቃዋሚ ፓርቲ አባሎች ላይ ተከሰተ የተባሉት አካላዊ ጉዳቶች የሚያጠናክር የህክምና ሪፖርቶች የሆስፒታል ባለስልጣናት እንዳልለቀቁ ለአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ ሪፖርቶች ደርሶታል።

ፍርድ ቤቶች ጉዳዮችን የሚፈቱበት ፍጥነት ባብዛኛው ለህግ ሂደት የመከበር መርህና በትክክል ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት በበቂ ሁኔታ ለመከበሩ ጥርጣሬ ያስነሳል። በብዙ ጉዳዮች ላይ የቅስቀሳ ቁሳቁስ በማጥፋት የተከሰሱና የህግ ምክር አገልግሎት የሌላቸው ሰዎች በቂ ጊዜ ሳይኖር ወይም መከላከያቸው የማዘጋጀት ዕድል ሳይኖራቸው በሁለት ቀናት ውስጥ እስከ አስር ወር እስራት ተፈርዶባቸዋል።[26] ይሁንና ተቃዋሚዎች ባቀረቡት ቢያንስ በአራት ጉዳዮች ላይ የፍትህ አካላቱ የበለጠ ፈዘዝ ማለታቸውና መንቀራፈፋቸው አሳዛኝ አጋጣሚ ነው።

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ የቀረቡለትን አራት የምርጫ ቦርድ እና የቅሬታ ሠሚው ኮሚቴ ውሣኔዎችን አፅድቋል። የእነ ዚህ ከምርጫው በፊት የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ልኡክ እንዲያውቃቸው የተደረጉ ብቸኛዎቹ ይግባኞች መሆናቸው በምርጫው ወቅት የነበረውን ወደ ፍርድ ቤት የመሄድ አዝማሚያ የተገደበ እንደነበር ያሣያል።

### *ለ. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ (ኢብምቦ) እና ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች*

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መዋቅር አካል የሆኑ የቅሬታ ሠሚ ኮሚቴዎች በክልል፣ በምርጫ ክልል እና በምርጫ ጣቢያ ደረጃ መቋቋም ነበረባቸው። ነገር ግን ብዙ የቅሬታ ሠሚ ኮሚቴዎች ካለመቋቋማቸው የተነሣ ውሣኔዎች የሚሠጡት በምርጫ ክልል የምርጫ አስፈፃሚዎች ነበር። እነ ዚህ ኮሚቴዎች ሦስት አባላት ያሏቸው፡ አንዱ አካባቢው የምርጫ ፅ/ቤት ሀላፊ ሲሆን ሁለቱ ደግሞ የህዝብ ታዛቢዎች ናቸው። በህዝብ ታዛቢዎች የህግ እውቀት አለመኖር እና

---

[25] ኢትዮጵያ የፌዴራል ፍትህ አካላት ከእያንዳንዱ የክልል ፍትህ አካላት ጎን ለጎን የሚኖርበት ድርብ የፍርድ ቤት ስርዐት አለው። የፌዴራል ፍትህ አካላት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ያጠቃልላል። የእያንዳንዱ ክልል ፍትህ አካላት በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚመራና የክልል ፍርድ ቤትና የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ወይም የወረዳ ፍርድ ቤቶች የሚያጠቃልል ተመሳሳይ አወቃቀር ነው ያለው።

[26] ከኢትያጵያ ህገ መንግስት አንቀጽ 20፣ ከአፍሪካ ሰብዓዊና የሰዎች መብት ኮሚሽን አንቀጽ 7 እና ከአለምአቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት አንቀጽ14 ጋር የሚጋጭ።

ማንስ በቅሬታ ሠሚ ኮሚቴዎቹ በሚቋቋመበት ጊዜ የተስተዋለ ችግር ነበር። ለወደፊት ምርጫዎች የምርጫ አስተዳደሩን የቅሬታ አፈታት ስነ ስርዓት ተአማኒነት ለማረጋገጥ ይህ ችግር መፈታት አለበት።

የቅሬታ ሠሚ ኮሚቴዎቹ የመራጮች ምዝገባን፣ የእጩ ተወዳዳሪዎች ምዝገባን፣ ምርጫን፣ የደመፅ አሰጣጥንና ውጤቶቹን በተመለከተ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ይመለከታል። የምርጫ ሂደቱን በተመለከተ የሚቀርቡ ቅሬታዎች ወዲያው ቅሬታው እንደቀረበ ውሣኔ እንዲሠጥባቸው ለምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሠሚ ኮሚቴ መቅረብ አለባቸው። ከድምፅ ቆጠራና ከውጤቶች ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች ለምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሠሚ ኮሚቴና በምርጫ ክልል ደረጃ ባለ የቅሬታ ሠሚ ኮሚቴ ከምርጫው ቀን በኋላ ባሉት 48 ሠዓታት ውስጥ ሊቀርቡ ይችላሉ። የምርጫ ጣቢያው ቅሬታ ሠሚ ኮሚቴ ቅሬታዎችን አልቀበልም በሚልበት ወቅት ምንም እንኳን ይህን የተመለከተ የህግ ድንጋጌ ባይኖርም አቤቱታዎቹ በምርጫ ክልል ደረጃ ላለ የቅሬታ ሠሚ ኮሚቴ ሊቀርቡ ይችላሉ። የምርጫ ክልል ደረጃ የተሠጡ ውሣኔዎች ለምርጫ ቦርድ ይግባኝ ሊባልባቸው ይችላል። የምርጫ ቦርድ ውሣኔዎች ደግሞ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊባልባቸው ይችላል። ይህ አይነቱ የይግባኝ አወቃቀር ከጉዳዩ ጋር ከሚያያዙ አለምአቀፍ ስምምነቶች ጋር አብሮ ይሄዳል።[27]

የምርጫ ቦርድ ከምርጫው ቀን በፊት ከበታቹ ባሉ አካላት ቀርበው የነበሩና ከእጩ ተወዳዳሪዎች ምዝገባ፣ ከቅስቀሣ ጋር የተያያዙ ችግሮች፣ ማስፈራራቶችና የምርጫ ቅስቀሣዎችን ማወክ ጋር የተያያዙ ወደ 62 አቤቱታዎችን ተቀብሏል። ይህ በብሔራዊ ደረጃ ወደተቋቋመው አካል ማዘንበል የሚያሳየው ተቃዋሚ ፓርቲዎች በዝቅተኛ ደረጃ በተቋቋሙት የምርጫ አስተዳደሮችና በቅሬታ ሠሚ ኮሚቴዎች ውስጥ የታጩ የህዝብ ታዛቢዎች ነፃና ገለልተኛ መሆን ላይ ያላቸው መተማመን አነስተኛ መሆኑን ነው። የምርጫ ቦርዱ ውሣኔዎች በቂ እርምጃዎችን በመውሰድ አቤቱታዎቹ መሠረት ያላቸው የሚመስል ከሆነ በአወቃቀሩ ከበታች ላሉ አካላት በሚፈለግበት ጊዜ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎች እንዲወስዱ መመርያ ሠጥቷል።

ከምርጫ ቀን በፊት የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑካን እንደጠቆሙት በምርጫ ክልልና በክልል ደረጃ ያሉ የምርጫ ቦርድ ፅ/ቤቶች በትንሹ 223 ቅሬታዎችን ተቀብለዋል። እነዚህ ቅሬታዎች በሚመለከታቸው የቅሬታ ሠሚ ኮሚቴዎች መፈታት የነበረባቸው ቢሆንም ከላይ እንደተጠቀሰው አብዛኛዎቹ ውሣኔ የተሠጠባቸው በምርጫ አስፈፃሚዎች ነበር። አብዛኛዎቹ ቅሬታዎች ከምርጫ ቅስቀሳ ማደናቀፍ ጋር የተያያዙ ናቸው (115 ቅሬታዎች) ሌሎቹ ደግሞ እጩዎችንና ደጋፊዎችን ከማስፈራራት፣ ማንገላታትና ጥቃት ጋር የተያያዙ ናቸው (50 ቅሬታዎች)። ቀሪዎቹ የምርጫ አስፈፃሚዎችና የህዝብ ታዛቢዎች ገለልተኛ አለመሆን እና የመንግስት ሠራተኞች ለምርጫ ቅስቀሣ ለሚሆናቸው ጊዜ የስራ ፈቃድ አለማግኘት ጋር የሚገናኙ ሲሆን ሌሎች 13 ቅሬታዎች ደግሞ ከመሬት፣ ከምግብ እርዳታ፣ የፓለቲካ ፓርቲ ደጋፊዎችና እጩዎች ከስራ ቦታቸው መቀየር እና ስድስት ህገወጥ እስራቶችን ይጨምራሉ። በአጠቃላይ በሽምግልና ጉዳዩን ለመፍታት በመሞከር ወይንም ለፖሊስ ወይም የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በማስተላለፍ ወደ 90 የሚሆኑ ውሣኔዎች ተሠጥተዋል።

በምርጫው ቀን በአውሮፓ ህብረት ምርጫ ታዛቢ ልዑክ በተጐበኙ 815 የምርጫ ጣቢያዎች የተመዘገቡት 24 ቅሬታዎች ብቻ ነበሩ።፡ እነዚህ ቅሬታዋች የድምፅ አሠጣጥ ስነ ስርዓቱን ሚስጥራዊነት አለመከበር፣ ድምፅ በሚሰጥበት ወቅት ቅስቀሣ ማድረግ፣ የምርጫ ጣቢያ ሠራተኞች መራጮችን ማንን መምረጥ እንዳለባቸው ከማስረዳት ጋር የተያያዙ፣ መራጮች የመራጭነት መዝገብ ላይ አለመፈረም፣ አንድ የመራጭ መዝገብ ላይ አስመስሎ የመፈረም ክስ እና ሌላ አንድ በአከፋፈቱ ላይ የተነሣ ረብሻ ጋር የተያያዙ ነበሩ። እንዲሁም በድምፅ ኮሮጆ የመክፈት ሂደቱ ላይ ሦስት ቅሬታዎች የቀረቡ ሲሆን ስድስት ደግሞ በቆጠራና በውጤት ላይ ቀርበዋል። በተጨማሪ ቅሬታ አልቀበልም ያሉ የምርጫ ጣቢያዎች ጉዳይ የሚመለከቱ ስድስት ቅሬታዎች ቀርበዋል።

*ሐ. የፓለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ጉባኤ ጥምር ምክር ቤቶች*

የፓለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ስነምግባር ደንብ (ECCPP) አማካኝነት የተቋቋመና በብሄራዊና በምርጫ ክልል ደረጃ ተቋቁሟል። ሆኖም ግን በተለያዩ ደረጃዎች በሚገኙ በነዚህ የጋራ ምክር ቤቶች መካከል የስልጣን ተዋረድ ግንኙነት የሌለ ሲሆን ራሣቸውን ችለው በራሣቸው ደንቦችና ስነ ስርዓቶች መሠረት ይንቀሣቀሣሉ። በአጠቃላይ በነዚህ የፓለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ጉባኤ የተሣተፉ አብዛኛዎቹ የፓለቲካ ፓርቲዎች እነዚህን ፎረሞች ለቅሬታ ማቅረቢያነት የመረጧቸው ይመስላል። ይህ ደግሞ በሂደቱ ቀላልነትና በሚደረጉት ግምገማዎች አልያም ደግሞ ለፍርድ ቤትና ለምርጫ ቦርድ ለማቅረብ ፈቃደኛ ካለመሆናቸው የተነሣ ሊሆን ይችላል። የአውሮፖ ህብረት ምርጫ ታዛቢ ልዑክ እንደተመለከተው የጋራ ጉባኤው በብዙ ሁኔታዎች ላይ አዎንታዊ ሚና

---

[27] የአለምአቀፍ ሲቪልና ፖለቲካዊ መብቶች ስምምነት አንቀፅ 2 ይመልከቱ፣ የተባበሩት መብግስታት የሰብአዊ መብት ኮሚሽን፣ ጠቅላላ አስተያየት ቁ. 25 አንቀፅ 20፡- "መራጮች በድምፅ መስጫው ደህንነትና በድምፅ ቆቸራው ላይ መተማመን እንዶኖራቸው የድምፅ አሰጣጡና የቆጠራው ሂደትና የፍርድ አካላት ወይም ተመሳሳይነት ያላቸው አካላት ተደራሽነትን ነፃ በሆነ አካል በጥልቀት መመርመር አለበት።" በተጨማሪም አፍሪካ ህብረት, ኤ-ሲ-ኤች-ፒ-አር (ACHPR) አንቀፅ 7ን ይመልከቱ።

ተጫውቷል፣ በተለይ እንደ የእጩዎች ምዝገባ ጊዜ መራዘም ያሉ ውጤት ያፈሩ ጥያቄዎችን ለምርጫ ቦርድ ማቅረብን የመሣሠሉ በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል መነጋገርንና መወያየትን በጉልህ የሚታዩ ናቸው።

ሆኖም ግን በምርጫ ክልል ደረጃ የአውሮፖ ህብረት ምርጫ ታዛቢ ልዑክ እንዳስተዋለው ገዢው ፓርቲ የምርጫ ሂደቱን ለመቆጣጠር የተጠቀመባቸው መሣሪያዎች እንደሆኑ በተደጋጋሚ አስተውሏል። አብዛኛዎቹ የጋራ ጉባኤው ምርመራዎች የሚደመድሙት የቀረቡት ማስረጃዎች ቅሬታውን ለመደገፍ በቂ አይደሉም የሚሉ ነበሩ። በተጨማሪም የጋራ ምክር ቤቶቹ የወንጀል ድርጊቶችን ልክ እንደ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተመለከቱ ጉዳዮችን መቀበላቸውና መወሠናቸው የወንጀል ድርጊቶችን በተመለከተ የፍትህ አካላትንና የመንግስትን የራሱን ሀላፊነት አለመኖር የሚያሣይ ነው። ቅሬታዎችን ለጋራው ምክር ቤት ማቅረብ የፍትሃብሄር ወይም የወንጀል ክስ መመስረትን የሚያስቀር አይደለም፣ ምንም እንኳን ይህ በተደጋጋሚ በተግባር ቢስተዋልም። ይህ ሁኔታ፣ የጋራው ምክር ቤት ውሣኔዎች ለምርጫ ቦርድ ወይም ለፍርድ ቤት በይግባኝ መቅረብና አለመቅረብን በተመለከተ ካለው የግንዛቤ እጥረት ጋር ተደማምረው የክሶችን ቁጥር ቀንሠውት ሊሆን ይችላል። ስለዚህም የውጤታማ መፍትሄ የማግኘት፣ ግልፅነትና የሂደቱ እውነተኛነት አደጋ ውስጥ ነበሩ።

የጋራ ምክር ቤቶቹ ከምርጫ ጋር የተያያዙ ወንጀሎችን ጨምሮ የበፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ስነምግባር ደንብ (ECCPP) ጥሰቶችን የመመርመር ሃላፊነት ነበረባቸው። የአጣሪ ኮሚቴ የመመስረትና ፓርቲዎች ጥፋታቸውን እንዲያስተካክሉ የመጠየቅ ስልጣን ነበራቸው። በተጨማሪም የመቅጣት ስልጣናቸው ጥያቄዎችን ማቅረብና ጉዳዮችን ይፋ ማድረግ፣ ውሣኔዎችን ለመንግስትና ለምርጫ ቦርድ ይፋ በማድረግ የተገደበ ነበር። የጋራ ምክር ቤቱ ውሣኔዎች ምርመራዎችን ተከትሎ በድምፅ ብልጫ መወሠን ነበር። በብዙ ጉዳዮች እንደተስተዋለው ቅሬታ አቅራቢው የምርመራው ሪፖርት ፈርሞ ቅሬታ ለቀረበበት ፓርቲ ይቅርታ ይጠይቃል፣ በሪፖርቱ ባይስማማበትም እንኳ።

ከምርጫ ቀን በፊት የተለያዩ የጋራ ምክር ቤቶች ወደ 80 የሚሆኑ ቅሬታዎችን ተቀብለዋል። ከእነዚህ ውስጥ ከፖስተር መገንጠል፣ በደጋፊዎች ላይ ጥቃት የመሠንዘር ክስ፣ በተወሠኑ አካባቢዎች ጽ/ቤት የመክፈትና ቅስቀሣ የማድረግ ሂደት ላይ ያጋጠሙ ችግሮች እንዲሁም የህዝብ ታዛቢዎችን አመራረጥ የተመለከቱ አምስቱ አቤቱታዎች ለብሄራዊ የፖርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ቀርበዋል። ሁሉም ምርመራዎች የደመደሙት ክሶቹን የሚደግፉ በቂ ማስረጃ የለም በማለት ነው። የአውሮፖ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ በምርጫ ክልል ደረጃ ባሉ የጋራ ጉባኤዎች የቀረቡ 76 አቤቱታዎችን ሪፖርት አድርገዋል። ከእነዚህ ውስጥ ሰላሣ አራቱ የምርጫ ቅስቀሣን ማወክን ጨምሮ ከቅስቀሣ ጋር የተያያዙ ሲሆኑ ሀያዎቹ ደግሞ እጩዎችና ደጋፊዎች ላይ የተደረገ ማስፈራራትና ጥቃትን የተመለከቱ ናቸው። ከእነዚህ ውስጥ 23 አቤቱታዎች ብቻ ውሣኔ ያገኙ ሲሆን አብዛኞቹም የተበዳዮቹን ፓርቲዎች ባላስደሠተ መልኩ ተወስኖባቸዋል።

*መ. ከምርጫ ጋር የተያያዙ ጥፋቶች*

ከምርጫ ጋር የተያያዙ የወንጀል ድርጊቶች በሶስት አካላት መካከል የስልጣን መጋጨትን በሚፈጥሩ ሦስት የህግ ሠነዶች ተሸፍነዋል። በምርጫ ህጉ ምዕራፍ 9፣ በወንጀል ህጉ ክፍል 5 (አንቀፅ 466-476) ውስጥ ተሸፍነዋል። ከምርጫ ጋር የተያያዙ የወንጀል ድርጊቶች ማስፈራራትን፣ የምርጫ ሂደቱን ማወክና መረበሽ፣ ስልጣንን አለአግባብ መጠቀም፣ ተፅእኖ ማድረግ፣ የምርጫ ማስታወቂያዎችን መገንጠል፣ በማታለል መመዝገብ እና የድምፅ መስጫ ወረቀቶችንና ሣጥኖችን ማንሣትና ማጥፋት እንዲሁም ሌሎችን ይጨምራሉ። ለጥፋቶቹ የእስራት እና/ወይም የገንዘብ ቅጣቶች ተሰጥተዋል።

ከምርጫ ጋር የተያያዙ ጥፋቶች በዋናነት በምርጫ ቦርድና በጋራ ምክር ቤቶች የሚዳኙ ሲሆን በትንሹ ደግሞ በፍርድ ቤቶች ይዳኛሉ። ከላይ እንደጠቀሠው የፖለቲካ ፓርቲዎች በአጠቃላይ ከምርጫ ጋር የተያያዙ የወንጀል ድርጊቶችን ለመፍታት ወደ ምርጫ ቦርድና ወደ የጋራ ጉባኤው መሄድን ያዘወትራሉ። ይህ ደግሞ ለፖሊስ ሪፖርት የሚደረጉና በፍርድ ቤት የሚዳኙ ጉዳዮችን ቁጥር ቀንሶታል። በተወሠኑ ጉዳዮች ላይ ከምርጫ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን የምርጫ ቦርድ ወይም የጋራ ጉባኤው ውሣኔ ከማስተላለፍ በፊት አናይም በማለት ፖሊስና አቃቤ ህግ መቃወማቸው ሂደቱ ላይ ተጨማሪ እንቅፋት ሆኖአል። በተወሠኑ ጉዳዮች የሚመለከተው የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ለማየት የተነሣሽነት (የፍላጐት) ማነስ እንደነበረ የአውሮፖ ህብረት ምርጫ ታዛቢ ቡድን አስታውቋል።[28] በአጠቃላይ በአፍ ከሚሠሙት አቤቱታዎች ጋር ሲነፃፀር ለፍርድ ቤት የሚቀርቡ ጉዳዮች ቁጥር እጅግ አነስተኛ ነው።

---

[28] ለምሳሌ የጉባለፍቶ ወረዳ ፍትህ ቢሮ (አማራ ክልል) በመኢአድ የሰሜን ወሎ ዞን አስተዳደር ላይ የመንግስት ሀብትን አለአግባብ መጠቀም በሚል ከወረዳው የፋይናንስ ቢሮ በወጣ የውስጥ ሠነድ ተደግፎ የቀረበ ክስን ወደ ጋራ ምክር ቤቱ ልኮ ሳይመለከት ቀርቷል። ጉዳዩ በቂ ማስረጃ የለውም በሚል ውድቅ የተደረገ ሲሆን የአውሮፓ ህብርት ምርጫ ታዛቢ ልዑክ ክሱ ወደ ፍርድ ቤት ቢህድ ተቀባይነት ሊያገኝ ይችል እንደነበር ተገንዝቧል።

የአውሮፖ ህብረት ምርጫ ታዛቢ ልዑክ ከምርጫ ጋር ለተያያዙ እንደ የምርጫ ቅስቀሣ መሣሪያዎችን በተለይም ፖስተሮችን ማውደምን የመሣሠሉትን ጥፋቶች በተመለከተ የተቀመጡት ቅጣቶች ከጥፋቶቹ ክብደት ጋር የማይመጣጠኑ ሆነው አግኝቷቸዋል። ህጉ ለዚህ ጥፋት እስከ አንድ አመት እስራት ወይም የገንዘብ ቅጣት የሚያስቀምጥ ሲሆን ሌሎች እንደ ማስፈራራት ያሉ ጥፋቶች ደግሞ ከስድስት ወር የማያልፍ የእስራት ቅጣትን ያስከትላሉ።[29] ልዑኩ እንደሚያውቀው ከምርጫ ቅስቀሣ መሣሪያዎች ማውደም ጋር የተያያዙ (በተደጋጋሚ የኢሕአዴግን ፖስተሮች) 86 ክሶች በዋናናነትም በአዲስ አበባ፣ በኦሮሚያና በትግራይ ክልሎች ለፍርድ ቤት ቀርበውነበር።[30] አብዛኛዎቹ እነዚህ ክሶች፤ ሶስቱ እድሜያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆኑትን ጨምሮ በሁለት ቀናት ውስጥ ውሣኔ ተሠጥቶባቸዋል። በተግባር ስናየው የገንዘብ ቅጣቶች በጥቂት ፈፃሚዎች ላይ የተፈረደ ሲሆን አብዛኛዎቹ ግን ከ 15 ቀን እስከ 10 ወር እስራት ተፈርዶባቸዋል፣ ምንም እንኳን አማካዩ እስራት ስድስት ወር ቢሆንም።

## XIV. የምርጫ ቀን

የምርጫው ቀን ሠላማዊና ህዝቡ በነቂስ ወጥቶ የተሣተፈበት ነበር። የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ሚስጥራዊነት ከታዘብናቸው ምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ በ 87 በመቶው የተከበረ ሲሆን በአብዛኛዎቹ የምርጫ ጣቢያዎችም አስፈላጊዎቹ ቁሣቁሶች በሙሉ ተሟልተው ነበር። የአውሮፖ ህብረት ምርጫ ታዛቢ ልዑክ ታዛቢዎች በተለይ በመክፈቻ፣ በመዝጊያ፣ እንዲሁም በቆጠራ ሂደቶች ወቅት ተመሣሣይ ያልሆኑ ስርዓቶችን አስተውለው ነበር። እንዲህ አይነቶቹ የስነ ስርዓት ልዩነቶች በአንድ ሶስተኛው ላይ ሪፖርት ተደርገዋል። በምርጫው እለት የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ በሀገሪቱ ሁሉም ክልሎች 815 የምርጫ ጣቢያዎችን ጐብኝተዋል።

*ሀ. አከፋፈት*

የአውሮፓ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ልዑክ የምርጫ ታዛቢዎች የመክፈቻ ስነ ስርዓቱን ከታዘቧቸው የምርጫ ጣቢያዎች በ 46 በመቶው ‹‹ጥሩ›› የሚል ውጤት ሠጥተዋቸዋል። ከምርጫ ጣቢያዎች በ 93 በመቶዎቹ በበቂ ሁኔታ የሠው ሀይል ያላቸው ሲሆን ስነ ስርዓቶቹን በተመለከተ ያላቸው እውቀት በአጠቃላይ በቂ የሚባል ነበር። ነገር ግን ከታዘብናቸው የምርጫ ጣቢያዎች አንድ ሶስተኛ በሚሆኑት የመክፈቻ ስነ ስርዓቶች በትክክል አልተተገበሩም። ከታዘብናቸው ጣቢያዎች በ 34 በመቶ የመራጮች መዝገብ ለፓርቲዎች ተወካዮች ያልቀረበላቸው ሲሆን ይህም እስከ ሚዛጋ ድረስ ሊኖር የሚችለውን ለውጥ ለማወቅ እድል አልሠጣቸውም። ከታዘብናቸው የምርጫ ጣቢያዎች በ 24 በመቶው ደግሞ የተቀበሏቸው የምርጫ ኮሮጆዎች በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ይፋ ከተደረገው ሠነድ አንፃር ያልተፈተሸ ሲሆን ይሄ ደግሞ ይህንን ቁጥር በመዝጊያው ላይ ከነበረው የኮሮጆ ቁጥር ጋር ማነፃፀር እንዳይቻል አድርጓል።

*ለ. ድምፅ አሰጣጥ*

በእለቱ የድምፅ አሠጣጥ ስርዓቱ በአግባቡ የተደረገ ነበር። የአውሮፓ ህብረት ምርጫ ታዛቢ ልዑክ ከታዘባቸው የምርጫ ጣቢያዎች በ 87 በመቶው ሂደቱ ‹‹ጥሩ›› እና ‹‹አጥጋቢ›› የሚል ውጤት ተሠጥቶታል። ከተጐበኙት የምርጫ ጣቢያዎች በአብዛኛው የፖለቲካ ፖርቲዎች ተወካዮች ተገኝተዋል። የኢህአዴግ ፖርቲ ተወካዮች በሁሉም የታዘብናቸው የምርጫ ክልሎች የተገኙ ሲሆን የመድረክ በግማሾቹ የመኢአድ ተወካዮች ደግሞ ከታዘብናቸው ጣቢያዎች በ 20 በመቶዎቹ ተገኝተዋል። የሀገር ውስጥ ታዛቢዎች 76 በመቶ በሚሆኑት የታዘብናቸው የምርጫ ጣቢያዎች የተገኙ ሲሆን አብዛኛዎቹ የመጡት ከኢትዮጵያ ሲቪል ማህበራት ጥምረት ምርጫ ታዛቢ ቡድን ነው።

ሆኖም ግን ከታዘብናቸው የምርጫ ጣቢያዎች 13 ከመቶ በሚሆኑት ታዛቢዎቹ መምራት፣ ማስፈራራት ወይም መራጮች ላይ ጫና የማድረግ አዝማሚያ በምርጫ ጣቢያዎች አቅራቢያ አስተውለው ነበር። ከታዘብናቸው ውስጥ 15 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎች የምርጫ ካርዶች ስነ ስርዓቱ በሚያዘው መሠረት በዘዴ አልተወገዱም። በተጨማሪም በአውሮፖ ህብረት ምርጫ ታዛቢ ልዑክ ከተጐበኙ የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ 21 በመቶ በሚሆኑት ሠዎች የምርጫ ካርዳቸውን ሣይዙ እንዲመረጡ የተደረገ ሲሆን የተፈቀደላቸው ግን በስነ ስርዓቱ መሠረት ነው። የልዑካን ቡድኑ የአንድን ሠው ለብዙ ጊዜያት ድምፅ መስጠትን በተመለከተ በቂ ዋስትና ካለመኖሩ የተነሣ እነዚህ ሁኔታዎች አሣስበውት ነበር። የአውሮፖ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ቡድን ታዛቢዎች በየምርጫ ጣቢያው በተገኙት የመራጭዎ ት መመዝገቢያን በተመለተ

---

[29] የኢፌድሪ ወንጀለኛ ህግ አዋጅ ቁጥር 414/2114 አንቀፅ 580

የተለያዩ እንደ ተደጋግመው የተፃፉ ስሞች እና በመመዝገቢያው ላይ ያሉ ፊርማዎች ከምርጫው በፊት ካለው ጋር አለመመሣሠል ያሉ አለመጣጣሞችን ሪፖርት አድርገዋል።

*ሐ. አዘጋግ እና ቆጠራ*

አዘጋጉና ቆጠራው በተረጋጋ ሁኔታ የተደረገ ሲሆን ጥቂት አቤቱታዎች ብቻ ተመዝግበዋል። የአውሮፖ ህብረት የምርጫ ታዛቢ ልኡክ ታዛቢዎች ከተመለከቷቸው የምርጫ ጣቢያዎች በ66 በመቶ የነበረውን አዘጋግና ቆጠራ ‹‹አጥጋቢ›› ወይም‹‹ጥሩ››፣ ለተቀሩት 34 በመቶ ደግሞ ‹‹ጥሩ ያልሆነ ›› የሚል ውጤት ሰጥተዋል። የፖለቲካ ፖርቲ ተወካዮች በአጠቃላይ በቆጠራውስነ ስርዓት ላይ ተገኝተዋል። የኢህአዴግ ተወካዮች በሁሉም የምርጫጣቢያዎች የተገኙ ሲሆን የመድረክ ተወካዮች ደግሞ ግማሽ በሚሆኑት ተገኝተዋል። ከታዘብናቸው የምርጫጣቢያዎች 45 በመቶ በሚሆኑት የሀገር ውስጥ የምርጫታዛቢዎች ተገኝተዋል።

ተቀባይነት ያላቸው የዲሞክራሲያዊ ምርጫ መርሆዎች የምርጫ ህጉና የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የድምፅ አሠጣጥ፣ ቆጠራና የውጤት ማሣወቅ ደንብ የመራጮች ፍላጐት ግልፅ ያልሆነ ባቸውን የምርጫ መስጫ ወረቀቶች ውድቅ እንዲሆኑ ያዛሉ። ነገር ግን የምርጫ ህጉ እንደሚደረገው የድምፅ መስጫ ወረቀት ዋጋ እንዲኖረው የመራጩ ፍላጐት ‹‹X›› ምልክት ወይም የጣት አሻራ በማኖር ብቻ የተገለፀ እንደሆነ ነው። የአውሮፖ ህብረት የምርጫታዛቢ ልዑክ ለመራጩ ግልፅ ፍላጐት ትልቅ ግምት ሊሠጠው እንደሚገባ ያምናል። በተግባርም ዋጋ ያላቸውን የድምፅ መስጫ ወረቀቶች የትኞቹ እንደሆኑ ለመወሠን በቦታው የነበሩት ሁሉ ህጉን ለመተግበር ተስማምተው ስለነበር በአጠቃላይ ችግር አልነበረም። ይህ ሆኖ እያለ ግን የተወሠኑ የአውሮፖ ህብረት ምርጫታዛቢ ልዑክ ታዛቢዎች የተሠጠውድምፅ ለማን መሆኑ ላይ ተመርኩዞ የተወሠነ የአተገባበር ችግር እንደነበር ተስተውለዋል።

በተወሠኑ ምርጫ ጣቢያዎች የቆጠራ ሂደቱ ቁልፍ ነገሮች በበቂ ሁኔታ አልተከበሩም ነበር። ዋናው ደካማ ጐን በነበረው ሁሉንም የድምፅ መስጫ ኮሮጆዎች በአግባቡ አለመቁጠርና ዋጋ ያላቸውን፣ የሌላቸውን እና ጥቅም ላይ ያልዋሉ የድምፅ መስጫወረቀቶችን ለይቶ አለመመዝገብ ናቸው። በተጨማሪም በታዘብናቸው 25 በመቶ የምርጫክልሎች የውጤት መመዝገቢያ ቅጾች በሁሉም የፓርቲ ተወካዮች ያልተሠጠ ሲሆን 50 በመቶ በሚሆኑት ደግሞ ውጤቶች በደንቡ መሠረት ለህዝብ በሚታይ ቦታ አልተለጠፈም። ይህ የሂደቱን ግልፅነትና ተዓማኒነት ቀንሶታል።

## XV. ውጤቶችና የድህረ ምርጫሁኔታዎች

*ሀ. የጊዜያዊ የምርጫውጤቶች ይፋ መሆን*

በግንቦት 16 ምሽት ላይ 100 የሚሆኑ በስም ያልተገለፁ የምርጫጣቢያዎች ጊዜያዊ ውጤት ይፋ ሆነ። በግንቦት 17 ብሄራዊ የምርጫቦርድ ከ 547 የምርጫክልሎች የ 536ቱን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ምርጫ ጊዜያዊ ውጤት ይፋ አደረገ። በቀጣዩ ቀን ከአንዱ በስተቀር የሁሉም የምርጫ ጣቢያዎች ጊዜያዊ ውጤት ይፋ ተደረገ። ግንቦት 20 ብሄራዊ የምርጫቦርድ በክልላዊ ምክር ቤቶች የሁሉንም መቀመጫዎች ውጤት ይፋ አደረገ።

እነዚህ የጊዜያዊ የምርጫ ውጤት ገለፃዎች እንዲያደርጉ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በሀገራዊ ደረጃ ባሉ የምርጫ ጣቢያዋች የተዘረጋ የሪፖርት አሰጣጥ ስርዓት ዘርግቶ ነበር። የተሠጡድምፆችን መደመርን ብቻ አላማ ስላደረገ ሂደቱ ፈጣን ነበር። በምርጫክልል ደረጃ ካሉ የምርጫጽ/ቤቶች ደረጃ ከተደረገው የተዋረድ ስራ በተለየ መልኩ ይህ ሂደት የቁሳቁስ መረካከብና የድምፅ ቁጥሮችን ማስተያየትን አያካትትምነበር።

*ለ. በምርጫክልል ቢሮዎች የነበረው የውጤት ተደምሮ መጠቃለል*

ምንምእንኳን በአውሮፖ ህብረት የምርጫታዛቢ ልኡክ ታዛቢዎች በአጠቃላይ ችግር የነበረበት ነው ቢልም የማዋሀድ ሂደቱ በሠላማዊ ሁኔታ የተካሄደ ነበር። ከታዘብናቸው 60 በመቶ በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያዎችን ውጤቶች በምርጫ ክልል ደረጃ የማዋሃድ ሂደቱ በምርጫው ቀን ተጀምሮአል። ምንምእንኳን 20 በመቶ በሚሆኑት ከሁለት ቀናት በኋላ እንዲሁም 10 በመቶ በሚሆኑት ከዚያም ዘግይቶ ቢጀመርም፣ በዚህ ደረጃ መዘግየቶች ሊፈጠሩ የቻሉት የምርጫውጤት ቅፆችን ከምርጫ ጣቢያዎች ለማጓጓዝ የወሠደው ጊዜና የማዋሀድ ሂደቱን ከመጀመሩ በፊት የሁሉንም ምርጫ ጣሪቢያዎች ቅፅ መጠበቅ ከማስፈለጉ ጋር ተደማምሮ ነው። ሂደቱ በአብዛኛዎቹ ከልክ በላይ ጊዜ የፈጀ ነበር። 55 በመቶ በሚሆኑት ከምርጫቀን በኋላ አራት ቀናት የፈጀ ሲሆን 20 በመቶ በሚሆኑት አምስት ቀናት፣ 8 በመቶ በሚሆኑት

[30] በትግራይ ክልል የአረና እጩተወዳዳሪ የራሱን ፖስተር በማጥፋት የተከሰሰ ሲሆን ከዚያ በኋላ እንዳይቀድደውማስጠንቀቂያ ተሠጥቶታል።

ስድስት ቀናት እንዲሁም 6 በመቶ የሚሆኑት ሠባት ቀናት ፈጅቷል። በተወሠኑ የታዘብናቸው የምርጫ ክልሎች ሂደቱ የተጠናቀቀው ከምርጫ ቀን አስር ቀናት በኋላ ነበር።

ከተወሠኑ ሁኔታዎች በስተቀር በአዲስ አበባ፣ በአማራ እና በሶማሌ ክልሎች ሂደቱን ድብቅ ለማድረግ ወይም የአውሮፓ ህብረት ምርጫ ታዛቢ ልኡክን መኖር ለማወክ የተደረገ ሙከራ የለም። የፓርቲ ተወካዮች በዋናነት የኢህአዴግ ተወካዮች በተወሠነ መልኩ ደግሞ የመድረክ ተወካዮች በቦታው ተገኝተው ነበር። ነገር ግን የተገኙት በሂደቱ መጀመሪያ ላይ ብቻ ነበር። የሀገር ውስጥ ተወካዮች ከመጀመሪያው የሚዋህድ ቀን በኋላ በአጠቃላይ በቦታው አልተገኙም።

40 በመቶ በሚሆኑት ላይ የአውሮፖ ህብረት ምርጫ ታዛቢ ልኡካን ታዛቢዎች ውጤቶቹ ግልፅ በሆነ መንገድ እንዳልተደመሩ ተመልክተዋል። ይህም የሆነበት ምክንያት ለሂደቱ የተጠቀመባቸው ቦታዎች (ግቢዎች) ትንሽ ከመሆናቸው የተነሣ በአንድ ጊዜ ሁሉንም መሣሪያዎች የፖርቲና የታዛቢ ተወካዮችን ለማስተናገድ ስለማይችሉ የማዋሀድ ሂደቱን በበቂ ሁኔታ ለመከታተል ስለማይቻል ነው። ሂደቱ በእጅ በመጻፍ በመካሄዱ የተነሣም ችግሮች ተስተውለው ነበር።

በምርጫ ጣቢያዎች መከፈቻና መዝጊያ ወቅት በጥቅም ላይ የዋሉ፣ ጥቅም ላይ ያልዋሉ፣ ዋጋ ያላቸውና ዋጋ የሌላቸው የድምፅ መስጫ ወረቀቶች መመዝገብ ጋር በተያዘዘ የተስተዋሉ ችግሮች ነበሩ። መሞላት የነበራቸው ቅጾች በተደጋጋሚ በምርጫ አስፈፃሚዎች አልተሞሉም ነበር። ይህ ደግሞ በከፊል ከስልጠና እጥረት የተነሣ የመጣ ነው። በተጨማሪም ብቂ ያልሆኑ የቅፅ አነዳደፎች እንዲሁም ያለካርቦን ብዙ ቅጂዎችን በእጅ ፅሁፍ ማዘጋጀት የምርጫ ሠራተኞችን እንዲዘገዩና እንዲሠለቹ አድርጓል።

የአውሮፓ ሕብረት ምርጫ ታዛቢ ልዑክ ከታዘባቸው 27% በሚሆኑት የምርጫ ጣቢያ ውጤቶች በመጀመሪያ ከተመዘመገበው ጋር ተመሳሳይ አልነበሩም። ከነዚህ በርካታ ቁጥሮች የተሣሣቱ ወይም ያልተሟሉ የምርጫ ጣቢያ ቅዮች ቢገኙም በምርጫ ክልል ጽ/ቤቶች ተስተካክለዋል ወይም ተሞልተዋል፡ ይሄ አስፈላጊ የውጤቱን ትክክለኛነት ሊያመሳስል የሚያስችል ቁልፍ ነገርን ሊያጓድለው ችሏል። ውጤቱን ለማዋሃድ ለእያንዳንዳቸው ምርጫዎች ሁለት ቅዮች ጥቅም ላይ ውለው ነበር። "ቅጽ 8" የውጤቶች ማጠቃለያ የሚመዘገብበት ሲሆን "ቅጽ 10" ደግሞ ለእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ ውጤቶችን ይዘረዘራል። ከታዘብናቸው ውስጥ 13 በመቶ የ"ቅፅ 8" ለሚሆኑት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና 20 በመቶ ለሚሆኑት የክልል ምክር ቤት ምርጫዎች አልተሟሉም። ከአንድ ሶስተኛው በላይ በሚሆኑት ደግሞ የምርጫ ክልሎች የውጤት ቅፆች በምርጫ ክልል ጽ/ቤቶች አልተለጠፈም።

*ሐ. በኢምቦ ዋና መስሪያ ቤት የነበረው የውጤት አሰራር*

የምርጫ ጣቢያ ውጤቶችና የምርጫ ክልል ውጤቶች በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዋና መስሪያ ቤት ተሰብስበው ተጣርተው ወደ ኮምፒዩተራይዝድ ዳታቤዝ እየተመዘገቡ እንዲገቡ ተደርጓል። በቲዮሪ የፓርቲ ተወካዮች በቅድሚያ ጠይቀው በቦታው እንዲገቡ ተፈቅዶላቸው የነበረ ቢሆንም በተግባር ግን በዚህ ደረጃ ላይ የተገኘ የፓርቲ ተወካይ አልነበረም። የምዝገባ ቅድሚያ የተሠጠው ከተለያዩ ቦታዎች ስለሚሰበሰቡ በማለት ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና ከወታደራዊ መኖሪያዎች ያሉትን ውጤቶች ምምዝገብ ነበር።

ልዑኩ በአውሮፓ ህብረት ታዛቢዎች የተሰበሰቡ ለናሙና የተያዙ የምርጫ ጣቢያና የምርጫ ክልል ውጤቶችን በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ዋና መስሪያ ቤት ከገቡበት ጋር ያስተያያቸው ሲሆን በተወሠኑ አካባቢዎች ከነበሩት ጥቂት ስህተቶች በስተቀር ዋጋ ያላቸውን ድምፅ መስጫዎች በተመለከተ በአጠቃላይ ትክክለኛ መሆናቸውን ደርሶበታል። ነገር ግን ዋጋ የሌላቸውን እና ጥቅም ላይ ያልዋሉትን ድምፅ መስጫዎች በተመለከተ የተመዘገቡት ቁጥሮች ከፍተኛ የሖነ አለመጣጣም ይታይባቸዋል። የአውሮፓ ሕብረት ምርጫ ታዛቢ ልዑክ ታዛቢዎች ዋጋ ያላቸውንና ዋጋ የሌላቸውን የድምፅ መስጫ ሣጥኖች በተመለከተ የያዙት ሪከርድ 60 በመቶ በሚሆኑት (ከ 129ኙ በ 77ቱ) በርካታ መቶዎች ልዩነት ነበረው። የትኞቹ ቁቸሮች እንደጨመሩ ወይም እንደቀነሱ የሚያሳዩ አዝማሚያዎች አልነበሩም። በምርጫ ክልል ደረጃ እጩዎች ያገኙት ድምፅን በተመለከተ ጥቂት ልዩነቶች ብቻ የነበረ ቢሆንም የድምፅ መስጫ ወረቀቶችን በተመለከተ ግን ከፍተኛና በተደጋጋሚ ቁጥር ልዩነት ነበር። 64 በመቶ በሚሆንበት የነዚህ ቁጥሮች ላይ ልዩነት የነበረ ሲሆን በተወሰኑት ላይ በብዙ በርካታ ሺዎች የሚቆጠሩ ልዩነቶች ነበሩ።

*መ. ድህረ ምርጫ ሁኔታዎች*

ኢህአዲግ በመላ ሀገሪቱ በዋናነትም በአዲስ አበባ መሰቀል አደባባይ ከምርጫ ቀን ከ 48 ሠዓታት በኋላና እንዲሁም በአውሮፓ ህብረት የመጀመሪያ ደረጃ ሪፖርት ከመለቀቁ ከሠዕታት በፊት ሠላማዊ ሠልፎችን አዘጋጅቶ ነበር። ምንም እንኳን መንግስት እነዚህን ስብሰባዎች በአጋጣሚ የተከሰቱ ናቸው ቢልም በመላ ሀገሪቱ የነበሩ ተመሳሳይ ሠልፎች

ከተደራጀ ትራንስፖርት አቅራቦት፣ በቀበሌ ስፖንሰር ከተደረጉ ሠልፎች ከፍተኛ ጥራት ያላቸው ህትመቶች (አንዳንዶቹ በእንግሊዝኛ) ጋር ተደማምሮ ሠልፎች አስቀድመው የተዘጋጁ መሆናቸውን ያሣያል። በኦፊሴላዊነት ሠልፉ በግንቦት 16 የወጣውን ምርጫውን የተቸውን ለሂውማን ራይትስ ዎች (HRW) ሪፖርት ላይ የተደረገ ሕዝባዊ ተቃውሞን ለመግለፅ የተደረጉ ናቸው። አብዛኛዎቹ ንግግሮችና ባነሮች አለም አቀፍ ታዛቢዎችና አለም አቀፍ ማህበረሰብና የሕዝቡን ሉአላዊ ፍቃድ ጣልቃ ሣይገቡ እንዲያከብሩ የሚሉ ናቸው። ከእነዚህ ውስጥም "ታዛቢዎች እሺ፣ የትሮይ ፈረሶች እምቢ" የሚሉ ፅሁፎች ይገኙበታል። ሆኖም ግን እነዚህ ሠልፎች በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በዋዜማው በነበረበት ምሽት የተወሰኑት የምርጫ ውጤቶችን በከፊል ካሳወቀ በኋላ ለኢህአዴግ የድል ማክበሪነትም ሆነው አገልግለዋል።

በመስቀል አዳባባይ ባደረጉትና በመቀጠልም በመገናኛ ብዙሀን በሰጡት ንግግር ጠቅላይ ሚኒስቴሩ ከተቃዋሚ ቡድኖች ጋር ውይይት እንዲኖር እንደሚፈልጉ ገልፀዋል። ይህ ውይይትም ከፓርላማ ውጪ እንደሚሆን ግልፅ ሲሆን ምናልባትም በፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት አነሳሽነት በፎረም መልክ እንደሚሆን ነው። በተጨማሪም ከምርጫው በፊት የነበሩት ከምርጫ ጋር የተያያዙ ወንጀሎች በቸልታ እንደሚታለፉ ገልፀዋል። ምንም እንኳን የተወሡኑ ሠዎች ወደ ፍርድ ቤት ለማምጣት በርካታ ማስረጃዎች ቢኖራቸውም ከምርጫ በኋላ ሌላ ወንጀል እስካልተፈፀመ ድረስ ለመራጩ ሕዝብ ካላቸው አክብሮት የተነሣ ይህንን እንደማያደርጉ ገልፀዋል። አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ሁሉም ተሣታፊዎች እኩል እድል ባልተሠጠባቸው ሂደት ውስጥ እንደማይሣተፉ አመልክተዋል።

ገዢው ፓርቲ ያስመዘገበው መጠነ ሰፊ ድል ገዢውን ፓርቲ ጨምሮ ሁሉንም ፓርቲዎች አስደንቋቸዋል። ምንም እንኳን ገዢውን ፓርቲ አብላጫ ያለውን ድምፅ እንደሚያገኝ ቢጠበቅም በርካታ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የተወሰኑት መሪዎቻቸው ተቀባይነት ባላቸው አካባቢዎች እንደሚመረጡ ጠብቀው ነበር። የመድረክ መሪ በየነ ጴጥሮስ ምርጫውን "እውነተኛ ያልሆነ" በማለት የፈረዱት ሲሆን በጥምረቱ ያሉት ሌሎች አጋሮቻቸው ዶ/ር መራራ ጉዲና እና ኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው ምርጫው ነፃ ም ፍትሐዊትም አይደሉም በማለት ተቃውመውታል። በምርጫው ጊዜ የተናገሩትን ነገር በማንሣት የኢትዮጵያ ሕዝብን ይቅርታ ጠይቀዋል። የኢዴፓ መሪ አቶ ልደቱ አያሌው ውጤቱን የተቀበሉት ሲሆን በኢህአዴግ ድል ስፋት ጋር በተያያዘ የውጤቶችን ተአማኒነት ጥያቄ ውስጥ ከትተዋል። ሽንፈታቸውንም በፖለቲካ ማህደሩ መጥበብ፣ በተቃዋሚዎች መካከል በነበረው መከፋፈል፣ በቂ ያልሆነ ገንዘብ ባለመኖሩ፣ በገዢው ፓርቲ የነበረው ማስፈራራት እና ከስር በነበራቸው የድጋፍ ማነስ ምክንያት እንደነበር ገልፀዋል። ጥቂት የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች የአካባቢያዊ ውጤቶች ይፋ መደረጉን ተከትሎ ከፖለቲካ ውመውጣታቸውን ገልፀዋል።

ይህንን በምን ፅፍበት ወቅትና በ 1997 ምርጫ ከነበረው የድህረ ምርጫ ሁኔታዎች በተለየ መልኩ ከተወሡኑ የተቃዋሚ መሪዎች ክሶች በስተቀር ተረጋግተው ቆይተዋል። ነገር ግን የተቃዋሚ ፓርቲዎች ለማህበራዊ ድርጊቶችና የህዝባዊ ንቅናቄዎች ጥሪ አላቀረቡም። ከአካባቢያዊ ውጤቶች ይፋ መሆን በኋላ በርካታ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች ውጤቱን መቀበላቸውን ገልፀዋል። እነዚህ ፓርቲዎች ለገዢው ፓርቲ የእንኳን ደስ ያለህ መልክታቸውን ያስተላለፉ ሲሆኑ ሌሎች ፓርቲዎች የመራጩን ሕዝብ ድምፅ አክብረው ለሀገሪቱ ሠላምና ዲሞክራሲ መከበር የራሳቸውን አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ጠይቀዋል። መድረክና መኢአድም የምርጫውን ውጤት ላለመቀበል የወሡኑ ሲሆን በብሔራዊ የምርጫ ቦርድም ሀገር አቀፍ ምርጫ በድጋሚ እንዲደረግ አቤቱታቸውን አቅርበአዋል።[31]

*ሠ. የምርጫ አቤቱታዎች*

ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተወሡኑ የምርጫ ጣቢያዎች በድምፅ አሠጣጥና በቆጠራ ወቅት የተደረጉ ያልተገቡ ድርጊቶች በተመለከተ ማስረጃ ማቅረብ ከቻሉ የድጋሚ ምርጫ እንዲደረግ የማዘዝ ስልጣን አለው። ምንም እንኳን ከምርጫ ክልል ደረጃ ጀምረው ባለመቅረብ የሚጠይቀውን አመጣጥ ባይከተሉም ሦስት ኦፊሴላዊ አቤቱታዎች ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ቀርበዋል።

የመጀመሪው አቤቱታ በግንቦት 17 ቀን በመኢአድ የቀረበ ቢሆንም ማስረጃው ግን የቀረበው በግንቦት 23 ነበር። በመኢአድ በዋናነት ከምርጫው ቀን በፊት በተከሰቱ በርካታ ጥሰቶች ምክንያት ምርጫውን እንዲደገም ጠይቀዋል። ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ጉዳዮቹ ቀድመው መታያታቸውንና በድጋሚ ምርጫ ለማድረግ በቂ ምክንያት አይደሉም በሚል ምላሽ ሰጥቷል። በተመሳሳይም በግንቦት 23 መድረክ ምርጫውን ነፃና ፍትሐዊ ባለመሆኑ የተነሣ ሀገር አቀፍ ድጋሚ ምርጫ እንዲደረግ ጠይቋል። አብዛኛዎቹ ክሶች ከቅድመ ምርጫ ወቅት ጋር የተያያዙ የነበሩ ሲሆኑ በምርጫ ቀን የፓርቲ ተወካዮቻቸው ወደ ምርጫ ክልል እንዳይገቡ መከልከላቸውንና አንድ ሠው ከአንድ ጊዜ በላይ መምረጥም ይጨምራሉ። ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ መድረክ ክሶቹን የሚያጠናክሩ በቂ ማስረጃዎች አላቀረብክም በማለት

[31] ሁለት አነስተኛ ፓርቲዎች፣ ማለትም የኢትዮጵያ ፍትህና ዲሞክራሲ ግንባር እና ብርሀን ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ውጤቱን አልተቀበሉትም።

ሠርዟቸዋል። ሶስተኛው ክስ ያቀረበው የሲዳማ ነፃ አውጭ ንቅናቄ ሲሆን በሂደቱ ላይ በርካታ ችግሮች ነበሩበት በማለ በተወዳደረባቸው የምርጫ ክልሎች ድጋሚ ምርጫ እንዲደረግ ጠይቋል።

ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የቀረቡት ክሶች በጠቅላላ በምርጫ ቀን የተከሠቱ ችግሮችን አልጠቀሱም በምርጫ ቀን የተከሠቱ ችግሮች ድጋሚ ምርጫ እንዲደረግ ለመጠየቅ በቂ ምክንያት ሆነው ሊወሰዱ ይችሉ ነበር። ፓርቲዎች የተጠቀሱት ችግሮች የተከሠቱባቸውን ክልሎችና አካባቢዎች ቢጠቅሱም የምርጫ ጣቢያዎች ለመጥቀስና ጠንካራ ማስረጃ ማቅረብ አልቻሉም።

መኢአድና መድረክ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ውሳኔ ላይ ቅር በመሰኘት ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ብለዋል። የጊዜ ገደብን በተመለከተ የተወሠነ አለመግባባት ከተፈጠረ በኋላ ፍ/ቤት ይግባኙን ለማየት ወስኗል። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በቅድመ ምርጫ ወቅት የነበረውን ጊዜ በተመለከተ ተነስተው የነበሩት በቅድመ ምርጫ ወቅት የነበሩት ችግሮች በጠቅላላ አስቀድመው የታዩ መሆናቸውንና ፓርቲዎች ይግባኙን ከማቅረባቸው በፊት ሌሎች አማራጭ መንገዶች አልተጠቀሙም በሚል የብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ውሳኔ አጽድቆታል። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በተጨማሪም ለክሳቸው በቂ ማስረጃ አላቀረቡም ብሏል።

የኢትዮጵያ ፍትሕ እና የዲሞክራሲያዊ ሀይሎች ግንባር በግንቦት 23 ለጋራ ጉባኤው በምርጫ ቀን የፓርቲ አባላት፣ ተወካዮችና እጩዎች ላይ የተደረገ ድብደባን እና እስርን በተመለከተ እንዲሁም የአስተዳደር ሠራተኞች በመራጮች ላይ አላግባብ የሆነ ጫና አድርገዋል በማለት ክስ አቅርበዋል። ይህ በተፃፈበት ወቅት የጋራ ምክር ቤቱ በዚህ አቤቱታ ላይ ውሳኔ ለመስጠት የስብሰባ ቀጠሮ አልያዘም። ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በጉዳዩ ላይ ምንም አይነት እርምጃ ከመውሰዱ በፊት የጋራ ጉባኤውን ውሳኔ በመጠበቅ ላይ ይገኛል።

*ረ. የመጨረሻ የምርጫ ውጤት ሕትመት*

በምርጫ የጊዜ ሰሌዳው መሠረት ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በሰኔ 14 የምርጫውን ውጤት ለህትመት አብቅቷል። በምርጫ ሕጉ አንቀጽ 77/6 መሠረት ይህ ኦፊሴላዊ ሰነድ ለእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ ጥቅም ላይ የዋሉ ባዶ እና ዋጋ የሌላቸው የድምጽ መስጫ ወረቀት እንዲሁም እያንዳንዱ እጩ ያገኘውን ድምፅ ድምር ይዞ መውጣት ይኖርበት ነበር። ነገር ግን ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ይህንን መረጃ አላወጣውም፣ ኦፊሴላዊ ውጤቶቹ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እያንዳንዱ ፓርቲ ያገኘውን መቀመጫና እንዲሁም ለክልል ምክር ቤት ፓርቲዎች ያገኘውን መቀመጫ በክልሎች ከፋፍሎ ነው ያስቀመጠው። ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከተመዘገበው ውስጥ 93.4 በመቶ የሚሆነው ህዝብ መምረጡን የገለፀ ሲሆን የመራጮች ቁጥር በቦታ ከፋፍሎ አስቀምጧል። ኢፈሴላዊ ውጤቶች አህዴፓ ካገኛቸው መቀመጫዎች በስተቀር ከጊዜያዊው ውጤት ጋር ተመሳሳይ ነበሩ። ከጊዜያዊ ውጤቶች ጋር ሲነፃፀር አህዴፓ ያገኛቸውን ወንበሮች ብቻ በኦፊሴላዊ ውጤት ላይ ያለ ብቸኛው ለውጥ ነው። ይህ የተሟላ የዝርዝር የምርጫ ውጤቶች አለመቅረብ ውጤት የአገላለፁ ሂደት ግልፅነት የጎዳው ሲሆን ከምርጫ ሕጉ ድንጋጌዎች ጋርም የሚፃረር ነው።

ምንም እንኳን አገር አቀፍ የመራጭ ቁጥር ከፍተኛ ቢሆንም የተወሰኑ የሃገሪቱ ክልሎች ማለትም በትግራይ ክልል እንዲሁም በአማራ ክልል የተወሰኑ አካባቢዎች፣ በድሬደዋ፣ በጅጅጋ (ሱማሌ ክልል) እና በጅማ (ኦሮሚያ ክልል) ይበልጥ ከፍተኛ ነበር። የአውሮፓ ህብረት ምርጫ ታዛቢ ልዑክ እንደሰበሰበው ዳታና ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ይበልጥ ዘርዝሮ ባላስቀመጠበት ሁኔታ ገዢውን ፓርቲ የሚደግፉ የድምፆች ብዛት ከበአንፃራዊ መልኩ አነስተኛ የሆኑ ዋጋ የሌላቸው ድምፆች ጋር በነኚህ አካባቢዎች የነበሩት ውጤቶች ታአማኒነት አጠራጣሪ ያስደርጉታል። ትግራይ የተለመደ የህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) ጠንካራ ድጋፍ ያለበት ቦታ ቢሆንም እንኳ፣ በአክሱም የምርጫ ክልል 97.95 በመቶ ድምፅ ሰጪ በወጣበት ከነኚህም 98.76 በመቶ ድጋፋቸው ለህወሓት መስጠታቸው፣ በማዕከላዊ ትግራይ የሚገኘው በእንጤጮ የምርጫ ክልል 100 በመቶ መራጮች በወጣበት ከ 51,290 ድምፅ ውስጥ 4ቱ ብቻ ለተቃዋሚዎች መሄዱ፣ ወይም አብዛኛው ገጠራማ በሆነው ሰሜን ምዕራብ ትግራይ 0.44 በመቶ ድምፆች ብቻ ዋጋ የሌላቸው መሆኑ፤ የማይከሰት ባይሆንም እንኳ የመከሰት ዕድላቸው አነስተኛ ነው።

*ሰ. የምርጫ ውጤቶች ፖለቲካዊ ድባብ*

ውጤቶቹ በህዝብ ተወካዮች ከ 547ቱ 544፣ በክልል ምክር ቤቶች ደግሞ ከአራት ወንበሮች በስተቀር 1904ቱ ያሸነፉበት የገዢው ፓርቲና አጋር ድርጅቶች የህዝብ ተወካይ መቀመጫወች በተግባር የጠራረጉበት ከፍተኛ ድል የሚያሳይ ነው። ኢህአዴግ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከተወዳደረባቸው 501 መቀመጫዎች 499ኙን ሲያሸንፍ አጋር ድርጅቶቹ ተጨማሪ 45 መቀመጫዎቹን አሸንፈዋል። ኢህአዴግ ለክልል ምክር ቤቶች 1347 መቀመጫዎችን ያሸነፈ ሲሆን

አጋር ድርጅቶችም 551 መቀመጫዎችን አሸንፈዋል። የአርጎባ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ፓርቲ (አህዴፓ) በአፋር ክልል ምክር ቤት ሦስት መቀመጫዎችን ያሸነፈ ሲሆን መኢአድ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል ምክር ቤት 1 መቀመጫ አሸንፏል።

በህዝብ ተወካዩች ምክር ቤት ውስጥ ገዢው ፓርቲ ካላሸነፋቸው ሦስት ወንበሮች ውስጥ አንዱን የግል ተወዳዳሪ የሆኑት ዶ/ር አሸብር ገብረጊዮርጊስ አሸንፈዋል። ግለሰቡ በደቡብ ክልል በቦንጋ የምርጫ ክልል የአሁኑን የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስቴር አቶ ብርሐን አዴሎን አሸንፈዋል። ምንምእንኳን ያሸነፉት እጩ የኢህአዴግ አባል ሆኜ አላውቅም ቢሉም ደጋፊዎቹን ለክልል ምክር ቤት ኢህዴግን እንዲመርጡ ይቀሰቅሱ ነበር ተብሏል። በአንፃራዊነት አነስተኛ ከሆነ ውአህዴፓ እጩ የሆነ ተወዳዳሪ አንድ ወንበር አግኝቷል። ከዋንኞቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ውስጥ መቀመጫ ያገኙት የመድረኩ አቶ ግርማ ሰይፉ ማሩ ሢሆኑ ያሸነፉትም በአዲስ አበባ ወረዳ ስድስት ነው። አቶ ግርማ ሊመረጡ የቻሉት መራጮቹ በቀላሉ በኢህአዲግ ጫና ሊደርስባቸው የማይችሉ በራሳቸው የሚተዳደሩ ነጋዴዎች ስለሆኑ እንደሆነ ተናግረዋል።

ይህንንም ተከትሎ ለቀጣዮቹ አምስት አመታት በክልል ምክር ቤቶችም ሆነ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተቃዋሚ ፓርቲዎች ጫና አይኖርም። ስለዚህም እስከ 2007 ድረስ በሀገሪቱ ፓርላማ ውስጥ የተለዩ ሀሣቦች ሊያመጡ የሚችሉት ተፅእኖ አይኖርም። እንዲሁም አሁን ባለው የምርጫ ዘመቻ በጀት አመዳደብና በመንግሥት ሚዲያዎች የሰዓት ክፍፍል የተነሳ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከገዢው ፓርቲ ጋር ሲነፃፀር ለ 2007ቱ ምርጫም ተጎጂ ይሆናሉ።

## XVI. ማጠቃለያ አስተያየት

በኃላፊነቱ መሠረትና በኢትዮጵያ የምርጫ ሂደት ላይ ተጨማሪ መሻሻሎች እንዲመጡ ለመርዳት ካለው ፍላጎት የተነሳ የአውሮፓ ሕብረት የምርጫ ታዛቢ ልኡክ ለኢትዮጵያ መንግሥት፣ ለብሔራዊ የምርጫ ቦርድ፣ ለፖለቲካ ፓርቲዎችና ለኢትዮጵያ ሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ግምት ውስጥ እንዲከቷቸው የሚከተሉትን ምክሮችና አስተያየቶችን ይሰጣል።

**የሕግ መዋቅር**

*የሕግ መዋቅሩ ትግበራ ኢትዮጵያ ከፈረመቻቸው ዓለም አቀፍ ግዴታዎች ጋር እንዳይለያይ ለመከላከል፣ በተለይ መሠረታዊ የሆኑ ነፃነቶችን:*

1. ከምርጫ ጋር የተያያዙ ጥፋቶች እና እነሱን ለመዳኘት ስልጣን ያለው አካል በምርጫ ህግ ውስጥ ግልፅና አጠቃላይነት ያለው መመሪያ እንዲኖራቸው በሚል መከለስ አለባቸው። ይህም ሁሉም ጥፋተኞች በፍርድ ቤት ፊት ለሠሩት ስራ እንዲጠየቁ የመንግሥት ሀብትን መጠቀምም መጠቀስ አለበት። ተመጣጣኝነቱን ለማረጋገጥም ለአንዳንድ የምርጫ ጥፋቶች የተዘረዘሩት ቅጣቶች መከለስ አለባቸው። ሠብዓዊ መብቶችንና መሠረታዊ ነፃነቶችን የተመለከቱ በቅርብ ጊዜ የወጡ አዋጆች በምርጫ ሂደቱ ላይ በአጠቃላይም በሠብዓዊ መብት ሁኔታው ላይ ሊያመጡ የሚችሉትን ተፅእኖ ለመቀነስ በሚመለከታቸው አካላት ውይይት ሊደረግባቸውና ሊከለሠም ይገባል።

**የምርጫ ስርዐት**

*ለሀገሪቱ የሕግ አውጭ አካል የበለጠ ተወካይነትን ለማምጣት ለመጨመር፣ ሂደቱን ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ እና የድምፅን እኩልነት ለማረጋገጥ:*

2. በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የበለጠ የተወካይነት ደረጃን ለማበረታታት በኢትዮጵያ የምርጫ ስርዓት ላይ የተወሰነ የተመጣጠነ ውክልና እርምጃዎችን ማስተዋወቅ በሁሉም የፖለቲካ ሀይሎች መታሰብ አለበት። የተወሰኑ የምርጫ ወረዳዎችን ለውጭ ሀገር ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መፍቀድ፣ ከሀገር ውጭ እያሉ በኢምባሲዎችና በቆንስላ ፅሕፈት ቤቶች እንዲመርጡ ከማድረግ ጋር ተደምሮ ሊታሰብበት ይችላል። ሕገ መንግሥቱ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጨማሪ ሶስት ወንበሮችን ከመፍቀዱ ጋር እነዚህ ወንበሮች በውጭ ሀገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ለመወከል ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።

3. የምርጫ ክልሎች ትክክለኛ የሕዝብ ብዛትን እንዲወክሉ የምርጫ ክልል ድንበሮች በድጋሚ መታየት አለባቸው፣ ይህም ለድምፅ እኩልነት ከፍተኛ የሆነ አስተዋፅኦ ያደርጋል። ይህ ክለሣ ነፃ በሆነ ፓናል መደረግ አለበት። ለአነስተኛ ቡድኖች የልዩ የምርጫ ክልሎች ክፍፍልም መከለስ አለበት።

4. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና የመከላከያ ሰራዊት የአመራረጥ ስርዓት ለግልፅነት ሊባል መስተካከል ይችላል። በተጨማሪም በፓርቲ ተወካዮችና በታዛቢዎች በቀላሉ ክፍት ባልሆኑ ቦታዎች ላይ የድምፅ መስጠት መካሄድ የለበትም፣ ለምሣሌ ልክ አሁን በወታደራዊ መኖሪያ ስፍራዎች እንደሚደረገው። ለማዋሀድ ሂደቱ መቀላጠፍ ሲባል እነዚህ ሁለት የህብረተሰብ ክፍሎች ቀድመው እንዲመርጡ የሚደረግበት ሁኔታ ቢመቻች መልካም ነው።

**የምርጫ አስተዳደር**

*የምርጫ አስተዳደሩን ግልፅነትና ተዐማኒነት ለመጨመር እንዲሁም በገለልተኝነቱና በነፃነቱ ላይ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ያላቸውን መተማመን ለመጨመር፡-*

5. በምርጫ አደረጃጀትና አፈፃፀም እስከ ታች ቀበሌ ድረስ ያለውን የመንግስት አስተዳደራዊ ጣልቃ ገብነት ለመወሰን ጥረት መደረግ አለበት። በሂደት ከአከካባቢያዊ አስተዳደር ጥገኝነት የሚላቀቅ እና በእራሱ የቆመ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መቋቋም ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነገር ነው። እነኚህ እርምጃዎች መንግስት በምርጫ ቦርድ ላይ ያለውን ቁጥጥር ጥርጣሬዎችና እንዲሁም በምርጫ እንቅስቃሴ ጊዜ በሀገር እና በገዢው ፓርቲ መሀል ያለው ያልተጣራ ልዩነት እንዲሁም በክልላዊና በአካቢባያዊ ደረጃ ያሉትን የሀገር ሃብት አላግባብ ጥቅም ለመካላከል ይቻላል።

6. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ በሁሉም የምርጫ ደረጃዎች ግልፅነት ለመፍጠር እና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ የምርጫ ቦርድ የምርጫ ጣቢያዎች ዝርዝር፣ የምርጫ ክልሎች ዝርዝር፣ የተመዘገቡ መራጮችን ዝርዝር፣ በምርጫው ዘመቻ የተደረገውን የመንግስት ገንዘብ እና በአናሳ ምርጫ ክልሎች ያለውን ትክክለኛ አካሄድ እና ምደባ አሳትሞ ማሰራጨት አለበት።

7. በሁሉም ባለድርሻ አካላቶች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ገለልተኝነት ለማረጋገጥ የምርጫ ቦርድ አባሎች የሹመት አሰራር ሊከለስ ይገባል። ለዚህ ደግሞ ገለልተኛ የሆነ መድብሉ ፓርቲ የሹመት ፓናል ማዋቀር ይቻላል። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ አባሎች ከዚህ ኃላፊነታቸው ጋር የሚጋጭ ሌላ ቦታ እንዲይዙ ሊፈቀድ አይገባም።

8. የምርጫ ታዛቢ ልዑኩ በተለይ በቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ የህዝብ ታዛቢዎች ለግልፅነት ወይም ለሂደት መተማመኛ አስተዋፅኦ ነበራቸው ብሎ አያስብም።

**የመራጭ ምዝገባ**

*ግልፅነት፣ ታማኝነትና ትክክለኛ የመራጮች ምዝገባ ለትክክለኛ ምርጫ አስፈላጊ አካሎች ናቸው፡*

9. ድጋሚ ምዝገባን ለመከላከል በሚያስችል ማገናዘቢያ እና ደህንነት ያለው ማዕከላዊ እና ኮምፒውተራይዝድ ብሄራዊ የመራጮች ምዝገባ መፈጠር አለበት። በዚህም ቋሚ መዝገብ ሊኖር የሚችልበትን ሁኔታ ማየት ይቻላል። የምርጫው መዝገብ አዲት መደረግ (መጣራት) ሊታሰበበት ይችላል። የከፍተኛ ትምህርትና የወታደሮችን ምዝገባ ጨምሮ የመዝገቡ ቅጂ ከምርጫው ቀን በፊት ለሁሉም ፓርቲዎች ሊሰጥ ይገባል። ጠለቅ ያለ ተሳትፎንና ሁሉን ያቀፈ ምርጫ እንዲሆን የመራጮች ምዝገባ ጊዜ ቢያንስ ለአራት ሳምንታት ሊራዘም ይችላል።

**የተመራጮች ምዝገባ**

*የሁሉም ዜጋ ለምርጫ እኩል የመቆም መብት መሰረተ ሀሳብ በበለጠ ለማክበር፡*

10. በምርጫ ክልል ላይ ያለው የተመራጭ ቁጥር እና የፖለቲካ ፓርቲዎቸ ከ 12 ተመራጭ በላይ መሆን የሚከለክለው ገደብ ሊነሳ ይገባል። በተመሳሳይ የግል ተመራጮች (ተወዳዳሪዎች) ከመንግስት ገንዘብ ምደባ እና ከመንግስት የሚዲያ ጊዜ ስርጭት ሊገለሉ አይገባም።

**የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ተመራጮች**

*በዲሞክራሲው ሂደት መተመማመን ለመጨመር የፖለቲካው ምህዳር በአገር ውስጥ ለማስፋት እና በአሁን ሰአት ያለውን ሚዛን ያልጠበቀ የፖለቲካ ጨዋታ ለመርዳት፡*

11. በስደት ላይ ይሚገኘው የተቃዋሚ አንድ መሪ እና በተባበሩት መንግስታት እንደ አላግባብነት የታሰሩት ሌላ መሪ እስር ጉዳይ ሊታይ ይገባል። የነዚህን መሪዎች የህግ ሁኔታ መከለስ የፖለቲካው ማህደሩን ለማስፋት ጠቃሚና አስፈላጊ ደረጃ ሊሆን ይችላል።

12. ቢቻል በአቅም ግንባታ ፕሮግራም የፖለቲካ ፓርቲዎች ብሄራዊ አቅም መጠናከር ያስፈልጋል። በምርጫ ዘመቻ ብቻ ባልተወሰነ መልኩ በየአመቱ በገንዘብ ሊረዱበት በሚችሉበት መልክ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ሊሻሻል ይገባል። ለዚህ ገንዘብ ክፍፍል እና ተጠያቂነትን ለመፍጠር ንፁህ እና ግልፅ ደንብ ሊወጣ ይገባል።

**የምርጫ ዘመቻ**

*በምርጫ ዘመቻ ጊዜ የተመጣጠነ የመጫወቻ ሜዳ ማቅረብ ለዲሞክራስ ውሂደት አስፈላጊ ነው፡*

13. ፓርቲዎች በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባላቸው መቀመጫ ጋር እንዲመጣጠን ተደርጎ ለምርጫ ዘመቻ የሚሆን ገንዘብ ለተወዳዳሪ ፓርቲዎች የተመደበበት የአመጣጠን መስፈርት እንዲገደብ በድጋሚ ሊታይ ይገባል። ለዘመቻው የሚወጣውን ገንዘብ ሂደት ኦዲት ማድረግ (ማጣራት) በፓርቲዎች መካከል ያለውን የጨዋታ ሜዳ ከማደላደሉም በላይ በምርጫው ዘመቻ ላይ ግልፅነት እና ተጠያቂነትን ይፈጥራል።

14. የፖለቲካ ፓርቲዎች ለምርጫ ቅስቀሳ የሚውሉ ሀብቶችን በደንብ ለመጠቀም የምርጫ ቅስቀሳው ወደ ከአራት እስከ ስድስት ሳምንት ሊያንስ ይችላል።

**የመራጭ ትምህርት**

*የመራጮች በእውቀት ላይ የተመሰረተን የምርጫ እድል ለማረጋገጥ:*

15. የኢትዮጵያ ብሄራዊ የምርጫ ቦርድ የመራጮች መረጃ ፕሮግራም በተመለከተ ያለውን ያነሰ ፍላጎት እንደገና ሊያስብበት ይገባል። የመራጭ ትምህርት በበለጠ በአናሳ ቋንቋዎች እንዲገኝ ትልቅ ጥረት መደረግ ይችላል።

**ሚዲያ**

*በምርጫ ሂደት ጊዜ የሚዲያን ድርሻ በተመለከተ ግራ መጋባትን ለማስወገድ እና ሚዲያው ለህዝብ ሚዛኑን የጠበቀ መረጃ በመስጠት ሃላፊነቱን በነፃነት እንዲወጣ፡-*

16. ጋዜጠኞች በኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ እንዲፈቀድላቸው የተቀመጠው የምርጫ ህግ አንቀፅ 91 ጋዜጠኞች በነፃነት የምርጫ ሂደቱን እንዲዘግቡ ሊሻሻል ይገባል።

17. የመንግስት ሚዲያዎች በምርጫ ጊዜ ነፃ የአየር ጊዜ እንዲሰጡ የሚገልጸው የምርጫ ህግ አንቀጽ 59 በብዙሃን መገናኛ (ብሮድካስት) አገልግሎት ህግ መሰረት ሁሉም ሚዲያ በምርጫ ጊዜ ነፃ ጊዜ በሚሰጡት መልኩ ሊሻሻል ይገባል።

18. ከቅስቀሳ ነፃ በሆነው የ48 ሰዓት መራጮች ከቅስቀሳ ነፃ ሆነው ስለ ፖለቲካ ምርጫቸው በሚያስቡበት ጊዜ ያለውን የሚዲያ ድርሻ በተመለከተ ግልፅ የሆነ ህግ መውጣት አለበት።

19. የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን እንደ የህዝብ መገናኛነቱ ያለበትን ሃላፊነት በቋሚነት የሚቆጣጠርበትን መንገድ ሊታሰብ ይችላል። የኢትዮጵያ ብዙሃን መገናኛ (ብሮድካስት) ባለስልጣንና የተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ሚዲያ ከምርጫ ዘመቻ በኋላ ያላዳላና ተመጣጣኝ ሽፋን ስለመስጠታቸው ሊቆጣጠር ይችላል።

20. የሚዲያዎች የምርጫ አሸፋፈን በተመለከተ ቋሚ የስነ ስርዓት ደንብ ሊታሰብበት ይችላል። ይህ አይነት የስነ ስርአት ደንብ ሁሉንም ባለድርሻ አካላቶች ተወያይተው ሊስማሙበት ይገባል። ሁሉንም የምርጫ ሂደት አቅጣጫ በተመለከተ ሚዲያዎች ሚዛኑን የጠበቀ ዘገባ የማድረጋቸው ሀላፊነት ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

**የሴቶች ተሳትፎ**

*የውክልናውን እና በምርጫ ሂደቱ የሴቶች የተሳትፎ ድርሻ ለማሻሻል:*

21. በተወካዮች ምክር ቤት፣ በፖለቲካ እና በምርጫ አስተዳደር የሴቶች ተሳትፎ የበለጠ ሊበረታታ ይገባል። በመንግስት የምርጫ ዘመቻ የገንዘብ ድጋፍ ጊዜ ለሴት ተመራጮች የበለጠ ሊሰጥ ይቻላል። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ በሙሉ አወቃቀሩ ውስጥ የጾታ ድርሻ (ኮታ) ሊያስተዋውቅ ይችላል።

**ሲቪል ማህበረሰብ እና የአካባቢ ታዛቢዎች**

*ሲቪል ማህበራት በምርጫው ሂደት ያላቸውን ሚና ለመጨመር:*

22.0 በመራጮች ትምህርት እና በአካባቢ የምርጫ ታዛቢነት የሲቪል ማህበረሰቦች እንዲሳተፉ እርምጃ መወሰድ አለበት። ለአቅም ግንባታ፣ ለአካባቢ ታዛቢዎች ስልጠና እና ለመራጮች መረጃ ፕሮግራም ከውጭ ሀገር ለውስጥ የሲቪል ማህበረሰቦች የሚሰጠው ገንዘብ ላይ የተጣለው ገደብ ፈታ ሊል ይችላል።

**ቅሬታዎች እና ይግባኝ**

*ተፈፃሚነት ያለውን የካሳ መብት ለማረጋገጥ፣ ለምርጫ ጥፋቶች ተጠያቂነት እና በሂደት መተማመን ለመጨመር:*

23. ሁሉም ከምርጫ ጋር የተያያዙ ጥፋቶች ለመመርመራቸው እና ሁሉም ጥፋተኞች ጊዜውን በጠበቀ መልኩ በተጠያቂነት እንዲያዙ እና እንዲከሰሱ እርምጃ መወሰድ አለበት። የፍርድ ባለስልጣኖች እና አቃቢ ህጎች የበለጠ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ሊበረታታ ይችላል።

24. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴው አባሎች በቂ የህግ እውቀት ወይም ችሎታ ያላቸው እና ቢቻል በውድድር ሊመረጡ የገባል። የቅሬታ ሰሚ አባሎች ተጠያቂነት እና የምርጫ ጥፋቶችን ወደ ፍርድ ቤት የመምራት ሀላፊነት ሊታሰብበት ይገባል። ምርመራዎችን ለማካሄድ የአቅርቦት ሀይል ሊቀርብለት ይገባል።

25. የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ስልጣን ትንንሽ ለሆኑ የምርጫ ጥፋቶች ማለትም እንደ ፖስተር መቀደድና የምርጫውን ሂደት እና ቅስቀሳ በተመለከተ የማህበረሰብ ጉዳዮች ያሉ ላይ መሆን አለበት። ሌሎች ጥፋቶች ወዲያውኑ በቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት ነው መመራት ያለባቸው። የጋራ ምክር ቤቱ የፖሊስ እና የሲቪል ማህበረሰቡ የምርጫ ጥፋቶችን በሚያዩበት ጊዜ የበለጠ ተሳትፎ እና ግልፅነት እንዲኖር ማድረግ ይችላሉ።

26. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ በሁሉም የምርጫ አስተዳደር ደረጃ ያሉትን የተሟላ ሙሉ የቅሬታ ማህደሮች የሚቀመጥበት የመረጃ ክምችት ማእከል ማቋቋም አለበት። የምርጫ ቅሬታዎችን በተመለከተ አያያዙ በግልፅነት እና በተጠያቂነት መሆኑን ለማረጋገጥ ይህ የመረጃ ክምችት ማዕከል ምላሽ እና ውሳኔዎችን መጨምር አለበት።

**ድምፅ መስጠት፣ ቆጠራ እና ማጠቀለያ**

*የአሰራሩን ሂደት ወጥነት እና ግልፅነት ለመጨመር እንዲሁም የማጠቃለያውን ሂደት ቀልጣፋ ለማድረግ በዛውም በዴሞክራሲው ሂደት መተማመንን ለመጨመር:*

27. ተቀባይነት ያለው ድምፅ ለመስጠት ማንኛውንም ምልክት በመጠቀም የመራጩን ፍላጎት ቅድሚያ በሰጠ መልኩ የምርጫው ህግ ሊሻሻል ይገባል።

28. የምርጫ ጣቢያ ሰራተኞች በተለይም ስለአከፋፈት፣ አዘጋግ እና የቆጠራ ሂደት በተመለከተ የበለጠ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል። በሂደቱ በተለያዩ ደረጃዎች ላለው የቅፅ መሙላት እና በአጠቃላይ የማጠቃለያውን ሂደት በተመለከተ ትልቅ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል።

29. ከድምፅ መስጫ ጣቢያዎች እና በምርጫ ክልል ቢሮዎች በመስፈርትነት የተቀመጡት አጠቃላይነት ያላቸው የተለያዩ ቅፆች ለመረዳት እና ለመሙላት ቀለል ባለ መልኩ የቅፆቹ አይነት ማሳነስ ይገባል። በድምፅ መስጫ ጣቢያ እና በምርጫ ክልል ቢሮዎች ያሉት ቅፆች የምርጫ ቢሮ ሰራተኞችን ስራ ለማቃለል የመቀጠሩን እና የማጠቃለል ሂደቶች ለማፋጠን ካለ ካርቦን በሚባዛ ወረቀት መዘጋጀት አለባቸው። ለድጋፍ እና የተወሰኑ የማጠቃለያ ሂደት አካላቶችን ወደ ዲጀታል ቴክኖሎጂ ለመቀየር ከኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ማዕከላት የሰለጠነ ሰው ለመላክ ሊታሰብበት ይችላል።